# ወንጌል ነፃ ያወጣል::

## የወንጌል ስርጭት ታሪክ በከምባታና ሃዲያ::

ጸሐፊ:- ዓለሙ ሕምባሮ

ኤዲተር:- ዓለማየሁ ማሞ

"በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ::" (ገላ. 5:1)::

የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved

1992



የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ግልጽ፥ ነጻ የሚያወጣና እውነተኛ የምሥራች የማዳኑ ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ በ1920 ዓ.ም በከምባታና ሃዲያ ምድር ፈነጠቀ። ዮሐ. 8:36

የመጽሐፉ መታሰቢያነት ነፃ ላወጣን ለክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ነው። በተጨማሪም የወንጌልን አደራ እስከዚህ ድረስ በታላቅ ተጋድሎ ላደረሱት የእምነት አባቶችና በእምነት ላሳደጉኝ ለእናት ቤተ፡ ወርሃኒክ፥ እንዲሁም ለዘመኑ ወጣት ምእመናን ይሁንልኝ።

# ማውጫ

ገጽ

መግቢያ
ምዕራፍ አንድ:-በኢትዮጵያ የክርስትና አመጣጥ ሂደት ............1
ምዕራፍ ሁለት:- ቅድመ- ወንጌል በከምባታና ሃዲያ ................5
1. የፈንዳኖ እምነት ሥርዓት ........................................ 6
2. የጐሣ አለቃን ማምለክና ያሳደረው ተጽዕኖ ........................ 6
3. የፀሐይ አምልኮ ልምምድ........................................ 7
4. የዛርና የአቴቴ አምልኮ የድግስ አወጣጥ............................ 8
5. የሰይጣን ውስጣዊ አሠራር ምሥጢር...............................10
ምዕራፍ ሦስት:- ድኅረ- ወንጌል በከምባታና ሃዲያ ............... 13
1. ከ 1919-1930 ዓ.ም የወንጌል ተከላ ..............................13
2. ከ 1931-1935 ዓ.ም የወንጌል አደራረስና እንቅስቃሴ ...........22
3. ከ 1936-1940 ዓ.ም በክርስቲያኖች ላይ የተነሡት ስደቶች ............................................................. 32
ሀ. የሚሽግዳ ስደት ................................................. 33
ለ. 2ኛው ዙር ስደት ................................................. 36
ምዕራፍ አራት:- የወንጌል ስርፀት በከምባታና ሃዲያ .............39
ሀ. ዱራሜ ........................................................... 39
ለ. ቦቢቾ ............................................................ 42
ሐ. ከ 1941 ዓ.ም ጀምሮ የቤተ ክርስቲያናት መደራጀት.......... 44
መ. የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር መቋቋም .................. 45
ሠ. ከ 1943 - 1965 ዓ.ም የአንጋፋ ወንጌላውያን የመላክ ሂደት............................................. 45
ረ. በእነዚያ ዘመናት የሴቶች ተሳትፎ በወንጌል ስርጭት............ 47
ሰ. የራልፍ ጄኮብሰን አገልግሎት....................................... 48
ሸ. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች መከፈት........................ 49
ቀ. የሰይጣን ሥራ መሚሸሽ........................................... 52
በ. የቤተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ በዘመነ- ደርግ (1966-1983)................................................. 55
ምዕራፍ አምስት:- ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የቤተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ .................58
ማጠቃለያ..............................................................67
ዋቢ መጻሕፍት ........................................................ 70

# መግቢያ

"የዱሮውን ዘመን አስብ፥ የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።" (ዘዳ. 32፡7)።

በዘፍጥረት 1፡31 ላይ "እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ...." በሚለው በቃሉ መሠረት ጌታ በአባቶቻችን ዘመን በከምባታና ሃዲያ ምድር የሠራውን ድንቅ ሥራ ወደ ኋላ መለስ ብለን ቃኝተን ያለፈውንና የአሁኑን ሁኔታ በማመዛዘን ለወደፊትም የሚያስጨብጠንን ተስፋ መመርኮዝ መቻል አለብን። እናም ከዕድሜ ባለጠጐች ጠይቄ የተረዳሁትን፤ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደመጣ ከታሪክ ማኅደር የተመለከትኩትንና እኔም የማውቀውን ጽፌያለሁ። የመጽሐፉ መሠረት ይህን እውነት ተረድተንና አመዛዝነን፥ በዘመናት ሁሉ የማይለወጠውን የታሪኩን ባለቤት ጌታ እግዚአብሐርን የማመስገንና የታሪኩንም ቅርስ ለትውልድ የማስቀረት አሳብ ነው።

በመጽሐፉም ውስጥ በከምባታና ሃዲያ ምድር የተፈጸመውንና ወንጌል ያመጣውን የታሪክ ለውጥ በተቻለ መጠን ሳይዛባ በታሪኩ አጥንት ላይ ሥጋ ታክሎበት መንፈሳዊ ምክሮችን በመጨመር በዝርዝር እንዲቀርብ ጥረት ተደርጎአል። አልፎ አልፎ ታሪኩ በፎቶግራፎችና በሥዕላዊ መግለጫዎች ተደግፏል። ይህ የሆነበት ምክንያት ስፋት ያለውን አሳብ ለመጠቅለልና ባጭሩ ለመግለጽ ነው። በዚሁ መሠረት እኔም በጽሑፉ ጣልቃ አስፈላጊ ናቸው የምላቸውን ተጠቅሜባቸዋለሁ። በእርግጥ ታሪካዊ የመሆናቸውን ያህል ሥዕሎቹ ዕድሜአቸው የገፋ እንደመሆኑ አልፎ አልፎ ግልጽ ባይሆኑም የእማኝነታቸውን ደረጃ ከፍ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ። ንብ አግኝቶ ማር ለመብላት ቀፎ መስቀል ያስፈልጋል። ንብም ከአበባዎች ቀስማ ማር ታዘጋጃለች። እንዲሁም ይህ ጽሑፍ ከተለያዩ መንፈሳዊ ምንጮችና ጥበብን ሊሰጥ ከሚችለው ከታላቁ መጽሐፍ ማለትም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተቀነባበሩ ጥቅሶች ስለሚገኙበት አንባቢው ጥበብን ለማግኘት ሳይሰለች ሊያነበው ይገባል። "ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል.....የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" (2ኛ ጢሞ. 3፡15-17) በሚለው መሠረት የትላንትናውን፥ የዛሬውንና የነገውን የኢየሱስን ታሪክ ለማወቅ ለሚፈልግ ሁሉ የቀረበ ጽሑፍ ነው። ኢየሱስ ለዘላለም ጌታ ነው (ዕብ. 13፡8)።

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ:: ለዚህ የጌታ ሥራ አሳብ በመስጠት፥መረጃ በማቅረብና በትየባ የተባበራችሁኝን ወገኖች ሁሉ ከልብ አመሰግናችኋለሁ::

"እውነተኛ ክርስትና የሃይማኖት ባሕል ሳይሆን ራሱን የቻለ የልብ ለውጥ ነው::" ዓለሙ ሕምባሮ

# ማስታወሻ

በመጽሐፉ ሽፋን ላይ የተመለከተው ሥዕል መግለጫዎች:-

1ኛ:- የሰው ልጅ በኃጢአት ታሥሮ በጨለማ ውስጥ ይኖር እንደነበረ ያሳያል::

2ኛ:- ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ "ተፈጸመ" ባለ ጊዜ:-

ሀ. ሰይጣን ጭንቅላቱ ተመትቶ ለዘላለም ተሸነፈ፤ ሥራውም ፈረሰ::

ለ. የኃጢአት ዕዳ በመስቀሉ ተከፈለ::

ሐ. ሞት በትንሣኤው ኃይል ድል ተመታ:: እኛም በመስቀሉ ሥራ ከዘላለም ሞት ነፃ ወጣን::

3ኛ:- የተከፈተው ወንጌል ለሁሉም በይፋ ስለተገለጠ ከታሠረበት ሠንሠለት በወንጌል ብርሃን ነፃ የወጣ ሁሉ የወንጌሉንችቦ የመስቀሉን ጸጋ ከፍ አድርጎ ይዞ ሲሮጥ የሚያሳይ ነው:: በመጽሐፉም ጌታ በረከቱን ይስጠን:: አሜን:: ጸሐፊው::

# ምዕራፍ አንድ

## በኢትዮጵያ የክርስትና አመጣጥ ሂደት

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 የተጠቀሰው ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረው ኢትዮጵያዊ ከፊልጶስ የወንጌልን እውነት ተረድቶና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምኖ ቢጠመቅም የክርስትናን እምነት ወደ አክሱም ማምጣቱን የሚነግር የታሪክ ዘገባ የለም:: ሆኖም ክስተቱ ከ40 ዓ.ም በፊት መሆኑ ግልጽ ነው::

ፍሬምናጦስ:- ከ 370-430 ዓ.ም ገደማ የኖረውና በርካታ የሥነ-መለኮት መጻሕፍትን የጻፈው የሶሪያ ምሑር ሩፊነስ የክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ በዘገበው ጽሑፉ እንደገለጸው:- "መትሮዶስ" የተባለ ፈላስፋ አንዳንድ ስፍራዎችን ለማየትና ዓለምን ለመቃኘት ወደ ሩቅ ምሥራቅ ዘልቆ ሄዶ ነበር ይላል:: የዚህን ፈላስፋ አርአያ በመከተል ሌላ የጢሮስ ፈላስፋ ደግሞ ከራሱ ጋር ዘመዶቹ የሆኑና ስለ ሰብዓዊ ኑሮ ያስተምራቸው የነበሩ ሁለት ትናንሽ ወንዶች ልጆችን አስከትሎ ተመሳሳይ ለሆነ ዓላማ ሕንድን ሊጎበኝ ተነሣ::

ከሁለቱ ልጆቹ መካከል በዕድሜ የሚያንሰው ኤዲስዩስ የሚባል ሲሆን ታላቅየው ፍሬምናጦስ ይባል ነበር:: ይህ ፈላስፋ ጉብኝቱን ከፈጸመና ነፍሱ የረካችበትን ነገር ሁሉ ከመዘገበ በኋላ ወደ መጣበት መመለስ ሲጀምር ይጓዝበት የነበረው መርከብ ውኃ ለመቅዳት ይሁን ወይም ለሌላ ጉዳይ በአንድ ወደብ ላይ ቆይታ ያደርጋል:: በዘመኑ ሥልጣኔ ያልነበራቸው ኋላ ቀር የአካባቢው ሰዎች የሚጎራበቷቸው ጎሣዎች ከሮማውያን ጋር ያላቸው ውል የፈረሰ መሆኑን ከገለጹላቸው በኋላ በመካከላቸው የሚገኙትን ሮማውያን ሁሉ ጨፍጭፎ የመግደል ልማድ ነበራቸው:: እናም ፈላስፋው ያረፈበት መርከብ እዚያው እያለ እርሱና አብረውት የነበሩት ሰዎች ተሠዩፉ::

ይሁን እንጂ ሁለቱን ልጆች ጌታ ለዓላማ አተረፋቸው:: ከወደቡ ፈቀቅ ብለው በዛፍ ጥላ ሥር ሆነው ሲያጠኑና ትምህርታቸውን ሲያዘጋጁ ስለተገኙ በእነዚህ ባልሠለጠኑ ሰዎች ምሕረት ተደርጎላቸው ወደ ንጉሣቸው ተወሰዱ::

ንጉሡም ኤዲስዩስ የተባለውን የቤተ መንግሥቱ ጠጅ አሳላፊ አድርጎ ሾመው:: ፍሬምናጦስ ግን አርቆ አስተዋይና የረጋ መሆኑን ስለተገነዘበ የቤተ መንግሥቱ የገንዘብ ቤት ሹምና ጸሐፊ አደረገው:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወጣቶቹ በክብር ይጠበቁና ንጉሡም ይወዳቸው ነበር:: ከብዙ ጊዜም በኋላ ንጉሡ ሚስቱንና ለቅቆት የሄደውን ግዛት

የሚወርስ ጨቅላ ልጁን ትቶ ሞተ:: እነዚህ ሁለት ጎልማሶችም የወደዱትን እንዲያደርጉ ነጻነት ተሰጣቸው:: ይሁን እንጂ ንግሥቲቱ ልጇ እስኪያድግ ድረስ በግዛቷ ውስጥ ሁሉ መንግሥቷን በማስተዳደር የሚረዷት ከእነርሱ የተሻሉ ሰዎች አልነበሩትም:: በተለይ ፍሬምናጦስ ግዛቷን ሊያስተዳድር የሚበቃ ችሎታ የነበረው በመሆኑና ኤዲስዩስ ደግሞ ታዛዥና ልባም የተቀበለው ሰው ስለነበር አልቅሳ ከእርሷ ጋር እንዲቆዩ ለመነቻቸው::

በዚያም ሲኖሩ ፍሬምናጦስ የመንግሥቱን ሥልጣን ጨበጠ:: እግዚአብሔርም ልቡን ስላነሣሣው ክርስቲያን የሆኑ ሮማውያን ነጋዴዎችን አፈላልጎ ከእርሱ ጋር እንዲቀራረቡ በማድረግ በተለያዩ ሥፍራዎች የጸሎት ቤቶችን እንዲመሠርቱና በሮማውያን ልማድ መሠረት ለጸሎት እንዲሰበሰቡ ወተወታቸው:: ሌሎች ሰዎችንም ለማደፋፈር ከእነዚህ ክርስቲያኖች ጋር ተባበረ:: እነርሱንም ደግሞ በውለታውና በጥቅሞች አማካይነት ወደ ራሱ አቀረባቸው፤ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ አዘጋጀላቸው፤ ለቤቶች መሥሪያና ለሚያስፈልጉ ጉዳዮች ሁሉ የሚውል መሬት ሰጣቸው:: እንዲሁም የተዘራው የክርስትና ዘር በአገሩ ውስጥ እንዲስፋፋ በተቻለው መንገድ ሁሉ ጣረ::

አገሩን በእንደራሴነት ያስተዳድሩለት የነበረው ሕፃን ሲያድግ ሥራቸውን ፈጽመውና ተቀብለውት የነበረውን አደራ በእምነት አስረክበው ንግሥቲቱና ልጇ አብረዋቸው እንዲኖሩ ሊያስቀሯቸው ቢሞክሩና ቢለምኗቸውም እንኳ እምቢ ብለው ወደ ሮማውያን ግዛት ተመልሰዋል:: ኤዲስዩስ ወላጆቹን ሊያይ ወዲያው ወደ ጢሮስ ሄደ:: ፍሬምናጦስ ግን የእግዚአብሔርን ሥራ መደበቅ መልካም አይደለም ብሎ ወደ እስክንድሪያ ተጓዘ:: በዚያ ለሚገኘውም ጳጳስ ሁኔታውን ሁሉ አጫውተው፤ ባልሠለጠኑ ኋላ ቀር ሰዎች አገር ለተሰበሰቡት በርካታ ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት አንድ ሁነኛ ሰው ፈልጎ ጳጳስ አድርጎ እንዲልክላቸው ተማጠነው:: በዚህ ወቅት ገና ኤጲስ ቆጶስ የነበረው አትናቴዎስ የፍሬምናጦስን ንግግርና ድርጊት ከመረመረ በኋላ:- “እነዚህን ነገሮች ሊያከናውን የሚችል እንዳንተ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው ማንን እናገኛለን?” ብሎ በቀሳውስት ጉባዔ ተናገረ:: ከዚያም ቀድሶ በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ መጣበት ሥፍራ ተመልሶ እንዲሄድ አዘዘው:: ፍሬምናጦስም ጳጳስ ሆኖ በ 328 ዓ.ም በመመለስ በተቀበለው ጸጋ አማካይነት ሲያገለግል ቍጥር ሥፍር የሌላቸው አረመኔዎች ወደ ጌታ ተመልሰዋል:: አባ ሰላማ ተብሎ ይጠራ የነበረው ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰ ወቅት ንጉሥ የነበረው ኢዛናም ክርስቲያን ሆነ::

በዚህ ወቅት ፍሬምናጦስ ከሶሪያና ከግብፅ ይዞት የመጣው

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተውን የክርስትና እምነት እንጂ ይዞት የመጣው ሌላ ነገር እንዳልነበረ ታሪኩ ያስረዳል:: በዘመን ቆይታ ብዛት ወደ አእምሮ ዕውቀት በመለወጥ የተዛባው እምነት ወደ ልብ እምነት በመለወጥ እንዲቃና ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው አሳብ ቢመዘዘን መልካም ነው:-

ክርስትና በትክክል ሊመሠረትበት የሚችል አንድ መሠረት ብቻ አለ፤ ይህም በወንጌሎች ውስጥ በሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ላይ ነው::

የአዲስ ኪዳን ማዕከል ወንጌላት ሲሆኑ በእነርሱ ላይ የተቀረውን የአዲስ ኪዳን ክፍል እንጨምርባቸዋለን:: ክርስትና የአዲስ ኪዳንን ትምህርት የሚቀበሉ ሰዎች ሁሉ እምነት ነው:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት እምነት ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ ሰብስቦ የሚይዝ የሰበካ ስፍራ ነው ልንል እንችላለን:: ነገር ግን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃው ሳይሆን የጌታ መንፈስ ያደረበት አማኝ ሁሉ ነው:: ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ለጸሎትና ለመጽናናት በቡድን ሲሰበሰቡ ይህ ቡድን ወይም ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራል:: ምእመናኑን÷ ትምህርታቸውን ድርጅታቸውን አጠቃልለን ክርስቲያኖች ብለን እንጠራቸዋለን::

መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው ቅዱሳት መጻሕፍትን ተጫምቶ ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰበኩት በመልእክተኞች ነው:: ምእመናን መልእክቱን ሲቀበሉ እነዚህ አዳዲስ ቡድኖች ወይም አብያተ ክርስቲያን ይመሠረታሉ::

የክርስቲያኖች ሁሉ ወላጆች መንፈስ ቅዱስና ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ከሆኑ በምንም ዓይነት መንገድ አንዱ ቡድን ከሌላው አይበልጥም ወይም አያንስም የሚል መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን:: የነዚህ ቡድኖች ታማኝነት የሚመዘነው የቤተ ክርስቲያን መሥራች በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መሠረት ላይ ሲሆን ነው::

ከዚህ የተነሣ የክርስትና ትምህርት የእያንዳንዱ ክርስቲያን በቡድኖች መደራጀትና በሰፊው ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረውን የግለሰቦችና የቡድኖች ሕይወት ለብሉይና ለአዲስ ኪዳን ትምህርት ያለውን ታማኝነት የሚያንፀባርቅ አሳብ ነው:: በመንፈስ ቅዱስና በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት የተገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተብለው የመጠራት እኩል መብት ይኖራቸዋል::

በመጀመሪያ በ 310 ዓ.ም ከሶሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የወንጌል መልእክት እውነት ወዲያውኑ በአገሪቱ ውስጥ ተከታታይ

ለውጦች አምጥቷል። በአትናቴዎስ የተቀባው ፍሬምናጦስ ያመጣው መልእክት ከአዲስ ኪዳን ትምህርት የሚስማማ በመሆኑ አረመኔነትንና የጥንቆላን መንፈስ አንኮታኩቶታል።

አባ ሰላማ በ 330 ዓ.ም በእስክንድሪያ ፓትሪያሪክ ከነበረው ከአትናቴዎስ የማጥመቅና የጌታን እራት የመስጠት ሥልጣን ተቀብሎ ነበር። በሌላ አነጋገር ቀደም ብላ በግብፅ ትገኝ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በአክሱም የተመሠረተችውን አዲስ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛነት አረጋግጣ ነበር። አትናቴዎስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሕልውና በመጀመሪያ ያጸደቀ ዝነኛ የቤተ ክርስቲያን አባት እንደሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ይገልጻል።

በ 900 ዓ.ም አካባቢ በዮዲት ዘመነ መንግሥት በአክሱም ግዛት ውስጥ በተደረጉ ለውጦች ግዕዝ ሕዝባዊ ቋንቋ ከመሆን ይልቅ የቤተ ክርስቲያን ልዩ ቋንቋ እየሆነ ስለመጣ ከዚህ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ለካህናት እንጂ ለሌላው ሕዝብ እንቆቅልሽ ወደ መሆን እንደደረሰ የትናንትና ትዝታ ነው። በቤተ ክርስቲያን ይነበብ የነበረው በግዕዝ ብቻ ነበር።

በሰሜን አብያተ ክርስቲያናት እስከ 1930 ዓ.ም ድረስ ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወደ አማርኛ እንዳልተተረጐመ ከዚህ መረዳት ይቻላል።

ካህናቱ በግዕዝ ቋንቋ ምሥጢሩን ስለያዙ ለተራው ሕዝብ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት ምሥጢር ሆኖ ሳይረዳው ለብዙ ዘመናት ዝግ ሆኖ ቆይቷል።

ክርስትና ከሰሜን አሜሪካ በጌታ ፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ የመግባቱ እንቅስቃሴ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማስገኘቱ የወንጌል ብርሃን በርቷል።

ከሰሜን አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የወንጌል መልእክተኞች ከአሜሪካን ፕሪስቤቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዙ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ መልእክተኞች በ1922 ዓ.ም ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ገብተው ደምቢዶሎና ጐሬ ሁለት መስኮችን ከፍተዋል። በ1924 ዓ.ም የአድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞች በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍላተ አገሮች ውስጥ በአዲስ ዓለም፥ በደሴ፥ በደብረ ታቦር፥ ወዘተ... የአገልግሎት መስክ ከፍተዋል።

በ1919 ዓ.ም የሱዳን ኢንተሪየር ሚስዮን የተባለው ድርጅት አባላት ክርስቲያኖች በሌሉባቸው ሥፍራዎች ሄደው ወንጌልን በመስበክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው የተቀበሉትን

በአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት ማቋቋምና ማደራጀት ጀምረው ነበር:: እነርሱም በሰሜን በደብረ ማርቆስና በላሊበላ ሁለት፥ በምዕራብ ጅማና አጋሮ ሁለት፥ በደቡብና በተለያዩ ሥፍራዎች ደግሞ በርካታ ጣቢያዎች ነበሯቸው::

እነዚህ የተለያዩ ማኅበራት እየሰፉ ሲሄዱ በአዳዲሶቹ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ምስክርነት የአብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ተጠናከረ:: በሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ በመተርጐሙም አብዛኛው ሕዝብ ያንን እያነበበ የወንጌልን ምሥጢር እየተረዳ ሄደ:: የክርስትና እምነቱን ዕድል ራሱን በራሱ ወደ መወሰን ደረጃ ደረሰ:: የአጋንንትም ምሥጢር እየከሰመ ሄደ:: "ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ" (1ኛ ዮሐ. 3:8):: ለብዙ ትውልዶች ተሰውሮ የነበረው ምሥጢር በመጨረሻው ዘመን ለቅዱሳኑ ተገለጠ:: ምሥጢሩም የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ መሆኑ ነው (ቆላ. 1:26-27):: የፍርሃት አንድነት ተወግዶ የፍቅር አንድነት ተመሠረተ:: በዚህ ሂደት ነበረ የእግዚአብሔር ቃል የኢየሱስ ክርስቶስ የደኅንነት ወንጌል ወደ ከምባታና ሃዲያ አውራጃ የደረሰው::

# ምዕራፍ ሁለት

## ቅድመ- ወንጌል በከምባታና ሃዲያ

በ 1919 ዓ.ም ግልጽ የሆነ የወንጌል እውነት ከመግባቱ በፊት የከምባታና ሃዲያ ሕዝብ በባላባታዊ ሥርዓት ሥር ስለነበረ በዓመት የተገኘውን የጤፍ ምርት በየወሩ ለመልከኞቹ (ለባለመሬቶቹ) ቀለብ ወደ ሆሣዕና ከተማ ይሸከም ነበር::

በዚያ ዘመን ለተወለዱ ሕፃናት የሰላም አየር ለመተንፈስ በጣም ችግር ነበረ:: የቀለም ትምህርትም ስላልተዳረሰ ሕዝቡ ጉዳዩን ለበላይ መሥሪያ ቤት ያመለከተ እንደሆነ ለበታች መሥሪያ ቤት የሚጻፈውን ጠማር (ደብዳቤ) በባለ ጉዳዩ እጅ ይልኩ ነበር:: ደብዳቤው በላብ እንዳይቆሽሽ በማለት የጨንገር ጫፍን ሰንጥቆ ደብዳቤውን በመሰካት በታማኝነት ያደርሳሉ:: አንዳንዴ በደብዳቤው ውስጥ ባለጉዳዩ የሚቀጣበት ሁኔታ ተገልጾ ይገኛል:: እነዚያ መልከኞችም ሕዝቡ ተምሮ ከመሃይምነት ከተላቀቀ ሥልጣናችንን ይቀማናል ከመሬቱም ያስወጣናል ብለው ያስቡ ነበር:: ስለዚህ በሳምንት ሁለት ቀን የሁዳድ እርሻቸውን በማሳረስ በዚያ ቀን ሰው ቢሞት እንኳ እንዳይቀብር በመከልከል ጨቁነው ይገዙት ነበር:: ግን

የፈሩት መሬት መልቀቅም ሆነ ሥልጣን መመለስ አልቀረላቸውም:: በሌላ ጎን ደግሞ ሰይጣን የልባቸውን ዓይን አሳውሮ መንፈሳቸውን አሥሮ ሕዝቡን ያንገላታ ነበር (2ኛ ቆሮ. 4:4)::

ለገዢው (ለሰይጣን) ልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓቶች ነበሩት::

1) የፈንዳኖ እምነት ሥርዓት:-

እስከ 1931 ዓ.ም ድረስ አብዛኛው የከምባታና ሃዲያ ሕዝብ በባዕድ አምልኮ ሥርዓት የተያዘ ነበር:: ሆኖም ቀደም ሲል በተገለጸው መሠረት በ310 ዓ.ም ገደማ ከሶሪያ ሀገር የመጣውን የወንጌልን እውነት የተቀበሉ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮችም በአካባቢው ነበሩ:: የወንጌሉ ቃል ግን አብዛኛው በግዕዝ ቋንቋ ይነበብ ስለነበረ ሰው ምሥጢሩንና እውነቱን በውል ስላልተረዳ ከባዕድ አምልኮ ሊላቀቅ አልቻለም :: የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ እንኳን የንባብ ትምህርትን በግዕዝ በመማር ፊደል የቆጠረ ቢሆንም ለትርጉሙ ባዳ እንደነበረ ያስታውሳል::

በባዕድ አምልኮ ሥርዓት በትላልቅ ድንጋዮች፥ በተራሮች፥ በታላላቅ ሰዎች መካነ መቃብር፣ በፀሐይ እና በጨረቃ፥ ወዘተ... ማምለክ የተለመደ ነበረ:: በወቅቱ ከነበሩት የባዕድ አምልኮ ልምምዶች መካከል ታዋቂዎቹ:- የፈንዳኖ እምነት፥ የጐሣ አለቃ አምልኮ፥ የጃራና የወጣ (ዛር) እምነት ሥርዓቶች ናቸው::

"<u>ፈንዳኖ</u>" ማለት ለሕሊና ጽድቅ ማለት ነው:: ይህንንም ዓይነት ጽድቅ ለማግኘት የዘመኑ ሰው በየዓመቱ በነሐሴ ወር ለተከታታይ 15 ቀናት ያህል (ፀሐይ ከመውጣቷና ከመጥለቋ በፊት) ጾም እየዋለ (ምግብ ሳይመገብ) ማክበር ነበረበት:: የነሐሴ ወር መምጣቱን ያውቁ የነበረውም ጨረቃን በመመልከትና የዓመቱን የጨረቃ ብዛት በመቁጠር ነበር::

2) የጐሣ አለቃን ማምለክና ያሳደረው ተጽዕኖ

የዘመኑ ሕዝብ በጎሣ አባላት ለተመረጠ ወይም ራሱን ለሾመ የጐሣ አለቃም ይሰግድ ነበር:: ይህም ሰው ለመመለክ ሲል ራሱን ከተራው ሕዝብ ይለያል:: ፀጉሩን ያሳድጋል፥ ሰው ከሞተበትም ቤት አይገባም:: ስለዚህ "ቃልቻችሁ፥ አምላካችሁ፥ ጠንቋያችሁ <መገናኝ> እኔ ነኝና ስገዱልኝ" ይል ነበር:: ስለዚህ የጐሣው አባላት እንደ አምላክ አድርገው ይሰግዱለታል:: ሕዝቡም በጐሣ ተከፋፍሎ በወቅቱ ያመልካቸው ከነበሩት አማልክት መካከል ጥቂቶቹ:-

- የወማሎ ጐሣ አምላክ የነበረው አባ ሰሬቾ (የአማልክት ሁሉ በላይ ማለት ነው)::

- የኑርቶ ጐሣ አምላክ የነበረው ፎጣ

- የገበራ ጐሣ አምላክ የነበረው ወብሎ

- የሀደልመና ጐሣ አምላክ የነበረው ዋበንቃ

የዳሞታ ጐሣ አምላክ የነበረው ሀምባዛ እና ሌሎችም ነበሩ::

በተለይ በከምባታ ውስጥ ለ 67 ጐሣዎች ለእያንዳንዱ (ሦስት ሦስት) በድምሩ 201 የጐሣ አለቆች (ጠንቋዮች) እንደነበሩ የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑ ሽማግሌዎች ይናገራሉ::

ከላይ የተጠቀሱት ቃልቻዎች /ጠንቋዮች/ በማር. 5:6-9 በተገለጸው መሠረት በየቤቱ ስም አውጥተው ከሚያመልኩባቸው ጥቂቶቹም "እኛ ሌጌዎን ሠራዊት አማልክት ተጠሪዎቻቸው ነን:: እናንተን ሊገድላችሁና ሊያድናችሁ፥ ሊያሳምማችሁና ሊፈውሳችሁ፥ ሊያበለጽጋችሁና ሊያደኽያችሁ ይችላል:: ስለዚህ የዕድላችሁ ሁሉ ወሣኝ በእኛ ላይ ያደረው ውቃቢ ብቻ ስለሆነ ለእርሱ ብቻ ስገዱ፤ እርሱ በእኛ ላይ አድሮ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ፥ ታዘዙ፥ ተገዙ" እያሉ የሕዝቡን ልብ አታልለው እንደፈለጋቸው አድርገውና ሕሊናቸውን አደንቁረው ይገዙአቸው ነበረ (ዘዳግ. 18:20)::

ይህም የሚያመለክተው ከሰይጣናዊ አሠራር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ነው:: ምናልባት አንድ ሰው እንደ አጋጣሚ ታምሞ ወይም በአደጋ ምክንያት ቢሞት "እኔ በእርሱ ላይ ተቀይሜ ነው የገደልኩት" ብሎ በመፎከር "እናንተም እንደ እርሱ ሞታችሁ እንዳታልቁ የሚቹን ንብረት የሚቀመጥበትን ወንበር ሳይቀር ለእኔ አስገቡ" ብሎ ያዝዛቸዋል::

ሕዝቡም በታላቅ ፍርሃት የሚቹን ንብረት በሙሉ ለቃልቻው ያስረክባል:: የሟች ልጆችም ወላጆቻቸውንና የወላጆቻቸውን ሀብት በማጣት የቁም ሞት ሞተው በድህነት ቀንበር ውስጥ ገብተው መማቀቅ ይጀምራሉ:: ሰው ታምሞ ቢድንም "የፈወስኩት እኔ ስለሆንኩ የምሥጋና መሥዋዕት አምጡልኝ" ብሎ ገንዘብ ይቀበላል::

3) የፀሐይ አምልኮ ልምምድ

ካጠራቀሙት ውስጥ ከቡና የመጀመሪያውን ምርት ድፍኑን ቆልተው፥ ትኩስ ወተት አልበው ቅቤ አንጥረው፥ የማር ወለላ አጥልለው በሰፌ ጣባ (አንድ ጉድጓዳ ሣህን በሚመስል ከሸክላ በተሠራ ዕቃ) ውስጥ በጥብጠው፥ ረዥም የሠርዶ ሣር አሥረው እየነከሩ "ይህ የፀሐይ አምልኮ ነው፥ ፀሐይ ይህንን ውሰጂ" እያሉ ወደ ውጪ አውጥተው ወደ አራቱ ማዕዘን እየዞሩ ወደ ላይ በመርጨት ያመልኩ

ነበር:: እንደዚያ ቢያመልኩም አንዳንድ ሰዎችን ጥቃቅን የእከክ በሽታ ያጠቃቸው ነበር:: ይህን በሽታ የሚያመጣው አሰልሳይ "ወሪቀአ" የሚባለው የሰይጣን ክፍል ነው ብለው ያምናሉ:: "ወሪቀአ" ማለት ከሃዲይኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ውስጥ ውስጡን የሚያመነምን ሰይጣን ማለት ነው::

ሰይጣን ሕዝቡን በሚያታልልበት መንገድ ከማናቸውም ምርት የመጀመሪያው ለባለዛሩ ይለያል:: እህል ሲደርስ የመጀመሪያው ምርት ለዚያ ለጠንቋይ ይወሰዳል፤ ከንብ ቀፎ ማር ሲቆረጥ ከአናቱ ላይ ለእርሱ ይሰጣል፤ ከብት ሲወልድ በኩሩ ለእርሱ ይገባል:: እንገሩንም እርሱ ሳይጠጣ ማንም አይቀምስም:: ቡና ሲፈላ በመጀመሪያ የተቀዳውን ሲኒ ቡና ለሰይጣን ከቤት ወደ ጓሮ ይደፉለታል:: በቆሎ እሸት ሲደርስ ንፍሮ ተቀቅሎ የመጀመሪያው በአድባር ዛፍ ሥር ተወስዶ ይበተንለታል:: በአጠቃላይ የማንኛውም ዓይነት ምርት በቅድሚያ ለእርሱ ሳይሰጥ ሰዎች የመጠቀም መብት አልነበራቸውም::

የከብት ወረርሽኝ የገባ እንደሆነ ይህንን ለመከላከል በቅቤ የተለወሰ በሶ በእሳት በተለበለበ ኮባ ጠቅልለው በአድባር ዛፍ ሥር ወስደው ያስቀምጡለታል:: ጅብ በሌሊት መጥቶ እየተጯጯኸ ሲበላው" እሰይ "ጃቻ" (ሰይጣን) በጅብ ፈረሰኛ ጋልቦ መጥቶ መሥዋዕታችንን በልቶአልና በሽታውንም አራቀልን" ብለው ምሥጋና ያቀርባሉ::

ለሰይጣን የተለየን ነገር የነኩ እንደሆነ በጭካኔ ይገድላቸዋል:: በወቅቱ ግብሩን ካላቀረቡለት ተቆጥቶ ቤተሰቡን ያለ ምሕረት በመደዳ ይገድላቸዋል፤ ከብቶቻቸውን ያከሣል፤ ወደ ቤቶቻቸው እባብ ይለቅቃል፤ ብዙ እባብ ወደ ቤት እያፏጨ ስለሚገባ ሰዎች ፈርተው እየተንቀጠቀጡ ለሰይጣንና ወኪሎቻቸው ለሆኑት ጠንቋዮች ይገዙላቸው ነበር::

4) የዛርና የአቴቴ አምልኮ የድግሥ አወጣጥ

ለዛር የሚደረገውን ድግስ ወንዶች በመሰብሰብ ይደግሳሉ፤ ዛሩም የሚወርደው በወንዶች ላይ ነው::

ለአቴቴ (ወጣ) ተሰብስበው መደገስ ያለባቸው ሴቶች ብቻ ናቸው ተብሎ ይታመናል::

በከምባትኛ፥ ዛር ጃራ፥ አቴቴ ደግሞ ወጣ ይባላል:: የጃራን ዝግጅት በተመለከተ በመጀመሪያ ከሁሉም ዓይነት ምርት የመጀመሪያው እስከ አንድ ዓመት ድረስ ይሰበሰባል፤ ከብትም ቢሆን በኩሩ ይለያል፤ ከከብቶችም መካከል አንዱን ከብት ለይቶ "ጃራ"

የእኔ ነው ብሎ ጆርባውን ከመታ ለእርሱ ተለይቶ ይቀርባል።

ዛሩን ደግሰው የሚቀበሉበት ጊዜ ሲደርስ ሕዝቡ ተሰብስቦ ባለዛሩ ለሕይወታችን አንድ መልካም ነገር ይናገረናል ብለው ስለሚያምኑ በድግሱ ላይ ተባብረው የሰውዬውን ዛር እንዲወርድ የራሱን ስም "ጃራሃዮኔ" እያሉ እየጠሩ፥ እያጨበጨቡና እያሸበሸቡ ይለምናሉ። ጨዋታው ሞቅ ሲል ባለዛሩ በራሱ ላይ የተቀባውን ቅቤ በሰይጣን ለማስላስ ወደ ጓዳ ውስጥ ይገባል። በእባብ ውስጥ ላለ ሰይጣን ቅቤውን አስልሶ ከጓዳ ወጣ ሲል በቅቤ የተሠራውን የገብስ በሶ በእጁ ላይ ተጨማሪ የተነጠረ ቅቤ እየተጨመረለት እያንከራፋ፥ እየፎከረ ይበላል። ዛሩም በወረደበት ጊዜ እየፎከረ ወደ ሕዝቡ ፊት ቀርቦ በደረቅ ወይራ እንጨት ፍልጥ በነደደው በቀይ እሳት ፍም ውስጥ በባዶ እግሩ መሃል ገብቶ ቁጭ በማለት ተንከባልሎ ምንም ሳይቃጠል ይወጣል። ቢላዋ ወይም ጦር በፍም ውስጥ ጨምሮ ብረቱ ግሎ ከቀላ በኋላ አውጥቶ ምላሱ እየተንጣጣ ይልሳል። ምላሱም ስለማይቃጠል ሰዎች በጣም ፈርተው ያከብሩታል።

ከዚህ እውነታ እንደምንረዳው ሰይጣን በሲኦል ውስጥ የእግዚአብሔር የፍርድ እሳት እንጂ ምድራዊ እሳት የማያቃጥለው ርኩስ መንፈስ መሆኑን ነው። የአቴቴ /ወጣ/ አቀባበሉም ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ ባለ አቴቴዋ ሴት ሰይጣኑ ከወረደባት በኋላ እልል- እልል እያለች በእሳት ውስጥ ገብታ ተንከባልላ ትወጣለች፤ በመጨረሻም ዘመን መኖሪያው በዘላለም እሳት ውስጥ መሆኑን ራሱ በዚህ ይገልጻል። ከዚህ ሌላ በየመንገዱ ዳር ትልቅ ዛፍ ዝግባ፥ ሾላ፥ ሎል ዛፎችን መርጠው ይሰግዳሉ፤ በዛፎቹም ላይ ቅቤ ይቀባሉ። ለምለም ሣር አጭደው /ነጭተው/ በባላው ላይ ያደርጋሉ፤ አላፊ አግዳሚ ሁሉ "ያባቴ ውቃቢ አትለፈኝ" እያለ ዛፉን እየሳመ እየሰገደለት ያልፋል።

በየአድባሩ ዛፎች ሥር ለጃቸ እያሉ ምግብ በቅቤ ሠርተው በተለበለበው የእንሰት ቅጠል ላይ ያስቀምጣሉ። ገንዘብ የጠፋበት ሰው ወደ ዛፉ ሥር ሄዶ ስዕለት ይሳላል። ገንዘቡም የተገኘ እንደሆነ ጠፍቶ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን ያህል በዛፍ ሥር ይቀበራል። ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በእምነቱ የሚታወቁ ስሞች በሐዲይኛና በከምባትኛ ቋንቋ ሐቡሳ፥ ወሪቀአ፥ ሺጣና፥ ጃቾ እየተባሉ የሚጠሩ ተባራሪ (ተወንጫፊ) አጋንንት ነበሩ። ባለዛሩ ወይም ጠንቋዩ አንዷን ልጃገረድ ለጋብቻ የፈለጋት እንደሆነ በውቃቢአቸው ስም ጆርባዋን ይመታታል፤ ማንም ከቶ ሊያገባት አይችልም። አላገባም ካለች ያላት ዕድል መሞት ብቻ ነበረ። ባለዛሩ ወይም ጠንቋዩ አካለ ስንኩል ወይም ለምጻም ቢሆን እንኳ ወደ እርሱ መሄድዋ ግዴታ ነበር። ከዚህም የምንረዳው በጋብቻ ላይም ተጽዕኖ

እንደነበረው ነው።

ሰው ቢታመም መሬት ቆፍረው ያሾልኩታል። ስድስት ስድስት ሙልሙል (ቀቀቦ) ከቆጮ ጋግረው በትኩስነቱ በቀለጠው ቅቤ እየነከሩ በበሽተኛው ግራና ቀኝ ከራስ እስከ እግሩ ድረስ በሁለቱ ጎን ያዝ ያዝ እያደረጉ ካቆዩት በኋላ ጃራ ሊጠቀምበት በሚችል ስፍራ ላይ ወስደው ያስቀምጡታል። በዚህ ዓይነት በሽታውን አራቅን ብለው ያምናሉ። ሰው ታሞ ለመሞት እያጣጣረ ሳለ ሰዎቹ ተሯሩጠው ከጐረቤት በግ ከወለደችበት ከማንም ሰው ቤት ውቃቢው የሚፈልገውን ባለመልክ ግልገል አምጥተው ነፍሱ ከመውጣቱ በፊት ችግሩን (ጦሱን) ወሳጅ (ሃይድማ) ብለው ያርዱለታል። ባለከብቱም አይከለክላቸውም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ በቤተሰብ ወስጥ ሰላም ሲጠፋ ወይም ጉንፋን ሲበዛ ጃራ ተቆጥቶ ነው በማለት አንድ ጥቁር የበግ ግልገል አርደው ወደ እንሰት ውስጥ ወስደው የወንድ ዐዋቂዎች ብቻ ሥጋውን በልተው የሆድ ዕቃውንና አጥንቱን አቃጥለው ይገቡ ነበር። ያንን ጅብ ሊበላ ማታ ቢመጣ "እሰይ በሽታችንን አራቀልን" ብለው እጅግ ይደሰታሉ።

5) የሰይጣን ውስጣዊ አሠራር ምሥጢር



አቶ ሠጋሮ ሠለጠ ኤጌዶ በሚሽግዳ ቤናራ ከአንጋፋዎቹ አማኞች አንዱ የሆኑ በሾኔ አምቡርሴ ካሉት ከአቶ ዳዕሞ አበበ ጋር በመሆን ከ1931-1938 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ስለ ጌታ እስከ አሰላ ድረስ ሁለት

ጊዜ ታሥረው በመሄድ በከምባታና ሃዲያ አውራጃ የጸሎት ቤቶች እንዲመሠረቱ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ የእምነት አባት ናቸው:: የሰይጣንን ውስጣዊ የአሠራር ምሥጢር በውስጡ ሆነው ሲያገለግሉት የነበረውን ሁኔታ ከላይ ከተገለጸው በተለይ የተናገሩት በየጐሣ ከተዘረዘሩት ለአንዱ የዘራቸው ጠንቋይ እንዴት እንደተገዙለትና የአምልኮውም ልምምድ እንዴት እንደነበረ ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ ገልጸዋል::

በአጐታቸው ልጅ ላይ ሰይጣን አድሮ ሲያስጓራው አይተው በልባቸው በጣም ይጠሉት ነበር:: ይህም የሆነው በኤፌ. 1:4 ላይ "ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን" በሚለው መሠረት ነው:: ጠንቋዩ አቶ ሠጋሮ የእርሱ የቅርብ ተጠሪው እንዲሆኑለት ቢፈልጋቸውም እርሳቸው ግን እምቢ ብለው ስለነበር ሁለት ወንዶች ልጆቻቸውን በየዓምንቱ አከታትሎ ገደለባቸው:: ቀጥሎም እየፎከረ ወደ ቤታቸው የእባብ መዓት ለቀቀባቸው:: ወደ ቤት ለገቡት እባቦች በጦር ጫፍ ላይ ቅቤ አሞልሙለው ሠክተው ሲያስልሷቸው ለጊዜው ለቅቀው ይሄዳሉ:: ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ምክንያት በዚህ ሁኔታ ዝም ብለው እየኖሩ ሳሉ፤ ከዕለታት አንድ ቀን የባለቤታቸው አባት ለዚህ ጉዳይ ሆን ብለው እስከ ቤታቸው ድረስ መጥተው "ሰው በሕይወት ቢኖር ነው ሁሉንም ነገር የሚያደርገው፤ እናም አንተ ወደ ጠንቋዩ ቤት ሄደህ አገልግለው::" ብለው ስለመከሯቸው ልባቸው ሳይፈቅድ አማታቸውን ፈርተው ወደ ጠንቋዩ ቤት ሄደው ማገልገል ይጀምራሉ:: ለጠንቋዩ ክበር ይዘው የሚያሞጋግሱት ከአካባቢው የተመረጡ በቊጥር ሰባ የሚሆኑ ሴቶች በከምባትኛ (ሞሮታ)፤ ነበሩ:: ከእነርሱ ጋር ሦስት ወንዶች (መጋዎች) በተፈጥሮው ሩር (ዕንቁር) መምቻ የሚመስል ቀልማማ ዱላ ይይዙ ነበር፤ መሪያቸው የሆነውን ጠንቋይ ሰይጣን ደወል አስይዞ እያሽከረከረ ወደ በራፍ ሲወስደው እነዚያ ሴቶች ወንዶቹ እያሞጋገሱት እያጓሩና እየጨፈሩ ይመላለሳሉ:: በዚያን ጊዜ ጠንቋዩን ይዘው ወደ ቤት ይመልሱ የነበሩት አቶ ሠጋሮ ሆኑ:: በየዓምንቱ እሑድ ሴቶቹ በጠንቋዩ ቤት ተሰብስበው ከበሮአቸውን እየደለቁ "ሀዬ" "ሀዬ"...በሚሉት ጊዜ ወንዶች "ሆአ" "ሆአ"...እያሉ ቀኑን ሙሉ እየጨፈሩ ይውላሉ:: ዘፈኑ ሞቅ ሲል በድንገት ዛሩ ወይም ሰይጣኑ በጠንቋዩ ላይ ሠፍሮ እያስጮኸ ወደ ጫካ ሊወስደው ሲያሮጠው አቶ ሠጋሮ ባላቸው ጉልበት ባለዛሩን ሰውዬ ይዘው ያስቀራሉ:: በዚያን ጊዜ ሴቶቹን ልክ እንደታረደች ዶሮ በመሬት ላይ እንፈራፍሮ የታጠቁት የቆዳ ልብሳቸው ሁሉ ተፈትቶ እርቃናቸው እስኪታይ ድረስ በመሬት ላይ ይጥላቸዋል:: ጠንቋዩን ከውጪ አምጥተው በወንበሩ ላይ ካስቀመጡት በኋላ ወደ እነዚህ ሴቶች ሄደው እንዲነሡ ዛሩ ባስተማራቸው ቃል "ሸከም"

"ሸከም"...በሚሉበት ጊዜ ሴቶቹ እየተጣደፉ ልብሳቸውን ታጥቀው ይነሣሉ::

አልፎ አልፎ እሑድ ማታ ከአካባቢው ሴቶች አንድዋ በድንገት ወደ ውጪ ወጥታ "ሀዬ" "ሀዬ"! ...ብላ ስትጮህ የሰማ ሕዝብ በሙሉ ግር ብሎ ወደ ጠንቋዩ ቤት ይሮጣል:: እነዚያ አገልጋይ ሴቶችም በሌሊት ከየቦታቸው እየተሯሯጡ ይሰበሰባሉ:: ባሎቻቸውም የሚያገለግሉት አምላክ ጠርቷቸዋል ይላሉ እንጂ ሊነኳቸውና ሊያስቀሩአቸው አይችሉም ነበር:: እነዚህ አገልጋዮች በሙሉ በእርሳቸው መሪነት ከተራራ ላይ አበባና ሳታ የሚባለውን ቅጠል (ሰይጣን እንደ ጢፍ ይጠቀምበት የነበረውን ተክል) በጥቅምትና በግንቦት ወራት ከወንዝ ድንጋዮችና የወይራ ቅጠል ከጫካ ሰብስበው በበራፉ ይከምሩ ነበር:: ይህ ለእርሱ የክብሩ መግለጫና ማሚያ ነበረ:: ሁለት ትላልቅ ከበሮዎች በቤቱ ይቀመጣሉ:: በዚያን ወቅት ጠንቋዩ ራሱ "በሰማይ ላይ ነጭ አሞራ በሚበርበት ጊዜ ሰዎች በየማግሥቱ ይሳሳማሉ:: እኔም ወንበሬን ገልብጬ ባዶዬ ወደሚባልበት አገር እገባለሁ:: ጠንቋዮች የሚንኮታኮቱበት ዘመን ይሆናል::" እያለ ይተነብይ ነበር:: የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቦታውን ሲረከብ ምንም ነገር ወደሌለበት ምድረ በዳ ለዙረት እንደሚሄድ ያውቅ ነበረና::

ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ "ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ የሚያርፍበት ቦታ በመፈለግ ውኃ በሌለበት በደረቅ ቦታ ይዞራል:: ነገር ግን አያገኝም፤ ስለዚህ ወደ ወጣሁበት ቤት ተመልሼ ልሂድ ይላል:: ተመልሶም ሲመጣ ቤቱ ባዶ ሆኖ ጸድቶ ተዘጋጅቶ ያገኘዋል:: ከዚህ በኋላ ርኵሱ መንፈስ ይሄድና ከእርሱ ይብስ የከፉ ሌሎች ሰባት አጋንንት ሰብስቦ ይመጣል:: እርሱ ቀድሞ በነበረበት ሰው ገብተው አብረው ይኖራሉ:: ስለዚህ የዚያ ሰው የመጨረሻ ሁኔታ ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ ይሆናል" ማቴ. 12: 43-45:: (ከአዲሱ ትርጉም )(መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ) በዚህ ዘመን በየከፉዎች ሰዎችም ላይ የሚሆነው ይህንኑ የመሰለ ነገር ነው::

በዚህ አጋጣሚ አባባ ሠጋሮ ለዚህ ትውልድ ያስተላለፉት መልእክት" ማስጮኸና ማስጓራት የሰይጣን ሥራ በመሆኑ ይህንኑ ረቂቅ ምሥጢሩን ሳልተረዱት፤ አባቶች፥ እናቶችና ወጣቶች ተገናኝተው በመጸለይ የሰይጣንን ሥራ ቢያፈርሱ መልካም ነው የሚል ነው:: በተጨማሪም 1ኛ ዮሐ. 4:7 እና 2ኛ ቆሮ. 2:11 "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" "በሰይጣን እንዳንታለል የእርሱን አሳብ አንስተውምና" የሚለውን አሳብ በመጥቀስ ወላጆችና ልጆች መነጣጠል እንደሌለባቸው አስገንዝበዋል::

# ምዕራፍ ሦስት

## ድኅረ- ወንጌል በከምባታና ሃዲያ

1. ከ 1919-1930 ዓ.ም የወንጌል ተከላ

"ጅማሬህም ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል" (ኢዮብ. 8:7)::

1. <u>የምሥራች ዜና</u>

"*ደቀመዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ*" (የሐዋ. 11:26)::

አዎን ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚቀበሉ የእርሱ ተከታዮች ሁሉ "ክርስቲያኖች" ተብለው የሚጠሩበት በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ላይ የተመሠረተው እውነተኛ የክርስትና እምነት መሆኑን ያስተምረናል::

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዴት ወደ ከምባታና ሃዲያ አካባቢ እንደዘለቀ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘረው መሠረት ለመግለጽ ተሞክሯል::

"...በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው" (ማቴ. 4:16)::

በመጀመሪያ የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ብቸኛ አስተዋጽኦ ያደረገችው እና ከዚህ በታች የተመለከተችው "*የሕይወት መንገድ የደኅንነት መሰላል*" መጽሐፍ የታሪክ ቅርስ ሽፋን ናት::

ይህችን "*የደኅንነት መሰላል*" የተሰኘችውን ባለ ኢትዮጵያ ባንዲራ ሽፋን ትንሽ መጽሐፍ በአዲስ አበባ አትመው ያመጡት የክርስቶስን የደኅንነት ወንጌል ለዓለም ሁሉ ለማዳረስ ባላቸው ዓላማ በዶክተር ላምቤ መሪነት በ1919 ዓ.ም በሱዳን በኩል አድርገው ወደ አዲስ አበባ የገቡት ከላይ የተጠቀሱት የወንጌል መልእክተኞች (ሚስዮናውያን) የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ነበሩ::

## የደኅንነት ፡ መሰላል ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፳፰ ፡ ፲-፲፱ ።

ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ሰማ
ያት ፡ የሚያወጣ ፡ መሰላል ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ነው ። ተጽፎአልና ፡ ኢየ
ሱስ ፡ አለ ፡ እኔ ፡ መንገድና ፡
እውነት ፡ ሕይወትም ፡ ነኝ ፡
በእኔ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ አብ ፡
የሚመጣ ፡ የለም ።
ዮሐንስ ፡ ፲፬ ፡ ፮ ።

ከሞት ፡ ወደ ፡
ሕይወት ፡ የሚያሻግ
ር ፡ ድልድይ ፡ ኢየሱስ ፡
ነው ። ተጽፎአልና ፡ ኢየሱስ ፡
አለ ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እላ
ችኋለሁ ፡ ቃሌን ፡ የሚሰማ ፡ የላ
ከኝንም ፡ የሚያምን ፡ የዘላለም ፡
ሕይወት ፡ አለው ፡ ከሞትም ፡ ወደ ፡
ሕይወት ፡ ተሻገረ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡
አይመጣም ።
ዮሐንስ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ።

ዶክተር ሳምቤ በአዲስ አበባ አንድ ሆስፒታል አቋቁመው ነበር:: ቆይተው ዘጠኝ የሥራ ባልደረቦቻቸው በእርሳቸው መሪነት ከመንግሥት የሥራ ፈቃድ ለጂማ ተሰጧቸው ሥራቸውን በዚያ ለመቀጠል በ 66 የጭነት በቅሎዎች ጓዝ ይዘው ወደዚያው ለመድረስ ጉዞአቸውን በእግርና በጭነት ጌኛ ጀመሩ:: በቀን ከ24-30 ኪሎ ሜትር በላይ ሳይጓዙ ከ500 ኪሎ ሜትር የማያንስ ርቀት ሄዱ:: በዚህ ዓይነት ወደ ጂማ ለመግባት የጀመሩት ጉዞ ከምባታና ሃዲያ አውራጃ (ዋቸሞ) ሆሣዕና ከተማ ሲደርሱ መንገድ መሳታቸውን ተረዱ:: ይሁን እንጂ እነርሱ ቢሳሳቱም መንፈስ ቅዱስ በመሪነቱ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መራቸው:: ቡድኑም "መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ" ተብሎ በኢሳ. 30፡21 የተጻፈውን ክፍል አንብቦ ልቡን አረጋጋ::

በወቅቱ የሆሣዕና ከተማ ገዢ ደጃዝማች መሸሻ ታላቅ አቀባበል

አድርገውላቸው በእርሳቸው ዘንድ ቆይተው ክሊኒክ እንዲከፍቱ ጋበዟቸው::

የቡድኑ መሪ ዶክተር ላምቤ የጉዞ ዓላማቸውን ሳይቀይሩ ወደ ደቡብ ቀጥለው ወላይታ ሲደርሱ የጊዜው አስተዳደር በታላቅ ደስታ ተቀበላቸው:: በዳሞት ተራራ አካባቢም ቦታ ሰጣቸው::

በዚያም ያገሩን ቋንቋ ተምረው ወንጌልን በአካባቢው አሠራጩ:: በኋላም በከምባታና ሃዲያ፥ በጋሙ ጎፋ፥ በሲዳሞና በከፋ ምድር ሁሉ የወንጌልን የምሥራች ዜና አዳረሱ:: እየቆዩም የቀለም ትምህርት ቤቶችንና የጤና ክሊኒኮችን ማቋቋምና ማስፋፋት ጀመሩ::

በዚህም በማቴ . 9:35 ላይ "ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር" በሚለው መርሖ ላይ የተመሠረተ ሥራ ይንቀሳቀስ ጀመር::

ድርጅቱም ዓላማው ወንጌል ባልደረሰበት የወንጌል እውነት መስበክ ነበር:: ሕዝቡ ከተቀበለ ሰብስበው ማኅበረ ምእመናን በመመሥረት ራሳቸውን በራሳቸው እንዲችሉ፣ በራሳቸው እግር ቆመው የራሳቸው የሆኑትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲያቋቁሙ ይረዷቸዋል:: የተቋቋሙትም ቤተ ክርስቲያናት እንደ እግዚአብሔር ቃል መመሪያ መሠረት በቤተ ክርስቲያን ሕዝበ ምእመናን በተመረጡ ሽማግሌዎች እንጂ አንድ ሰው ጳጳስ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን ሊመራት አይገባም የሚል የአስተዳደር ስልት የነበራቸው ናቸው (ቲቶ 1:5-9፤ 1ኛ ጢሞ. 3:1-7::) እነርሱም ሰብከው አሳምነው ያቋቋሙአቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት በዚህ ዓይነት አስተዳደር እየተመሩ በራሳቸው ቋንቋ የአምልኮ ሥነ ሥርዓትን እንዲያካሂዱ፤ መዝሙሮችንም በራሳቸው ቋንቋ እየዘመሩ ጌታን በኅብረት እንዲያመልኩ የሚያደፋፍሩ ነበሩ::

ከመንግሥት ወንጌልን እንዲሰብኩ በተለያዩ ቦታዎች የቀለም ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ጣቢያዎችን እንዲከፍቱ በተሰጣቸው ነፃነት መሠረት በአገሪቱ ውስጥ በጣም ሩቅ ገጠር ወደ ሆኑ ቦታዎች በእግር ጉዞ፥ በበቅሎዎችና በመኪና በአይሮፕላንም በረራ የወንጌልን ዜና አደረሱ:: እውነተኛውን የደኅንነት ክርስትና ለመመሥረት ባላቸው ዓላማና ዕቅድ መሠረት ተንቀሳቀሱ:: ዶክተር ቶማስ ላምቤ ፥ ሚስተር ዳፍ፥ ሚስተር ከውዝርና በሚስተር ጆን ኢ.ፊልፕስ ከነባለቤቶቻቸውና ከሌሎችም መሰል ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው በበቅሎዎቻቸው ላይ ተቀምጠው በደቡብ ኢትዮጵያ በሚዘዋወሩበት ዘመን በከምባታና ሃዲያ ምድር ሁለት ቦታዎችን ይዘው የወንጌልን እውነት ለኅብረተሰቡ ለማስተላለፍ ባደረጉት ጥረት ለመጀመሪያ ጊዜ

በ 1920 ዓ.ም ላምቡዳ በተባለ ቦታ ላይ ሠፈሩ፤ ወደዚያም ከደረሱ በኋላ ዶክተር ላምቤ ሌሎችን ቦታዎች እየተዘዋወሩ ሲቃኙ የቀሩቱ ሚስዮናውያን በላምቡዳ ተቀምጠው የወንጌልን እውነት ለአካባቢው ሕዝብ እያስተማሩ የአገሩን ሃዲይኛ ቋንቋ መለማመድ ጀመሩ::

አቶ ሽጉጤ ዳዳንና አቶ ሰብሮ ወሰሮን ልጆች ስለነበሩ ወደ ቤት ወስደዋቸው የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀትና በስፋት አስተማሯቸው:: እነርሱም ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል መድኃኒታቸው አድርገው ተቀበሉ:: ሚስዮናውያኑም በዚያ ሆነው በተለማመዱበት ቋንቋ የማቴዎስ ወንጌልን ወደ ሃዲይኛ ቋንቋ ተረጐሙ:: ከዚያም ሌላ የተለያዩ የወንጌል እውነቶችን እየተረጐሙ ማስተማር ጀመሩ:: ትንሽ ቆይተው አባ ጐሌ ጌታን ተቀበሉ:: በአማርኛ ቋንቋ የተተረጐመችው ትንሽ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ባንዲራ ሽፋን ያላት ማለት (አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ) መልክ የተጠረዘች "የሕይወት መንገድ" የመጨረሻዋ ገጽ ለታሪክ ቅርስ ቀርታ በዚህ መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት በወንጌል ስርጭት ጅማሬ ላይ ተመልክታለች::

ይህች የደኅንነት መሰላል የምትለዋ መጽሐፍ የወንጌልን እውነተኛነትን ለመግለጽ በተቀነባበሩ ጥቅሶች የተዘጋጀች በመሆንዋ በምድሪቱ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተሠራጨች:: ሚስዮናውያን ያመጡአት ስለሆነ የሚስዮን ሃይማኖት እየተባለ መጠራት ጀመረ:: ሚስዮናዊ ማለት የወንጌል መልእክተኛ ማለት ሲሆን የመጣው የጌታ ቃል እውነት ግን ለሁሉም ነበረ::

አቶ ሽጉጤ ዳዳና አቶ ሰብሮ ወስሮ እነዚህን መጻሕፍት ከአዲስ አበባ ከኤስ.አይ.ኤም ማተሚያ ቤት እያመጡ አማኞች ወደ ሚገኙበት ቦታ ድረስ በአስቸኳይ እንዲያደርሱ አሠለጠኑአቸው::

አባ ጐሌ ግን በዚያን ጊዜ ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወሩ የወንጌልን እውነት ያሠራጩ ነበር::

እነዚህ የወንጌልን ጥሪ ከሰሙት ሕዝቦች መካከል ለመጀመሪያ ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው በላምቡዳ ተቀብለው እውነተኛውን የክርስትና እምነት በከምባታና ሃዲያ ምድር ያስፋፉትን አንጋፋ የእምነት አባቶቻችንን ታሪክ እያስታወሳቸው ይኖራል::

ለመጀመሪያ ጊዜ ጌታን እንዲቀበሉ ልባቸውን የከፈተ ጌታ እግዚአብሔር ለዘለዓለም ስሙ ይባረክ::



የእምነት ዘመናቸው
1928 ዓ.ም
አቶ ሰብሮ ዋሶሮ
ወይም አባ ደግሦ

የእምነት ዘመናቸው
1929 ዓ..ም.
አቶ ሶፌቦ ኑነሞ
ወይም አባ ጎሌ

የእምነት ዘመናቸው
1920 ዓ.ም
አቶ ሽጉጤ ዳዳ

## የአባቶቻችንን አምላክ እንርሳ፡፡

ከእነዚህ አባቶች አቶ ሽጉጤ አንድ ጊዜ አነጋግሬአቸው ከነገሩኝ ነገሮች ትዝ የሚለኝ በፊልጵ. 4:4 የተገለጸውን በመጥቀስ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ÷ ክርስቲያን በሆነውና በሚሆነው ነገር ሁሉ ሁልጊዜ በጌታ ደስ መሰኘት አለበት ያሉኝ ነው፡፡ የክርስትና እምነት እንደ ዓይን መነጽር እየተወለወለ የሚጠበቅ ነው ብለው መነጽራቸውን ከዓይናቸው አውልቀው በኪሳቸው የያዙትን ንጹሕ

ጨርቅ አውጥተው በመወልወል አሳዩኝ::

2ኛ ጴጥ. 1:19 "ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራውን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ::" "...ስለዚህ የቀድመውን ትውልድ ጠይቅ፥ አባቶቻቸውም ለመረመሩት ነገር ትጋ፥..."(ኢዮብ 8:8-9)::

በዚህ ዓይነት የወንጌል ስርጭት ቀጥሎ ሚስዮናዊው ሚስተር ዳፍ ከላይ ስማቸው ከተገለጹት ከእምነት አባቶች ጋር ሆነው ከላምቡዳ አልፎ በደቡብ ክምባታ ወንጌልን ለማስፋፋት ፈለጉ :: ማዕከላዊነት ባለው ቦታ ላይ ለመስፈር ፈልገው ውኃና ድንጋይ የሚገኝበትን አካባቢ እየጠየቁ ሲዞሩ አቶ ያምቦ የሚባሉትን ሰው አግኝተው ጠየቋቸው:: እርሳቸውም "መሬት ቢሰጣችሁ በመሬቱ ላይ ምን ምን ትሠራላችሁ?" አሏቸው:: ሚስዮኖቹም "ልጆችን የቀለም ትምህርት እናስተምራለን፥ የታመመውን እናክማለን::" ሲሉ መለሱ::

አቶ ያምቦም በነገሩ አምነውበት ከመሬታቸው ቆርሰው በዱራሜ ወረዳ ጠዛ ሱሄ የሚባለውን ቦታ አሳዩአቸው:: ሚስዮኖቹም ቦታውን አይተው በልባቸው ያሰቡትን መስፈርት የሚያሟላ ቁሳቁስ መኖሩን በማወቅ ስለወደዱት ትንሽ መሬት ለ30 ዓመት ኮንትራት ያዙ:: በዚያም መሬት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የኤስ. አይ. ኤም ጣቢያ በ 1923 ዓ.ም በዱራሜ ጠዛ ተቆረቆረ:: እናም የእግዚአብሔር ወንጌል በዙሪያው ለመንቀሳቀስ ለመጀመሪያ ጊዜ እግሩን ማሳረፊያ ስፍራ አገኘ::



በጣቢያው ለመጀመሪያ ጊዜ ዮሐንስ ኢ . ፊልፕስ የሠሩት ለምድራችንም ሕዝብ ለዘመናዊ ቤቶች ሠርቶ ማሳያ የሆነው ቤት ይህ ነው:: ቤቱም የተሠራው በአምባርቾ ተራራ በስተ ምሥራቅ ባለው ሥፍራ ሲሆን በዘመኑ የነበረውን የአንባርቾ ተራራ አቀማመጥም ሁኔታ ያሳያል :: ቤቱን የሠሩት ዮሐንስ ኢ. ፊልፕስ በቤቱ ውስጥ ሳሎን፥ የአልጋ ክፍልና የእሳት ማንደጃ ክፍሎች እንደነበሩት ይናገራሉ::

በቤቱም ውስጥ አቶ አርጅኖ ያምቦ የሚባሉ ወጣት በየምሽቱ ወደ ሚስተር ፊልፕስ እየመጡ ከምባትኛ ቋንቋ አስተምረዋቸዋል:: በተማሩትም ቋንቋ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ለአቶ አርጅኖ መስክረውላቸው ጌታን ተቀብለዋል:: በየመስቀል በዓል ይታረድ ከነበረው በሬ ደም ሰው ሁሉ ለደኅንነት እያለ በየግምባሩ በሚቀባበት ወቅት "ለእኔስ የኢየሱስ ደም ይበቃኛል" ብለው ከዘመዶቻቸው ተለይተው አለመቀባታቸውን ሚስዮናዊው ይናገራሉ::

ሚስዮናውያኑም ከኢጣሊያ ወረራ በፊት ለአምስት ዓመት በዚያ ቤት ውስጥ እየኖሩ በምድሪቱ ወደ ተለያዩ ስፍራ እየተዘዋወሩ ድንኳንም ተክለው እየሰፈሩ እነርሱን ለማየት ለሚመጣው ሕዝብ የወንጌልን እውነት ይመሰክሩ ነበር::

ከላይ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያው የአገልግሎቱ አንቀሳቃሽ ዶክተር ላምቤ በበላይ ሆነው ይቆጣጠሩ ነበር:: ከእርሳቸው በታች በላምቡዳ ሚስተር ዳፍ፥ በዱራሜ ጠዛ ጆን ኤ.ፊልፕስ ይኖሩ ነበር:: ሚስተር ዳፍ የዱራሜ ጠዛ ጣቢያን ከአቶ ያምቦ በኮንትራት በያዙበት ዘመን ሚስዮኖቹ እንዳይሰፍሩ ስለፈለጉ በጊዜው ከአውራጃው አስተዳደር ሥር ሆነው ያስተዳድሩ የነበሩት ሻምበል አቦ የሚባሉ ባለሥልጣን ያስቸግሯቸው ስለነበረ አቶ ያምቦ ወደ ሊሙ ላምቡዳ ሄደው ለሚስተር ዳፍ ይህንኑ ነገሯቸው::

ሚስተር ዳፍም ይህንን ጉዳይ እንደሰሙ ወዲያውኑ አቶ ያምቦን ይዘው ወደ አውራጃው አስተዳዳሪ (ደጃዝማች መሸሻ) ሆሣዕና ከተማ ሄዱ:: በዚያን ጊዜ ደጃዝማቹ በችሎት ላይ እንዳሉ ሚስተር ዳፍ የአቶ ያምቦን እጅ ይዘው ወደ ሕዝቡ መካከል ደፍረው ገብተው በፊታቸው እጅ ነሥተው ቆሙ:: ደጃዝማቹም አይተዋቸው "ምነው? ምን አመጣችሁ?" ሲሉ ጠየቋቸው:: ሚስተር ዳፍም "በመንግሥትና በእናንተም ፈቃድ ሕዝቡን ለማስተማር ከእኚህ ሰውዬ በኮንትራት በያዝነው መሬት ላይ እንዳንሠፍር የወረዳው ረዳት አስተዳዳሪ ሻምበል አቦ ሰውየውን ያሰቃዩአቸዋል" ብለው መለሱላቸው:: በመቀጠልም "ይህንን ጉዳይ እርስዎ አሁን በዚህ ይጨርሱልናል?

ወይስ ወደ ንጉሡ ልሂድ?" ብለው አመለከቱ::

የአውራጃው አስተዳደሪም ይህንን እንደሰሙ ወዲያው ሁለት ወታደሮችን በሆሣዕና ከተማ ወደሚገኘው ወደ ሻምበል አቦ መኖሪያ ቤት ላኩ:: ሻምበሉም በፍጥነት ወደ እርሳቸው እንዲመጡ እንዲነግሯቸው አዘዙ:: ወታደሮቹም ሄደው መልእክቱን ሲነግሯቸው ሻምበሉ"አሁን ታምሜ ተኝቻለሁ" ብለው መልስ ላኩ:: ደጃዝማቹም ይህንን እንደሰሙ ወዲያውኑ ከችሎት ላይ ተነሥተው ሠራዊታቸውንና ባለጉዳዮችንም አስከትለው ወደ ሻምበሉ ቤት አመሩ:: በር ላይ ቆመውም አስጠሯቸው:: አስተዳዳሪውም የደጃዝማቹን ድምፅ ሰምተው በጣም በመደንገጥ በሁለት አሽከሮቻቸው ተደግፈው እየተንቀጠቀጡ ወደ ፊታቸው ቀርበው እጅ እየነሱ "ጌታዬ ምን አጠፋሁ?" አሉ:: ደጃዝማች መሸሻም "በመንግሥት ፈቃድ ከዚህ ሰውዬ ላይ /አቶ ያምቦን እያመለከቱ/ ሚስዮናውያን ሕዝባችንን ለማስተማር ስለያዙት ኮንትራት መሬት ጉዳይ በእኛ በኩል ካልሆነ እያላችሁ ይህንን ሰው የምታሠቃዩበት ምክንያት ምንድር ነው?" ሲሉ በኃይለ ቃል ጠየቋቸው::

ሻምበሉም "እኔ በነገሩ ውስጥ የለሁበትም" በማለት መለሱላቸው:: ደጃዝማቹም "በል በነገሩ አልነበርኩበትም፤ ለወደፊቱም አልገባበትም፤ ብለህ ና ፈርም" ብለዋቸው ወዲያው በማስፈረም ጉዳዩን በአጭር ቀጩት::

በኋላም ዓላማቸው ሳይሳካ በመቅረቱ ቁጭታቸውን ለመወጣት ብለው "አቶ ያምቦ ሳከሎ ሰው የሚበሉትን ሰዎች ወደ አገራችን አስገብቷልና በማናቸውም ጉዳይ ላይ አትተባበሩት::" በማለት በጊዜው የነበሩትን ዳኞች በማስነሣት ሕዝቡን በማሳደም የአቶ ያምቦን ልብ አሸብረው ነበር:: አንድ ቀን አቶ ያምቦ ወደ ጆን ኢ. ፊልፕስ ረዳትና በመጀመሪያ ጌታን ወደ ተቀበሉት አባት ወደ አቶ ሽጉጤ ዳዳ መጥተው "ልጄ እናንተ የቅርብ ረዳቶች ስለምታውቁ እነዚህ ነጮች የሰውን ሥጋ ይበላሉ የሚባለው ነገር እውነት ነውን? ንገረኝ" ብለው ጠየቋቸው:: አቶ ሽጉጤም መልሰው "ውሸት ነው! የሰውን ሥጋ አይበሉም፤ እነርሱ ከመሬት የሚበቅለውን አትክልት ይበላሉ:: በጓሮአቸው አትክልት ዘርተው ጌታ ከሰማይ ዝናብ እንዲያዘንብላቸው ወደ ሰማይ እያዩ ይጸልያሉ." ብለው አረጋጉአቸው::

ነገሩ በዚያ ላይ ከሽፎ ሕዝቡም "ለችግራችን አንዳንድ የቀን ሥራ እየሠራን እንዳንጠቀም የተወራ ወሬ ነው::" በማለት ያወገዙአቸውን እየተው ወደ ሚስዮኖቹ መጠጋት ጀመሩ:: ቀስ በቀስ ሕዝቡም የጌታን ቃል መስማት ጀመረ::

በ1928 ሚስዮናውያን ኢትዮጵያን ለቅቀው ከመውጣታቸው በፊት በቆዩባቸው በአምስቱ ዓመታት ውስጥ ጆን ኢ. ፊልፕስ ከባለቤታቸውና ከሁለቱም ወንድና ሴት ልጆቻቸው፥ እንዲሁም ሚስ ሆዋይት ከሚባሉ ሴት ሚስዮናዊ ጋር በመሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ መሪነት በከምባታ ምድር በፈረሶች እየተዘዋወሩ ወንጌልን እየተናገሩ ወደ ዳቶ ተራራ፥ ወደ ለመቻ፥ ወደ ባደዋቾ፥ ወደ ማሣፌና ወደ አንጋጫ ወዘተ... ተዘዋውረዋል:: በተለያየ የገበያ ሥፍራ "ከብዙ ዘመን በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ስለሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ ሞቶ ደሙን አፍስሶአል:: በእርሱ ደም ከኃጢአታችሁ ትነፃላችሁ፥ ሌላ የበሬና የበጐችን ደም አትቀቡ፤አያድናችሁም ለሰይጣን አትስገዱ" እያሉ በሚመሰክሩበት ወቅት አንዳንድ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ተቀብለዋል:: ያ የተዘራው ቃል በታ ይዞ ቆየ::

በ1925 ዓ.ም ላይ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ በጸጥታ ማነስ ምክንያት የዱራሜዎቹ ሚስዮናውያን ከነሚስተር ዳፍ ጋር ተቀላቀሉ:: በዚያም አካባቢ ፋኖዎች የሚስዮኖችን ዕቃ ዘርፈው ወሰዱባቸው:: ለሚስዮኖቹ ሕይወትም የሚያሠጋ ስለሆነ የመጀመሪያዎቹ አማንያን ከሆኑት አንዱ አባ ጐሌ ሚስዮኖችን ከፋኖዎቹ ለማስጣል ከነቤተሰቦቻቸው ይዘው እስከ እነቆር አሎልቾ ጠረፍ ለጠረፍ ይዘዋቸው ሲዘዋወሩ ሚስዮኖቹ ያልተቀየረ ልብስ ከመልበሳቸውም በላይ ያገሩን የእንሰት ሥር ሃምቾ ለመብላት ተገድደው ነበር::

ይህንን ሁሉ መከራ መቀበላቸውን ስለ ኢየሱስ ሲሉ እንደ ታላቅ ደስታ ይቆጥሩት ነበር:: በወቅቱ በከምባታ ሃዲያና በነፍጠኞች መካከል በነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ሳቢያ ጣሊያኖቹ አገሪቱን ስለተቆጣጠሩ ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ይህን የጀመሩትን የወንጌል ስርጭት አደራ በውስጣቸው ላሠለጠኑአቸው ለአቶ ሸጉጤ ዳዳ፤ ለአቶ ሰብሮ ወሰሮና ለአባ ጐሌ አስረክበው "ጌታ ቢፈቅድ በምድር ካልሆነም በሰማይ ቤታችን እንገናኛለን:: ይህንን የወንጌልን አደራ ለሌሎች አስተላልፉ" ብለዋቸው ተሰነባብተው በ1930 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ተመለሱ:: ሚስዮኖቹ በወጡባቸው ሥፍራዎች የነበሩ እፍኝ የማይሞሉ ምእመናን እየተገናኙ እየጸለዩና እየጾሙ በየአካባቢአቸው የተረከቡትን የወንጌልን አደራ በታማኝነት በመመስከራቸው ታላቅ ለውጥ ቀጠለ:: በየሥፍራው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ተቀጣጠለ:: የሰይጣን ምሽግም በየቦታው ፈራረሰ:: ስለዚህ ሚስዮኖቹ ለቀው ቢሄዱም ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያን አልተዋትም::

"ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፥

እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በአደገች ጊዜ ግን፥ ከአትክልቶች ትበልጣለች፥ የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች" (ማቴ. 13:31-32)::

## 2. ከ 1931-1935 ዓ.ም የወንጌል አደራረስና እንቅስቃሴ



አቶ ዳእሞ አበበ ከሾኔ አምቡርሴ

እኚህ አንጋፋ የእምነት ጀግና ከ1931-1938 ዓ.ም ወንጌል እንዴት እንደ ሰደድ እሳት እንደ ተሠራጨና እርሳቸውም ለዚህ ቅዱስ ሥራ ራሳቸውን ሰጥተው ወንጌል ወዳልደረሰበት አካባቢ ለመውሰድ ዓይነተኛ የወንጌል ሰባኪ እንደነበሩ ይናገራሉ.::

አንድ ቀን ከባሌ ክፍለ ሀገር አንሥቶ እስከ ከምባታ ጠምባሮ ድረስ ያለው ፍጥረት በሙሉ ሰውም እንስሳቱም፥ ዛፎችም ቤቶችም እንኳ ሳይቀሩ በምድር ላይ ለጥ ብለው ወድቀው ሊጠፉ ሲጣጣሩ ያያሉ:: እርሳቸው ብቻ በዚህ በወደቀው ፍጥረት መካከል ሁለቱን እጆቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ቆመው "ጌታ ሆይ፥ ከዚህ መዓት ዕልቂት አድነን" /ዋአ ከኒ ገትሴ.../ እያሉ በሃዲይኛ ቋንቋ ጌታን ሲማፀኑ ወዲያው አንድ መልኩ ቀስተ ደመና የሚመስል ረዥም ሰው ቀርቦ "ከዚህ ለመዳን ከፈለግህ በኢየሱስ እመን..." ይሳቸዋል:: እርሳቸውም ምንም ሳያወላውሉ ሁለቱን እጆቻቸውን አንሥተው "ሰይጣንን ክጄ ኢየሱስን አምኜዋለሁ" ብለው በጌታ ኢየሱስ አመኑ::

ከዚያ በኋላ የአካባቢአቸውን ሕዝብ በሙሉ ካሜራ የሰበሰባቸው በማስመሰል አሳይቶአቸው "በል ያመንከውን ኢየሱስን እነርሱም እንዲያምኑ ንገራቸው፥ ለጊዜው ሁሉም አምነናል ይላሉ ግን ቆይተው "ፊትተምዮ" በሀዲይኛ ቋንቋ "አይጸኑም" እነ እገሌ እነ እገሌ ግን ከአንተ ጋር ጸንተው ይቆማሉ፤ በዚሁ ሁሉ ነገር ሳትደነቅ ለራስህ በርታ፥ እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ አንተም ታርፋለህ:-

በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ::" ብሎአቸው ሄደ:: ሲነቁ ሕልም ነበረ::

ሕልሙን በነጋታው ለወላጅ አባታቸው ሲነግሯቸው አባታቸውም በጉሣቸው አንድ የታወቀ ጠንቋይ ወደነበረበት ይዘዋቸው ሄዱ:: ሕልሙንም ለጠንቋዩ ሲነግሩት "በዚህ ብላቴና ላይ ታላቁ እግዚአብሔር ሊያድርበት ስለሆነ የሚወርደውም በደም በኩል ስለሆነ ከዚህ እንደ ተመለሳችሁ አንድ በሬ አርዳችሁ በደሙ እጠቡት" ይላቸዋል:: እነርሱም ይህንን ጉዳይ ሰምተው ሄደው በሬውንም ሳያርዱ ዝም ብለው ተቀምጠው ሳሉ ይህ ከሆነ ከአንድ ሳምንት በኋላ ሁለት ወንጌላውያን ከሊሙ ላምቡዳ መጥተው ስለጌታ ኢየሱስ መስክረው አሳመኑአቸው:: እርሳቸውም በሁለት ሳምንት ውስጥ የአማርኛ ፊደል ቆጥረው ንባብ ችለው በሃዲይኛ ቋንቋ የተተረጐመውን የማቴዎስ ወንጌልን አግኝተው እያነበቡ ለጎረቤቶቻቸው ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት መመስከር ጀመሩ:: በሕልማቸው እንደተነገራቸውም አንዳንዶቹ ክደው ወደ ኋላ እስከሚመለሱ ድረስ ሁሉም አምነው ነበር:: ከዚህም በመነሣት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የወንጌልን ችቦ ይዘው በከምባትኛና በሃዲይኛ እየተረጎሙ እየተናገሩ መሮጥ ጀመሩ:: ጌታ እንዴት እንደ መረጣቸው ያብራሩት ከላይ እንደተጠቀሰው ነበር::

"እግዚአብሔር በቃሎቹ የታመነ ነው፥ በሥራውም ሁሉ ጻድቅ ነው፥ እግዚአብሔር የተፍገመገሙትን ሁሉ ይደግፋቸዋል የወደቁትንም ያነሣቸዋል::"

በዚያን ዘመን ከእርሳቸው ጋር ሆነው የወንጌልን ችቦ ይዘው በየሥፍራው ያቀጣጥሉ የነበሩት የጌታ ልጆች ታሪክ የሚያስታውሳቸው ቀዳሚ አማኞች የሚከተሉት ናቸው::

ከበሌሳ አቶ አበበ ቡሼሮ

በአሞሾራ አቶ ሞሎሮ መሌቦ

በድኒቃ አቶ አሼቦ ኤደሞና አቶ ሐንዲሶ /ወዕለቦ/

በአመቾ አቶ ሀደሮ ኤርቲሮ

በሀዎራ አቶ ድሌብ /ኤርጊቾ/

በፋነሙራ አቶ አርፍፌ /አባ ኤርበሎ/

በሺኖ አቶ ኃይሌና አቶ ሰላቶ

በኢባላ አቶ ሕምባሮ ማዴቦ

በሙጉንጂ አቶ ዶሌ አወኖ

በቃጫ ባብ ባቾሬ

በአሸራ  አባች ኢዳሞ

በአጀባ አቶ ሐቤቦ ምሴቦና አቶ ንቂስ

በዶዶባ አቶ አነሜ ጉቤቦና አቶ ዶቼ ደንታሞ

በዌራሞ አባ ሐንድሶ (ሱሞሬ)

በቤናራ አቶ ሠጋሮ ሰለጠ

በአቦንሳ አቶ ዋኖሬ አገቶ

በቃጫቢራ አቶ ጎጉሞ

በሂልፊታ አቶ ኡረጐ

በያያማ  አባች ኤርቤቶ

በሌሾ አቶ ዘመርኮ

በሚኖ አቶ ዋጫጎ

በሺንሺቾ አቶ አሼቦ... እና ሌሎችም ነበሩ::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 16፡18 ላይ ለጴጥሮስ "እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም::" ብሎ በተናገረው መሠረት የገሃነም ደጆች ሊዘጉአት የማይችሉ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት በአንጋፋ የእምነት አባቶች የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተመሥርታለች (ኤፌ. 5፡23)::

በመሠረቱ ማንኛውም እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የሚመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው::

በእነዚህ አባቶች ነበር የወንጌል ችቦ ቀጥሎ ወደ ተዘረዘሩት ቦታዎች የተስፋፋው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኩየአ | ፌነቄራ | ኤሰ | ጌሬ |
| ፋንዲዶ | ጉሙዳ | ዎባራ | ቦራራ |
| ጀንጐ | ፈረጥቀሳ | ሱሉኢ | ቦሰና |
| ገምበላዜ | ገዴ | ደውባራ | ዌረቦያ |
| ገመሻ | ሆብቾ | ጃርሶ | |

| | | |
|---|---|---|
| አሉየቃ | ቀዕላማ | ሲቄ |
| አሉላሞ | ኢባለ | ሻሸጐ |
| ዋገበታ | 1ኛ ቃጫ ቢራ | አሼ |
| ሠራራ | ባንተ ወሰን | ኤዶ |
| ሶሮ ደንሰዓ | ሸሎ | ሚሺጊዳ |
| ቡሸሉጋ | ለመቻ | ላሻ |
| ሰድቾ | ሐመአንቾ | ዛቶ |
| በንቆረአ | አንቡርሴ | ቤናራ |
| ቀርከቾ | ቡልጊታ | ጠዛ |
| ዶንጋ | ሾኔ | ጦጠንቄ |
| ዋልድያ | ቆርጋ | ዱራሜ |
| ቀዲዳ | ለኮሌ | ሄቦኮታ |
| ደነማ | ቆቆሬ | አቦንሣ |
| ያአ | ትካሬ | ጆሬ |
| ቦሊዳቂዬ | ላንጋኖ | ጌሽጐላ |
| ቆቶ | መሐል ቆርጋ | አዲሉ |
| ዋዳ | አንጁሉ | ሸሸራ..... ወዘተ:: |

በዚህ ዓይነት ወንጌል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየተዳረሰ የሰይጣንን ምሽግ ማፈራረሱን ቀጠለ::

የመጀመሪያዎቹ አማንያን እየተሰበሰቡ የበላይ አስተባባሪዎችና ሰባኪዎች ሆነው በየቦታው ጌታን የተቀበሉትን ወንጌል ወደ ማንበብ ደረጃ ለማድረስ የአማርኛ ፊደል በማስቆጠር ከፍተኛ ርብርቦሽ ቀጠሉ:: ሰዎች ቀን በየሥራቸው ላይ ውለው ማታ ከጫካ ደረቅ ቀጫጭን እንጨት በችቦ መልክ አሥረው በሚለኮስ መብራት እየተረዱ ፊደል ይማራሉ :: የተማረ ሌላውን እያስተማረ ወንጌልን ወደ ማንበብ ደረጃ የማድረስ የፍቅር ግዴታ ነበረበት::

በዚያን ዘመን አዛውንቶች ሁሉ ሳይቀሩ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ሲሉ መማር ጀመሩ:: ሴት ልጆች ግን "ሴት ተምራ ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን ስለማትችል በማጀት ቆይታ የእናቷን ሙያ ትማር" በሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ በመጀመሪያ ጊዜ አልተማሩም ነበር::

ሆኖም እየቆየ ሲሄድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነተ ጠንካራ ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ከወንዶቹ ጋር እኩል አሰልፈው ማስተማር ሲጀምሩ እንደ ትንግርት የታዩበት ወቅትም ነበረ። ትንሽም ሳይቆዩ የባሕል ተጽዕኖ ገመድ ተበጥሶ ሁሉንም ወንጌል አስተካከለ።

ቆይቶ መንግሥታትም ድጋፋቸውን አክለውበት ስለተገኘ ይኸውና ዛሬ ማንም ከማንም ሳያንስ ሁሉም በእኩልነት ደረጃ ይማራል።

በዚያ ዘመን አማኞች ፊደሎችንና አኀዞችን ከሦስት እስከ አሥራ አምስት ቀን ድረስ ተለማምደው በአማርኛ ቋንቋ ማንበብ ጀመሩ። ጽሕፈትንም እንደ ፊደሉ አቀራረጽ ትክ ብለው በማየት ወደ ትምህርት ቤት ሳይሄዱ በየቤታቸው እርሳስ፥ ወረቀትና ቀለም ስላልነበረ የቀርከሃ ቅራፊና ትናንሽ የእንጨት ገበታ ጠርበው እንደ ወረቀት በማድረግ የዛፍ ተቀጽላ አበባዎችን እንደ ቀለም ጨምቀው የመቃ ሽምበቆ ብዕር እየቀረጹ በመጠቀም ጽሕፈትን ተለማመዱ።

ከላይ የተጠቀሰውን የእንጨት ገበታ በአራት ማዕዘን ጠርበው ከሥሩ እጀታ ሠርተው ፊደሎችን በየሀዳጉ ለይተው በቀኝ ጎን ፊደል በግራ ጎን አቡጊዳ... ጽፈው ከቦታ ወደ ቦታ እየወሰዱ ይማማሩ ነበር።

አቶ ዳዕሞ አበበ የዚህ ሥራ ዋና አስተባባሪና ከአባ ጎሌ ቀጥለው የከምባታና ሃዲያ ምድር ሰባኪ ሆኑ። አቶ ዳዬቦ አበበ ደግሞ ፊደል ያወቁትን ሌሎችን እንዲያስተምሩ ወደ ልዩ ልዩ ቦታ በመመደብ ሲሠሩ፥ አቶ ኬዕምሶ ሉዳሞ ቤተሰቦችን እየተዘዋወሩ ፊደል ማስተማር ቀጠሉ።

አቶ ንቁስ ምሴቦ የአካባቢ ጉዳይ አማካሪ ፥ አቶ ሐቤቦ፥ አቶ ኤደሞ ሒቤቦና አባች ኤደሞ ከአቶ ዳዕሞ አበበ ጋር እየተዘዋወሩ ሰባኪዎች፥ አቶ ጴጥሮስ ሉዳሞ ለአስቸኳይ ጉዳይ ተላላኪ፥ አቶ ኡልቾ ኮኔ የጆንጉ፥ አቶ ተክሌ ደጋጋ በእልጊራ፥ አቶ ሄለሞ ዋደሞ ለቃጫና ለዶዶባ የፊደል አስተማሪዎች፥ አቶ ደሳለኝ ሉዳሞ ለኡንፉራ፥ አቶ ኤፍሬም አኮሼ ተመላላሽ ረዳት፥ አቶ ዶንጋ ደጋጋ የሻሸመኔ ሰባኪ፥አቶ ደግሞ ላምቤቦ የድንሰዓና የስድቾ፥ አቶ ሻንካ የኩየአ፥ የደኔና የሰድቾ፥ አቶ ቦጋለ ሉዳሞ የቃጫ ቢራ አስተማሪዎች፥ አቶ ሞሎሮ መሌቦ ደግሞ በየሰብሰባዎች ሥርዓት አስከባሪና አስተባባሪ በመሆን አገልግሎታቸውን ቀጠሉ።

በዚህ ዓይነት የወንጌል ስርጭት ይጓዝ በነበረበት ዘመን አባቶች፥ እናቶች፥ ሽማግሌዎች፥ ባልቴቶች አማኞች በሙሉ በቀድሞ ዘፈን ፈንታ መዝሙሮችን፥ በጫዋታ ፈንታ ስብከትን ቀጠሉ። ከባሕል

መዝሙሮቹም ለትዝታ ያህል በሃድይኛ ቋንቋ የወንጌል መልእክት አዘል መዝሙር ከዚህ በታች ቀርቧል።

| በሐድይኛ ቋንቋ | | ወደ አማርኛ ሲተረጐም |
|---|---|---|
| ሼጣን ሔዋን ቀዊሱኮ | (2) | ሰይጣን ሔዋንን አታለላት፥ |
| አዳም ባጢሎ አጉኮ | " | አዳምም በኃጢአት ወደቀ። |
| ኤ. ባጢሎም ዋዕ ሲዱኮ | " | ኃጢአቱንም እግዚአብሔር አወቀ። |
| ሲዳ ዕጥ ቤቶም ኡዉኮ | " | አውቆም ልጁን ሰጠ። |
| እጥ ቤት እጥ ጢግ ጉሉኮ | " | ልጁም በራሱ ደም ጨረሰ። |
| መና ኤሃኖን አመዕኔ | " | ሰዎች በዚህ አመኑ፥ |
| ኤኸም ሰቡ ኬኔና | " | ይህንን እምቢ ለሚሉት |
| ግዕል ፈረድም ኮረማኮ | " | የእሳት ፈረሰኞች ተዘጋጅተዋል |
| ሙሮ ቢላዊ ሌፈማኮ | " | የሚቆርጥ ቢላዋ ተስሏል። |
| አሴአማን ለዴአኮ | " | መልእክተኞችም ተዘጋጅተዋል |
| መና ዋአን አመዕኔሄ | " | ሰዎች በእግዚአብሔር እመኑ፥ |
| ሄአ ዋኦም በዴኼ | " | ሕያው እግዚአብሔርን ፍሩ። |
| ኢመዕን ዋኦም ሉንሴሄ | " | ሰማያዊ እግዚአብሔርን ፍሩ። |
| መና አኸኖ ቆጤሄ | " | ሰዎች በዚያ ጽኑ፥ |
| ዕመዕን መንግሥተም አጌና | " | ወደ መንግሥተ ሰማያት ልትገቡ፥ |
| አጋ ኤሄ ኡሼጥ ቶቶ | " | ገብታችሁም በዚያ ታርፋላችሁ። |

እየተባለ በቅብብሎሽ ይዘመር ነበረ። አሁንም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በእምነት አባቶች ይዘመራል።

በሐዲይኛ ቋንቋ የሚዘመርበት ምክንያት በመጀመሪያ ጌታን የተቀበሉት አንጋፋዎች ሐዲይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለነበሩ ሚስዮናውያንም በእነርሱ መካከል ተቀምጠው ሃዲይኛ ቋንቋ ተምረው የማቴዎስ ወንጌልን ወደዚሁ ቋንቋ በማስተርጎማቸው ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። በየለቅሶዎችም እንጉርጉሮዎች የሃዲይኛ ግጥም ይቀናቸው ነበር፤ ሌላ ምክንያትም ሊኖር ይችላል።

አባቶቻችንን በቦቢቾ ጣቢያ መጽሐፍ ቅዱስን ያስተማሩት ከቀድሞ ሚስዮኖች አንዱ የነበሩት ሚስተር ካውዘር የተጠቀሙት በሐዲይኛ ቋንቋ ነበር:: እርሳቸውም "እኛ ያስተማርናችሁ ሰዎች አገር ለቅቀን ስንሄድ ከእናንተ ጋር የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረው ይበልጣል" በማለት ታሪካዊ ንግግራቸውን አስቀምጠው ሄደዋል::

ይህም አባባል 1ኛ ዮሐ. 2:27 "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፥ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ" የሚለውን ያስታውሰናል:: በየአገሩ ያሉት የጌታ ልጆች ሁሉ ወደ ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ባይገቡም የጌታ ቅባት (መንፈስ ቅዱስ) ወደ እውነት ሁሉ ስለሚመራቸው የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ አለመሆኑንም መረዳት ያሻል::

ከላይ የተጠቀሰውንና ሌሎችንም የባሕል መዝሙሮች ሲዘመሩ የነበረው የዜማ ቃና በጊዜው መንፈስ ቅዱስ ያስተማራቸው ሲሆን፥ ሰዎቹ ቀድሞ በሰይጣን ግዛት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ለዛሩ ጉሪያ (መንቀጥቀጥ) ይጠቀሙበት የነበረውን የዜማ ቃና በቀጥታ ጌታን ወደ ማወደስ ለወጡት:: በየመስኩ ትንሽ ትልቅ፥ ከረዳዎችና ኮቦሌዎችም ይዘምሩ ነበር::

ከዚህ አኳያ አማኞች ሁሉ በእድሜና በጾታ እንዲሁም በሙያ መስክ ለሚቀርቡዋቸው ሁሉ ይመሰክሩ ነበር:: ልጆች፥ አባቶች፥ እናቶች፥ ባልቴቶች፥ እረኞች፥ ገበያተኞች፥ ነጋዴዎች፥ ዐዋቂዎች፥ ልጃገረዶችና እንጨት ለቃሚዎች ሁሉ ለመሰሎቻቸው ወንጌልን ሰብከዋል::

ስብከት የቻለና ያልቻለ በመዝሙር፥ በጸሎት በምስጋናና በምልጃ በመተባበር የወንጌልን እውነት አስፋፉ:: የጌታም መንፈስ የቅዱሳኖችን ኅብረት እያጠነከረ በኃይል ይሠራ ነበር:: በምእመኑም ውስጥ ከፍተኛ ፍቅር ነበረ:: መንገደኛም ወደ መንገዱ ሄዶ ባደረበት ከላይ በተጠቀሰው መዝሙር የጌታን ወንጌል ሲያበስር በ 1ኛ ቆሮ. 1:21 "በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና::" ተብሎ በተጻፈው መሠረት ሰዎችም ምንም ሳያወላውሉ ጌታን አምነው አማኞች ተብለው ይጠሩ ነበር:: በዚህ ዓይነት አሰረጫጨት ወንጌል ከ1933 ዓ.ም በኋላ በየአካባቢው በበለጠ ሁኔታ እየሰፋ ቀጠለ:: በሐዋ. 2:47 መሠረት "እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው::

ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።"

በ1933 ዓ.ም ወራሪው የኢጣሊያ ሠራዊት አገሪቱን ለቅቆ ሲሄድ አገር በባንዳዎች ተጨንቃ ሳለች "እይዞአችሁ የጠላት ሠራዊት ድባቅ ተመትቶ ስለለቀቀ ደርሰንላችኋልና በርቱ፤ ካምፑንና ግምቡን እየመታን እያባረርን መጥተናል፤ በያላችሁበት ወኔአችሁን አጠንክሩ።" የሚል ጽሑፍ በአውሮፕላን ከአርበኞች ለኢትዮጵያ ሕዝብ በየቦታው ተበተነ። ሕዝቡም ምሥጢሩን ስላወቀ በየሥፍራው ሴት ወንዱ የተቻለውን ማድረግ ጀመረ። በዚህን ጊዜ የጠላት ባንዳ የነበሩት በክርስቲያኖች ላይ ልዩ ጫና አደረጉ። ስለሆነም "ሕዝቡ ዓመፅ እንዲያካሂድ ያደረጉት በየቦታው ያሉት አማኞች የተበተነውን ደብዳቤ ምሥጢር ዐውቀው ውስጥ ለውስጥ ስላሰራጩት ነው። ስለሆነም ከያሉበት ታድነው እንዲያዙ!" የሚል የውሳኔ ትእዛዝ ከየአቅጣጫው ወጣ።

የመማር ጥቅሙ ለወንጌል ብቻ ሳይሆን በአገር ጉዳይና በማኅበራዊ ኑሮም የሚያመጣውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በዚህ መረዳት ይቻላል።

ለአማኞች ለጥቂት ጊዜ ፈተና በመብዛቱ ቢጨልምባቸውም ከድቅድቅ ጨለማ በኋላ ብርሃን እንደሚገለጥ አውቀው በዚያ በጨለማ ወቅት በጾም ጸሎት ወደ ጌታ ይበልጥ ቀረቡ። ከቦታ ወደ ቦታ እየሸሹ ለሀገሪቱ የጦር አርበኞች ይጸልዩ ነበር። ጠላትም ከአገሪቱ በመውጣቱ በጨለማ ከነበሩበት ጌታ ጠብቆአቸው ወደ ብርሃን ወጥተው መልካም አየር ለመተንፈስ እንደቻሉ አቶ ዳዕሞ አበበ ይናገራሉ።

"ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ" የሚለውን ማቴ. 10፡ 28-31 ላይ የተጻፈውን የቃሉን እውነት የተረዱ አማኞች ነበሩ።

## የወንጌል አደራ በተግባር ሲተረጎም።

የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ከሰው አንድ ነገር በመጠበቅ የሚሠራ ሥራ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮ. 9:16-17 እንዳለው "የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም። እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበስር ብቀር ወዮልኝ፥ የምሥራቹን ቃል ያለ ግዴታዬ በፈቃዴ ባበስር የድካም ዋጋ ይኖረኛል፥ በግዴታዬ ባደርገው ግን በአደራ የተሰጠኝን ኃላፊነት ፈጸምሁ እንጂ ሌላ ያደረግሁት ነገር አለ ማለት አይደለም።" (አዲስ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ)

በመጀመሪያ የወንጌል ስርጭት ጊዜ በከምባታና ሃዲያ ምድር የነበሩት አማኝ ወጣቶች በአንድነት ተባብረው እንደ ጌዴዎን ለእግዚአብሔር ክብር የማይሆኑትን የሥጋ አሳብ ማሠሮዎችን በንስሐ እየሰበሩ የጸሎት ቀንደ መለከቶቻቸውን በየቦታው እየነፉ የመልካም ሥራ ችቦዎቻቸውን በየሥፍራው እያበሩ ቀጠሉ:: ምእመናኑ የጌታን ትእዛዝ በሥራ እየተረጎሙ ለድሀ ገንዘብ እያዋጡ እየሰጡ፤ ረዳት ለሌላቸው ባልቴቶችና ለደካሞች የመኖሪያ ቤቶቻቸውን በአንድ ቀን አፍርሰው በዚያኑ ቀን ሠርተው በማስገባት፥ ክርስቲያኖች በጌታ ስም ቢታሠሩ ከሚበሉት ምርጥ ምርጡን ምግብ ስንቅ በመስጠት፥ መሬቶቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በመንከባከብ አጥር እያጠሩ እርሻቸውን በማረስ ለወንጌል ስርጭት የወጣውን ሰው ቤተሰብን በመንከባከብ ከሚበሉት አካፍለው ለወንጌላዊው በመስጠት እምነታቸውን በደግ ሥራ ፍሬ ሲያስመሰክሩ የጠላት ኃይል በየቦታው ተመታ፤ ጠንቋዮች እየከሰሙ ሄዱ::

እያንዳንዱ አማኝ የሰውነቱንና የልብሱን ንጽሕና እየጠበቀ ቤቱንና አካባቢውን እያጸዳ አጥር እያጠረ በጓሮው ጐመን እየተከለ መሬቱን በወቅቱ አርሶ እየዘራ የራሱን ልማት በየቦታው በማስፋፋት ለጐረቤቶቹ የመልካም ሥራ ችቦውን ያበራ ነበር:: በየሳምንቱም ረቡዕ እየዘመሩ ሄደው ለደከሙትና ለባልቴቶች የተስፋ ሥራ የሚሠሩበት ጊዜ ነበረ:: ከሥራ ሲመለሱም እየዘመሩ ነው :: ቤቶችን ለመሥራት በሚሄዱበት ጊዜ የራሳቸውን እንጨት፥ ገመድ፥ ሣርና ቀርከሃ ይዘው ይሄዱ ነበር:: ይህንን መልካም ምስክርነት የተመለከተ ያላመነ (ክርስቲያን ያልነበረው) ሕዝብ “ይህ ጥሩ ሃይማኖት ነው” እያለ ወደ ጌታ ይመጣ ነበር:: በዚህ ዓይነት የኅብረት ሥራ ውስጥ አንድ ወንድ ወይም ሴት የጓሮአቸውን አያያዝ የማያሳምሩ ሆነው ከተገኙ የእያንዳንዱን አማኝ ይዞታ ዞረው ለመጐብኘት የተሰየሙ ሰዎች ነበሩ:: ከሌላ አካባቢ ልምድ ቀስመው እንዲመጡ ከ 15 ቀን እስከ ሁለት ወር ድረስ ከአካባቢአቸው አርቀው በመውሰድ ተምረው እንዲመለሱና በርትተው ሠርተው ኑሮአቸውን አሻሽለው እንዲኖሩ ይረዷቸዋል::

ባሕር ዛፍ የተከለ ሰው ይሞታል የሚል እምነት ነበረ:: ስለዚህ ሌሎች ባሕር ዛፍን መትከልም አያውቁም ነበር፥ አማኞችን ጌታ ከማናቸውም ዓይነት ተጽዕኖ አውጥቷቸው ስለነበረ ምንም ሳይፈሩ ባሕር ዛፍ እያለሙ ኑሮአቸውን ያሻሽሉ ጀመር:: ቡና ዘርተው መትከልንም አያውቁም ነበር:: የአዘራሩን ሁኔታ ያወቀው ላላወቀው እያስተማረ በየጓሮአቸው የቡና ተክል ተስፋፋ::

የሸንኮራ አገዳ ተክል፥ የሙዝ ችግኝ፤ የብርቱካን እና የድንች ዘር ከሚስዮናውያንና ከወላይታ ምእመናን በኩል እያገኙ አስፋፉ:: ከዚህ

ከልማት ጎን ከላይ እንደተገለጸው የወንጌል ስርጭት በበለጠ ሥር ሰድዶ ይንቀሳቀስ ነበር:: ወንጌል ወደ ደረሰበት ሁሉ ሥልጣኔና ልማት አብሮ ይገባ ነበር::

ሰዎች ልብሶቻቸውን በእንዶድና በከብት ሽንት አጥበው ከመልበስ ወጥተው በሣሙና መጠቀምን ተለማመዱ:: ሴቶችም ቆዳን መልበስ ትተው ፍታይ ልብስ ወደ መልበስ ተሸጋገሩ:: ቤቶቻቸውን ከበፊት በተሻለ ጥራት ባለው ሁኔታ ሠርተው ዙሪያውን አጥረው በየበራፉ ልዩ ልዩ ዓይነት አበባ በመትከል አስውበው መኖር ጀመሩ::

በሰው ሞት ጊዜ ትንሣኤ እንዳለ ለማመልከት የእንጨት መስቀል፥ እንደ አበባ ረጋፊዎች መሆናችንን ለማሳየትም የአበባ ጉንጉን በመቃብር ራስጌ በማቆም ካላመኑት መቃብር ስለሚለይ በዚህ ሁናቴ የአማኞች እንቅስቃሴና የኑሮ አያያዝ ከሌሎች በቀላሉ ተለይቶ ይታወቅ ጀመር::

አማኞችም ልብሳቸውን አጥበው ጸጉራቸውን አሳጥረው ስለሚሄዱ በመንገዱ ላይ ያያቸው ሰው የጌታ ልጆች መሆናቸውን ገና ከሩቅ ይለያቸው ነበር:: ከሰይጣን ተጽዕኖም ነፃ ስለወጡ በበቅሎዎቻቸውም ላይ ሲቀመጡ ባጌጠ ዕቃ ሽላልመው ነቃ ብለው ስለሚቀመጡ የአማኞች በቅሎዎች መሆናቸውን ሰዎች ገና ከሩቅ ለይተው "ያ የሚመጣው ሰው አማኝ ነው" በማለት ይመሠክሩ ነበር::

ጌታን ተሰብስበው ለማምለክ የሣር ክዳን ቤቶችን ይሠራሉ:: በተለይም በግድግዳው ዙሪያ ላይ አልፎ አልፎ የምራቅ መትፊያ ክብ ቀዳዳዎችን ይሠሩ ስለነበረ አንድ ሰው በአምልኮ ሥነ ሥርዓት ላይ እያለ ምራቁ የመጣበት እንደሆነ ወደ ውጭ እንትፍ ይላል:: ክሰ የተጣባው ሰው በውጪ ይቀመጣል::

ምእመኑም ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲገቡ "ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ፥ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መሥዋዕት ይበልጣልና፤ እነርሱም ክፉ እንዲያደርጉ አያውቁምና:: እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን:: በእግዚአብሔር ፊት ቃል ይናገር ዘንደ ልብህ አይቸኩል፥ ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ትሁን::" ተብሎ በመክብብ 5:1-2 በተጻፈው መሠረት የእግዚአብሔርን ሕግ ተጠንቅቀው ይጠብቁ ነበር:: ለአምልኮ ወደ ጸሎት ቤት በሚገቡበት ጊዜ ትንፋሻቸውን ዋጥ አድርገው እግራቸውን ጠብቀው ሰውነታችውን ሰብስበው በታላቅ ሥነ ሥርዓት ገብተው ቃሉን በተመስጦ ያዳምጡና ለቃሉም ይታዘዙ ነበር:: በየቤቶቻቸው እናቶች የሚሠሩትን ነገር ሁሉ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" ብለው ይይዛሉ ፥ ስለዚህ በያዙት ነገር ሁሉ ላይ ታላቅ በረከት ነበረ:: ካላቸው ነገር ሁሉ ላይ አሥራትን ያወጡ

ስለነበረ ማዕዳቸውም በበረከት የተሞላ ነበረ።

በዚያን ዘመን የነበሩት ምእመናን የጌታን ሥራ ባሕላዊ አምልኮ አድርገው አይመለከቱም። የሚሠሩትን ነገር ሁሉ ከልብ ተነሣሥተው በሮሜ 12:9-13 ድረስ የተጻፈውንና "ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፥ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፥ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፥ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፥ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፥ ለጌታ ተገዙ፥ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፥ በመከራ ታገሡ፥ በጸሎት ጽኑ፥ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፥ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ" የሚለውን የአዲስ ኪዳንን ትምህርት በመጠበቅ ሥራቸውን ከቃሉ ጋር አስማምተው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሠሩ ነበር።

## ከ 1936-1940 ዓ.ም በክርስቲያኖች ላይ የተነሡ ስደቶች

ባለፈው ርእስ እንደተገለጸው አማኞች በየጸሎት ቤቱ እየተሰበሰቡ መጽናናትና መማር ጀመሩ። በኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ምእተ ዓመታት አንሥቶ ክርስትና የአገሪቱ የመንግሥት ሃይማኖት ነው በመባል ይታወቃል። ከ1855-1868 ዓ.ም በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ክርስትና በመንግሥት አሠራር ውስጥ ልዩ ድርሻ ስለነበረው የተከፋፈለውን አገዛዝ በእምነት ወደ አንድነት የማመጣት ዘይቤ ነበራቸው። በተከታታይ የተነሡ ነገሥታትም ቢሆኑ ድል ያደረጓቸውን ግዛቶች በሙሉ ክርስትናን እንዲቀበሉ የማስገደድ ሁኔታ ነበረ። የፕሮቴስታንት እምነት ወደ ከምባታና ሃዲያ በገባ ጊዜ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የባህል እምነት ለመልቀቅ ባልፈለጉ የጊዜው ባለሥልጣኖች በኩል ጠላት በረቂቅ ምሥጢር በመነሣት በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ስደቶችን ያስነሣ ነበር። ወደ ባሕል አምልኮ ሕዝቡ እንዲገባ ለማስገደድ ጥረት ተደርጎም ነበረ። ሆኖም ስላልተሳካላቸው ምክንያቶችን በመፍጠር ከመንግሥት ፈቃድ ሳይኖራችሁ መስበክና ማስተማር አትችሉም፥ በማለት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን እያነሡ ያስቸግሯቸው ነበር። ይነሡ የነበሩት ጥያቄዎችም "በማን ፈቃድ ትሰበሰባላችሁ? በማንስ ፈቃድ ወንጌልን በየቦታው ያለገደብ ትሰብካላችሁ? በማን ፈቃድ ጸሎት ቤቶችን ባልተባረከ ቦታ ሁሉ ትሠራላችሁ? በማን ፈቃድ በየጸሎት ቤት ታስተምራላችሁ?" የሚሉና የመሳሰሉት ነበሩ። በዚህም የአማኞችን ልብ ለማሸበር ይሞክሩ ነበር።

አማኞቹም "በማቴ. 28:18-20 በተጻፈው መሠረት የሰማይና የምድር ንጉሥ ታላቁ ባለሥልጣን እግዚአብሔር "እንግዲህ ሂዱና

አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፥ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" ሲል በሰጠን ትእዛዝ መሠረት ነው የምናስተምረውና አሳምነን የምናጠምቀው" በማለት የማያወላውለውን መልስ ይሰጡ ነበር:: ይህም ትእዛዝ የዓለም መንግሥታት በሙሉ ሊሽሩት አይችሉም:: ሰማይና ምድር ሲያልፉ የማያልፍ ዘላለማዊ የጌታ ትእዛዝ ነው በማለት የእምነት አቋማቸውን ይገልጡ ነበር:: መንፈስ ቅዱስም ሥራውን በድንቅና በተአምራት እያጸና የሚድኑትን ዕለት በዕለት በእነርሱ ላይ እየጨመረ ያበዛቸው ነበር::

ከ1936-1943 ዓ.ም በየወረዳው ከተነሡት የተለያዩ ስደቶች ዋና የሆነው እንዴት እንደነበረ ከዚህ በታች ቀርቧል:-

## ሀ. የሚሽግዳ ስደት

በከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የዱራሜ ጽ/ቤት ቅርንጫፍ በሆነው የሚሽግዳ ጽ/ቤት በታሪክ ዘገባ በተመለከተው መሠረት በእዚያ በነበሩት ዳኛ (ገገር) አማካይነት ባለሥልጣኖች የአካባቢውን አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን ካዱ እያሉ እያሰሩና ሀብታቸውን እየዘረፉ ያጉላሏቸው ጀመር::

አማኞቹም በዕብ. 10:34 ላይ "...የገንዘባችሁንም ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ::" ተብሎ በተጻፈው መሠረት ይህ ጥንትም ሲሆን የነበረ እንጂ በእኛ ላይ አዲስ ፈተና አልደረሰብንም በማለት በደስታ ይቀበሉት ነበር:: ሰዎችም ሲታሠሩ ከላይ እንደተገለጸው አማኞች የእነርሱን መሬት ያርሳሉ፥ ቤተሰቦቻቸውንም ይንከባከቧቸዋል፤ ይጸልዩላቸዋል:: ስደትንም እንደ ሙሉ ደስታ በመቊጠር መደሰትና መዘመር ይቀጥላሉ::

በ1936 ዓ.ም ሁለት ወታደሮች አማኞችን ለማስካድ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ተልከው ከአንጋጫ ከተማ ወደ ሚሽግዳ ሠፈር ሄደው ነበር::

በሚሽግዳ ሠፈር በአባቾ ኤዳሞ ምስክርነት ጌታን አምነው የነበሩትን ክርስቲያኖች ጌታን ካዱ እያሉ እያሠሩ ይገርፉአቸውና ይደበድቧቸው ጀመር::

በመጀመሪያው ሌሊት በአቶ ፎቼ አናሞ ቤት ለማደር ገብተው አቶ ፎቼን በቆጥ ላይ በገመድ ራሳቸውን ዘቅዝቀው በመስቀል ሲገርፉአቸውና ሲያሠቃዩአቸው በጣም ተወጥረው ሥቃይ

ስለበዛባቸው ጮኹ:: በዚህ ጊዜ ከውጪ የነበሩት ቤተሰቦቻቸው ነፍስ ለማዳን ወደ ቤት ግር ብለው ሲገቡ በቤት ውስጥ የነበረው መብራት በመጥፋቱ በቤት የነበሩት ወታደሮች በከፈቱት ተኩስ 10 አለቃ የነበረው ሁለተኛው ወታደር በገዛ ጥይታቸው ተመትቶ እዚያው ሞተ::

"...ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና..." ማቴ. 26:52:: በቃሉ መሠረት ጌታ እጅ በእጅ ሲሠራ ታይቷል::

ከዚህ የተነሣ አማኞች ነፍስ ገድለዋል ተብለው ስለተወነጀሉ ስደቱ በበለጠ ተጧጧፈ:: ንብረታቸውም ተዘረፈ:: አማኞችም እጅግ ተገረፉ፤በድብደባ ብዛት ያስወረዳቸውም ነፍስ ጡሮች ነበሩ:: በዚህ መንገላታት ውስጥም ጌታን አልካዱም::

በዚህ መንስዔ ከሚሸግዱ ከተያዙት መካከል ለማስታወስ ያህል፡- 1ኛ አቶ ሠጋሮ ሠለጦ÷ 2ኛ አቶ ለፌቦ ኤዳሞ÷ 3ኛ አቶ አጭሶ ጋጌ÷ 4ኛ አቶ ባቾሬ ካጥሶ÷ 5ኛ አቶ አንኬ ለበሴ÷ 6ኛ አቶ ለቴቦ ጫከሶ÷ 7ኛ አቶ ኬሻሞ ሐንዳሞ÷ 8ኛ አቶ ለቴቦ አልበሞ÷ 9ኛ አቶ ቦቂ አንጀ÷ 10ኛ አቶ ፊታሞ ዋቤቶ÷ 11ኛ አቶ ፎቼ አናሞ ይገኙበታል::

ሌሎችንም ከየቦታው እያደኑ ሰብስበው በመያዝ እጆቻቸውን የኋሊት የፊጥኝ አሥረው ወደ ሆሣዕና አውራጃ እሥር ቤት በመውሰድ ላይ እያሉ ወንጀላ በሚባል አውላላ ሜዳ ሲደርሱ የአባባ ሠጋሮ የእጃቸው እሥራት በጣም ከመወጠሩ የተነሣ ሕመም ሲሰማቸው በልባቸው "ጌታ ሆይ÷ ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው::" አላልክም? ብለው በ 1ኛ ቆሮ. 10:13 ላይ የተጻፈውን በመጥቀስ ጌታን ጠየቁት:: ጌታም የልብ ትርታን የሚያዳምጥ አምላክ በመሆኑ ወዲያው ከበስተኋላቸው መጥቶ የታሠሩበትን ገመድ አላላላቸው:: እግዚአብሔር የድሆችን ምኞት ሰማ ጆሮውም የልባቸውን አሳብ አዳመጠች:: እርሳቸውም ማን ነው ይህን ያደረገልኝ ብለው ወደ ኋላ ዘወር ብለው ቢመለከቱ ማንንም አላዩም:: ጌታ ይህን እንዳደረገ በልባቸው ተገንዘበው ጌታን እንዳመሰገኑ መስክረዋል:: በእርግጥም ጌታ ነበር ያላላላቸው:: ጌታ በቃሉ ታማኝ ነው::

አባባ ሠጋሮ አንዳንድ ጊዜ ሲናገሩ "በጌታ ስም በገመድ በታሠረው እጃችን ላይ ሰዓት እንድናስር እርሱ ስለሰጠን በተለይም በጌታ ሥራ ቀጠሮ ላይ ቸል ማለት የለብንም" ይሉ የነበረው ስለዚህ ነው::

ወደ ሆሣዕና እሥር ቤት ካደረሷቸው በኋላ በወህኒ ቤት ክርስቶስን

ካዱ እያሉ ሲደበድቧቸው ከነበሩት መካከል የዛቶው አባት አቶ ባቾሬ ካጥሶ ወይም ዋከቦ የሣንባ በሽታ የነበራቸው ሲደበደቡና ጀርባቸውን በጠብመንጃ ሰደፍ ሲመቷቸው ወዲያው ከበሽታቸው ድነው የዕድሜ ባለጠጋ ሆነው ቆይተው በ1985 ዓ.ም ወደ ወደዱት ጌታ ተጠቀለሉ:: በዚህ ዓለም መታጣት በሌላ ዓለም (በመንግሥተ ሰማያት) መገኘት ነው::

ሌሎቹ በዚያው እሥር ቤት ሲደበደቡ በድብደባ ብዛት ደም እየተፉ ወደ ጌታ የሄዱት 1ኛ አቶ ቦቄ አንጂ÷

2ኛ አቶ ፊታሞ ዋቤቶ ናቸው::

አስከሬናቸውም በሆሣዕና ከተማ የተቀበረ እንደሆነ ከተማውን ያረክሳል በሚል ሰበብ በመከልከሉ ወደ ቃልሻ ተወስዶ ተቀበረ:: "...እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ...እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፤ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ::" (ራእይ 7:13-14)::

በሆሣዕና ከተማ የነበረው እሥር ቤት በጣሊያኖች ወረራ ጊዜ እንደ ትልቅ መጋዘን ተሠርቶ ውስጡ በድንጋይ ስብርባሪ የተሞላ ነበር፤ በውስጡም በተናጻፊና ደም በሚጠባ ትል (ዱቁን ዱቂት) የተሞላ ነበረ:: ያም ትል ቀን ቀን ወደ መሬት ገብቶ ተደብቆ ውሎ ማታ ማታ እሥረኞችን ለመጥባት ይወጣና ያሠቃያቸው ነበር::

አማኞች በወህኒ ገብተው ሲጸልዩ ትሉ ጠፋ:: የጌታ ሥራ ዕጹብ ድንቅ ነው:: እሥረኞችም በሙሉ ከሥቃያቸው በማረፋቸው ጌታን አመሰገኑ:: በዚያን ጊዜ በእሥር ቤት ውስጥ አንድ አገር ያሰለቸ ሽፍታ ስንቅ የሚሰጠው ሰው ሳይኖረው ለአማኞች ከሚሰጠው ስንቅ እየበላ ይኖር ነበር:: አንድ ቀን ግን ከአማኞች ኪስ ገንዘብ ሠርቆ ተገኘ::

በዚያን ጊዜ አማኞች "ለእኛ ከተላከልን ስንቅ እየበላ የእኛንም ከሠረቀ ዳግመኛ ስንቅ አንሰጠውም" ተባባሉ:: አቶ ሠጋሮ ግን ወንጌል የሚለውን ቃል ፈጸሙ:: ስንቁ የእኛ አይደለም የጌታ ስጦታ ነው ይብላ" አሉ:: ሌሎች አማኞች አባባ ሠጋሮን አልሰሙአቸውምና ምግብ እንዳይበላ ከለከሉት::

ለአማኞች ከየአቅጣጫው ከሕዝበ ምእመናን ይጐርፍ የነበረው ስንቅ በዚያን ቀን ሳይመጣ ቀጥ አለ:: በረሃብ ተጨነቁ:: ኋላም ንስሐ ገብተው ወደ ጌታ ሲማጸኑ ስንቁ ከተቋረጠ ከአራት ቀን በኋላ መምጣት ጀመረ::

ጌታ አማኞችን በዚህም መንገድ ጠላቶቻቸውን መውደድ

እንዳለባቸው ያስተምራቸው ነበር:: "ጌታም አለ ፥በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" (ማቴ. 5:44-55)::

በኋላም ከሆሣዕና አውራጃ ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ አሰላ ወስደው አሠሯቸው:: በዚያ በአሰላ እሥር ቤት እያሉ አቶ ፋዕኑሮ አናሞ፥ አቶ መንተሞ ዋቤቶና አቶ አልበሞ ባኤ (የሽሎው) በእሥር ቤት መንገላታት ስለበዛባቸው ወደ ዘላለሙ ቤታቸው ሄደው አረፉ:: የቀሩቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲፈቱ ዋና ገዳይ ናቸው የተባሉት አቶ ፎቼ አናሞ የ10 ዓመት የእሥር ፍርድ ተበየነባቸው:: አቶ ፎቼም በእሥር ቤት ሲቆዩ ለ8 ዓመታት ሙሉ በእግራቸው ላይ እግር ብረት ነበረ:: ስምንት ዓመት ከታሠሩ በኋላ ለቀሩት ሁለት ዓመታት እግር ብረቱ ከእግራቸው ላይ እንዲነሣ በተወሰነላቸው ጊዜ ትዝ አላቸው እንጂ በእግራቸው ላይ ያ ማሰሪያ መኖሩንም እንዳላስታወሱ ተናገሩ:: ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ነው:: የተበየነባቸውን የ10 ዓመት እሥራት ፈጽመው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ጌታ የሠራላቸውን ውለታ እየመሰከሩ ኖረው በ1976 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በመልካም ዕረፍት ወደሚወዱት አባታቸው ተጠቀለሉ:: መዝ. /116/:6 "የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው::"

"የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው:: ከሰማይም ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው:: መንፈስ፦ አዎን ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ" (ራእ. 14: 12-13)

ለ. 2ኛው ዙር ስደት፦

ከአሰላ እሥራት በኋላ ከ1936-1940 ዓ.ም መካከል ሌላ ስደት ተነሣ:: በከምባታና ሃዲያ አውራጃ ውስጥ እምነት በበለጠ ሁኔታ መስፋፋት ጀምሮ ሳለ በየቦታው የአማኞች ጸሎት ቤቶች በተጠናከረ ሁኔታ መመሥረት ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ በዘመኑ የነበሩት ባለሥልጣኖች "በየደረሳችሁበት ቦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እያላችሁ አትሥሩ" የሚል ክስ ስላነሱ እነ አቶ ሚቆሬ ዶሌቦና ሌሎችም መሰል ጓደኞቻቸው ታስረው መንገላታት ጀመሩ:: "እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ ስለሚገኝ እርሱ በመረጠው ስፍራ ጸሎት ቤቶችን በሸለቆም ሆነ በሜዳ፥ በከተማም ሆነ በገጠር እየሠራን እንሰበሰባለን::

የአማርኛ ፊደልንም የተማረ ሳልተማረ ያስተምራል" ብለው በጠንካራ አቋም መለሱላቸው::

ከሰይጣን ቀንበር በጌታ ኃይል የመላቀቃቸው እውነት ልባቸውን ጠልቆ ገብቶአል:: እናም ከደው ወደ ኋላ በጣሉት ቀንበር ውስጥ ለመግባት አልፈለጉም:: በዓላማቸው ጸንተው መቆምን ስለመረጡ አልተበገሩላቸውም ነበር::

"ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ ቍረጡ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው" (የሐዋ. 4:19):: በዚያም ዘመን የነበሩት አማኞች ይህንን የደቀ መዛሙርትን ዓርማ ያነሡ ክርስቲያኖች ነበሩ:: "...የገዢ ቍጣ የተነሣብህ እንደሆነ ሥፍራህን አትልቀቅ" (መክ. 10:4)::

በዚህ መነሻ በሚሸግዳ ዙሪያ ከዱራሜ አካባቢ እምነታቸውን ካዱ ተብለው ወደ ሰባ የሚሆኑ አማኞች በ 1940 ዓ.ም ታሠሩ:: በዱራሜ ከተማ ባለው እሥር ቤት ውስጥ እጆቻቸውን የፊጥኝ እና የኋሊት ታሥረው ሳሉ እሥረኞችን ቀን ቀን ይጠብቅ የነበረው ዘበኛ አቧራ ረግጦ ከእሥረኞች በአንዱ ግምባር ላይ የእናንተን መስቀል አርማ በግምባርህ ላይ እሥላለሁ ብሎ ግንባሩን በጫማው በመስቀል ቅርጽ ሁለት ጊዜ ረገጠው::

አማኙ በመስቀል ቅርጽ ግምባሩ በተረገጠበት ቦታ ላይ ዛሬ የዱራሜ ቍጥር 1 ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ቤት ተሠርቶአል:: በፊት ለፊቱ ላይ ልክ እሥረኛው በተረገጠበት ትይዩ በአየር ላይ አሁን የመስቀል ዓርማ ተቀርጾ ይታያል:: በዚያ ጸሎት ቤት ሕዝቡ ዛሬ እየተሰበሰበ ጌታን የሚያመልከው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ነው::

በሚሸግዳና በዱራሜ በነበሩት ምእመናን ላይ ስደት ይጸና የነበረበት ምክንያት የጌታ እምነት ምሥጢር ጠልቆ ገብቷቸው የጸኑ ክርስቲያኖች የነበሩበት አካባቢ በመሆኑ ነበር:: አንድ አማኝ ወደ እግዚአብሔር ሲጠጋ የጠላት ፈተና ይጸናበታል:: ሆኖም "...እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፤" (ዳን. 11:11-31)::

በሆሣዕና አውራጃም ሲጠየቁ ቃላቸው ያው ስለሆነ አውራጃውም የወረዳውን ውሳኔ አጽድቆ አሠራቸው:: አማኞቹም ይግባኝ ጠይቀው ወደ ጠቅላይ ግዛቱ ወደ አሰላ ተወሰዱ:: የአሰላ ፍርድ ቤት ዳኞችም የወረዳና የአውራጃ ፍርድ ይጸናል ብለው ፈረዱባቸው::

በዚያን ዘመን ከፍተኛ ጉዳዮችን የሚያጣሩ ተዘዋዋሪ ችሎቶች ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ታዝዘው ወደ ጠቅላይ ግዛቶች ይላኩ ስለነበረ በእግዚአብሔር ቅንጅት እንደ አጋጣሚ እነዚያ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ወደ አሰላ ደርሰው ነበር።

ከእሥረኞቹ መካከል አባባ ሡጋሮ እና አቶ ዳዕሞ አበበ በአስተባባሪነት ይግባኝ ጠይቀው ለእነዚያ ባለሥልጣኖች ለማመልከት ወሰኑ። በዚያን ጊዜ ሁለቱም ይህንን አቤቱታ ከማቅረባቸው በፊት የተመካከሩበት ነገር ቢኖር የሚከተለው አሳብ ነበረ። "እነዚህ አፈንጉሦች እንደሌሎቹ ከፈረዱ ቤተ ክርስቲያናትን ላለመሥራትና ወንጌልን ላለማስተማር ወደ ከምባታና ሃዲያ ምድር አንመለስም። እንዲያውም ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ሄደን አቤት እንላለን ያለን ዕድል ወድቀን በመኪናቸው ተደፍጥጠን መሞት ብቻ ነው" በማለት ስለ ጌታ እስከ መጨረሻ ድረስ ታማኞች ሆነው ለመሞት ወሰኑ።

ከዚያም ውሳኔ በኋላ "እናንተን በሕዝብ ላይ የሾማችሁ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርንና የሰውን አደራ እንድትጠብቁ በዚህ በከፍተኛ ቦታ ላይ ሾሞአችኋልና ከእግዚአብሔር የሚመጣውን እውነተኛ የፍትሕ ውሳኔ በእናንተ በኩል እንጠብቃለን።" በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስም ጥቅሶችን ጨምረው ጽፈው ለእነዚያ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አቤቱታቸውን አቀረቡ። እግዚአብሔርም የዘገየ ቢመስልም በሚያስፈልግበት ሰዓት ጉዳዩን በእነዚያ ባለሥልጣኖች በኩል ሆኖ ለማከናወን ደረሰላቸው። እነዚያ ባለሥልጣኖችም ጉዳያቸውን በጽሞና ከመረመሩ በኋላ "ከወረዳ እስከ ጠቅላይ ግዛት ድረስ የተፈረደባችሁ ፍርድ ውሳኔ ሁሉም ውድቅ ሆኖ <ሃይማኖት የግል ነው፤ አገር የጋራ ነው> የሚል የንጉሡ ነገሥቱ መመሪያ ቃል ስለአለ ሄዳችሁ የግል አምልኮአችሁን በሚያስፈልጋችሁ ሁኔታ ልታካሂዱ ነፃነት አላችሁ" ብለው ፈረዱላቸው። አባባ ሡጋሮ ከደስታ ብዛት የተነሣ በፊታቸው ጸጥ ብለው ቆመው እንደነበር ገልጸዋል።

ቆይተውም በልባቸው ጌታን አመስግነው የፍርድ ውሳኔ ወረቀት ተቀብለው ከአሰላ ወደ ከምባታና ሃዲያ በእግር ጉዞ ጀመሩ። በአርሲ ውስጥ የሚገኘውን ከሴ በረሃ በእግራቸው አቋርጠው ሲመጡ የውኃ ጥም በጣም አሰጨነቃቸው። በአንድ ሥፍራ ላይ ቁጭ ብለው ጌታን ውኃ እንዲሰጣቸው በጸሎት ከጠየቁት በኋላ ከየት መጣ የማይባል ዝናብ ዘንቦ ከጎርፍ በመጠጣት ጥማቸውን ረክተው ጌታን እያመሰገኑ በሰላም ወደ ከምባታና ሃዲያ ምድር ደረሱ። ከደረሱም በኋላ የፍርድ ውሳኔ ወረቀቱን ለማንም ሳያሳዩ ዝም ብለው ሥራቸውን ቀጠሉ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ስደቱ አቅጣጫውን ቀይሮ ከሌላው አብሮ በመኖር

ተንጸባረቀ፡፡ ከዕድር በማስወጣት፥ ከብቶቻቸው ከሌሎች ዓለማውያን ከብቶች ጋር አብረው እንዳይውሉ በማድረግ፥ እሳት ቢጠፉ ከጐረቤት ገብተው እንዳይጭሩ በመከልከል... ወዘተ ሰይጣን የሞት ሽረቱን ትግል ቀጥሎ ነበር፡፡

ሆኖም ጌታ ከአካባቢ ጐሣዎችና ኅብረተሰብ ተጽዕኖ በላይ ስለሆነ ሕዝበ ምእመናኑ በድል እንዲወጡ ስለረዳቸው የጌታ ሥራ በየአካባቢው በተጠናከረ ሁኔታ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡

አሁን በዘመናችንም በየቦታው የሚታዩት ጸሎት ቤቶች /ቤተ ክርስቲያናት/ በዚህ ዓይነት ውጣ ውረድ በጌታ ኃይል አልፈው የተሠሩ መሆናቸውን ዐውቀን በውስጣቸውም በምንሰበሰብበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ውለታ እያሰብን በአክብሮትና በፍርሃት ማምለክ ይኖርብናል ፡፡

የጌታ ቃልም በትንሽ ጊዜ ውስጥ ተስፋፋ፤ ይኸውና እስከ ዛሬ ድረስ አለን፡፡ "ርኆቦት" ለወደፊትም እንበዛለን፡፡ (ዘፍ. 26፡22)፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የወንጌል ስርፀት በከምባታና ሃዲያ

### ሀ. ዱራሜ

ዱራሜና ቦቢቾ እነዚህ ሁለቱ ጣቢያዎች ለከምባታና ሃዲያ ምድር ሕዝብ እንደ ሁለት ዓይኖች የወንጌል ብርሃን መስጫዎች ናቸው፡፡

ከ1941-1943 ዓ.ም በነበሩት ዘመናት ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት በጣሊያን ወረራ ጸጥታ መጥፋት ምክንያት አገር ለቀው ሲሄዱ "ጌታ ቢፈቅድ በምድር ካልሆነም በሰማይ እንገናኝ" ብለው የወንጌልን አደራ ለእነ አባ ጎሌ ሰጥተው ወደ አገራቸው ሄደው የነበሩት የሱዳን ኢንቴርየር ሚስዮን አባላት ጌታ በምድር ላይ እንዲገናኙ ፈቀደላቸው፡፡ እናም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የወንጌልን ሥራ ባንቀሳቀሱበት ወቅት ቀደም ሲል በዱባንቾ የተጀመረውን ሥራ በቦቢቾ ጣቢያ ከፍተው በ1941 ዓ.ም እነ ሚስተር ካውዚር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና የቀለም ትምህርት ቤቶች አቋቁመው ማስተማር ጀመሩ፡፡ በከምባታም መካከል ይህንኑ ሥራ ለማስፋፋት በማሰብ ቀድሞ ሥራ ተጀምሮበት የነበረውን

የዱራሜ ጠዛን ጣቢያ ውል መልሰው ለማሳደስ ሞከሩ:: ሚስዮኖቹ ከቦቢች ጣቢያ እየተመላለሱ የአቶ ያምቦን ልጅ አቶ አልበሞ ያምቦን ወደ ቀድሞ ጣቢያቸው ለመመለስ በሚያነጋግሯቸው ወቅት ብዙ ውጣ ውረድ ገጥሟቸዋል::

በጊዜው ጉዳዩን ለማስፈጸም ይመላለሱ የነበሩት ሚስተር ዶናልድ የሚባሉ ሚስዮናዊ ነበሩ:: ሚስተር ዶናልድና አቶ በቀለ ኑነሞ ይህንን ጉዳይ ለመከታተል ወደ ዱራሜ ወረዳ በመጡ ጊዜ የዱራሜ ባለሥልጣኖች ሚስዮናዊውን የኢጣሊያ ሰልዳቶ ነህ፥ አቶ በቀለን ባንዳቸው ነህ ብለው አሠሯቸው:: በከተማይቱ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ የሚያልፍ ሁሉ ይታሠር ነበር:: ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሯሩጠው አስፈቷቸው::

ያኔ የነበሩት ባለሥልጣኖች "መሬታችን ለውጭ አገር ዜጋ ሊሸጥ ነው:: እነርሱ ከገቡ ሃይማኖታችንንም ያስለውጣሉ::" የሚለ አቋም ነበራቸው:: ስለዚህ ሹማምንቱ ተሰብስበው" አቶ አልበሞን ከሚሲዮኖቹ ጋር ውል እንዳይፈራረም ለማድረግ "ያልሠራውን ሥራ ሠርቷል ብለን በሐሰት ወንጅለነው ለሁለትና ለሦስት ዓመታት ያለፍርድ ይታሠር" ብለው በአድማ ተስማምተው በማግሥቱ 5 ወታደሮች ወደ አቶ አልበሞ ሄደው እንዲያመጧቸው ተፈራረሙ:: በማግሥቱ ተይዘው እንዲቀርቡ ወታደሮቹ ሲላኩ አብረው ከወሰኑት ባለሥልጣኖች አንዱ የአቶ አልበሞ ወዳጅ የነበረው በጉን ሌላ መልእክተኛ ልኮ "ልትያዝ ነው ቶሎ አምልጥ" በሚል ጥቆማ በስውር አሳወቃቸው::

ቡና በመጠጣት ላይ እያሉ የሣር ቤት ሁለት በሮች ይኖሩት ነበርና በጓሮ በር አንድ ሰው አቶ አልበሞን አስጠርቶ የተላከበትን መልእክት ነገራቸው:: ያኔ በፊተኛው በር በኩል የሚይዟቸው ወታደሮች ከተፍ አሉ:: እርሳቸውም ቀልጠፍ ብለው በቤታቸው አጠገብ ትልቅ የሾላ ዛፍ ሥር ባለው ቊጥቋጦ ውስጥ ተደብቀው የሚሆነውን ነገር ይመለከቱ ነበር:: ወታደሮቹም አቶ አልበሞን ስላላገኙ የቤቱን በር በርግደው ቆጥ ሳይቀር ፈልገው ስላጡአቸው ባለቤታቸውን ከደበቅሽበት ቶሎ አምጪው እያሉ እየደበደቡ ማጉላላት ጀመሩ::

በዘመኑ ሥርዓት በቤታቸው የነበረውን ንብረት የቡና ስኒዎችን፥ ብርጭቆዎችን፥ ገንዘብ፥ አውራ ዶሮችን ሳይቀር ዘርፈው ባለቤታቸውንም ለማሠር ይዘዋቸው ወደ ዱራሜ ወረዳ ግዛት ወስዱአቸው::

አቶ አልበሞ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይመለከቱ ስለነበር፥ ባለቤታቸውን ከወሰዱ በኋላ ወደ ቤታቸው ገብተው ሲዘረፍ

የተረፈውን ልብሳቸውን ለብሰው መጀመሪያ ወደ ጠቆመው ባለሥልጣን "ባለቤቴን በዋስ አስወጣት፥ እኔም እንደነገርከኝ አምልጬ ለአቤቱታ ወደ ሆሣዕና አውራጃ ሄጃለሁ::" ብለው ምሥጢራዊ መልእክት ልከው ወደ ሆሣዕና ሄዱ::

ሆሣዕና ሄደው በቦቢቾ ሚስዮን ጣቢያ ለነበሩ ለሚስዮኖቹ ኃላፊ አማርኛንም አቀላጥፈው ለሚናገሩ ለሚስተር ሆጅስ ነገሩአቸው:: እርሳቸውም ወዲያው እንደሰሙ በማግሥቱ አቶ አልበሞንም ይዘዋቸው ወደ አውራጃ ገዢው ጋ ወደ ሆሣዕና ከተማ ሄዱ:: አውራጃ ገዢውም ክቡር አቶ ፀሐይ ዕንቁ ሥላሴ ይባሉ ነበር::

ወደ ቢሮአቸው የአቶ አልበሞን እጅ ይዘው ገብተው "በዱራሜ ወረዳ ጠዛ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት በእጃችን የነበረውን ቦታ አሁን ከአቶ አልበሞ በውል ተቀብለን ሕዝቡን እናስተምራለን ስንል የዱራሜ ወረዳ ገዢ የአካባቢ ባለሥልጣኖችን አስተባብረው አቶ አልበሞን አሥረው ለማጉላላት ሲያድሙ በጠቋሚ አምልጠው መጥተው ነግረውናል፥ የቤታቸውንም ንብረት ዘርፈዋል" ብለው አመለከቱ::

የአውራጃ አስተዳዳሪውም በአስቸኳይ ለዱራሜ ወረዳ ገዢ ደብዳቤ ጽፈው "ነገ በሁለት ሰዓት በሆሣዕና ከተማ በአውራጃ ችሎት ላይ እንድትገኝ የሚል ትእዛዝ በአንድ ወታደር እጅ ላኩ:: ከሆሣዕና እስከ ዱራሜ ድረስ በእግር ጉዞ እንድ ሙሉ ቀን የሚፈጅ ነበር::

ወዲያውም ሚስተር ሆጅስ በመኪናቸው የተላከውን ወታደርና አቶ አልበሞን ይዘው ጣሊያን ከሆሣዕና እስከ ዱራሜ ድረስ ባሠራው አቋራጭ መንገድ በሹጻ ወደ ዱራሜ መጡ::

ወደ ዱራሜ ሲደርሱ የወረዳው ገዥ (አስተዳዳሪ) ለሥራ ጉዳይ ሾኔ አካባቢ ቆርጋ ወደሚባል ሥፍራ ወጥቷል ሲባል የተላከው ወታደር መልእክቱን የማድረስ ግዴታ ስለነበረበት ከዱራሜ ከተማ ፈረስ ተሰጥቶት ወደ ሦስት ሰዓት መንገድ በፈረስ ጋልቦ ደርሶ ለገዥው የአውራጃውን አስተዳዳሪ ትእዛዝ ጥሪ ሰጥቶ አስፈርሞ ወደ ዱራሜ ተመለሰ::

ሚስተር ሆጅስም በዱራሜ ይጠብቁት ስለነበረ የተላከውን ወታደርና አቶ አልበሞን ይዘው በዕለቱ ወደ ሆሣዕና ቦቢቾ ተመልሰው አደሩ::

የዱራሜ አስተዳዳሪ በማግሥቱ በሁለት ሰዓት ካልተገኘ ከባድ ቅጣት እንደሚያገኘውና ከሥራውም እንደሚፈናቀል ተነግሮት ስለነበር ፈርቶ ትእዛዙን አክብሮ ሌሊቱን ሲሄድ አድሮ ከሁለት ሰዓት በፊት ወደ ሆሣዕና ከተማ ደረሰ:: የአውራጃ ዋና ጸሐፊውን ግን ያንን

ጉዳይ እንዲያጉላላው አነጋገረው::

የአውራጃ ገዥውም ባላጋራችሁ መጥቷልና ኑ ብለው ወደ ቦቢቾ ወታደር ላኩ:: ሚስተር ሆጅስም ከአቶ አልበሞ ጋር ወደ አውራጃ ገዥው ቢሮ ደረሱ:: የዱራሜ ወረዳ አስተዳደር ተጠርቶ የአቶ አልበሞን ንብረት ለምን እንዳስዘረፈና ሊያስራቸውም ለምን እንደ ቃጣ ሲጠየቅ "እኔ ጉዳዩንም አላውቅሁም፤ ጉዳዩ ወደ እኔ አልደረሰም ምናልባት ሠንጋ ቀሮቹ አድርገውት እንደሆነ ገና ከዚህ ሄጄ አጣራለሁ::" ብሎ ካደ:: እነርሱ ከቦቢቾ እስከሚደረሱ ድረስ ከአውራጃው ዋና ጸሐፊ ጋር በተነጋገረው የሸንገላ ምክር መሠረት ነበረ::

አውራጃ አስተዳዳሪውም "ጉዳዩን እዚሁ ጨርሱ፤ የመሬቱን ውል አሁን ተፈራረሙ" ብለዋቸው ጸሐፊአቸውን አስጠሩ:: የአውራጃ ጸሐፊውም ተጠርቶ ወደ አውራጃው አስተዳዳሪ ፊት ቀረበ:: "ሚስዮኖቹ ከአቶ አልበሞ ስለሚይዙት መሬት ጉዳይ አሁን አፈራርመህ አስጨርስላቸው" ብለው መመሪያ ስጡት::

የአውራጃ ጸሐፊውም ከወረዳ አስተዳዳሪው ጋር ቀደም ሲል ውስጥ ለውስጥ ተነጋግረው በተስማሙት መሠረት "ጌታዬ አሁን የማፈራርምበት መዝገብ የለኝም፤ ከአዲስ አበባ እስከማመጣ ድረስ ያቆያቸዋል" በማለት ሸነገላቸው::

"ሐሰትን የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ፤ ደም አፍሳሹንና ሸንጋዩን ሰው እግዚአብሔር ይጸየፋል" (መዝ. 5፡6)::

እዚያ ከቆሙት ሰዎች አንዱ "መዝገብ በወንድም አገኘሁ ሱቅ አለ::" ብሎ ጠቆመ:: ወዲያውም የአውራጃ አስተዳዳሪውም "ከአዲስ አበባ እስከሚመጣላችሁ ትቆያላችሁ? ወይስ ገንዘባችሁ ወደፊት ይመለስላችኋልና አለ ከተባለበት ገዝታችሁ ውሉን አሁን ትጨርሳላችሁ?" በማለት ሚስተር ሆጅስን ጠየቋቸው:: እርሳቸውም በደስታ እንደሚገዙ ገለጹላቸው:: ወዲያውም ጊዜ ሳያጠፉ ከሱቁ ገዝተው አመጡ:: በዚያኑ ቀን በዚያ መዝገብ ላይ በመጀመሪያው ገጽ የዱራሜ ጣቢያ ውል በ1943 ዓ.ም ተፈጸመ::

"እግዚአብሔር÷ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስ-ለምታገለግሉአቸው÷ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና" (ዕብ. 6፡10)::

## ለ. ቦቢቾ

ለመጀመሪያ ጊዜ በቦቢቾ ሚስዮን ጣቢያ እምብዛም ባልተጠናከረ ሁኔታ በ1943 ዓ.ም መንፈሳዊ ኮንፍራንስ ተካሄደ::

ቀጥሎ በ1944 ዓ.ም በከምባታና ሃዲያ ምድር ለሁለተኛ ጊዜ በዚያው በቦቢቾ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተካሄደ:: ለኮንፍራንሱም ምእመናን ከከምባታ፥ ከባደዋቾ፥ ከጠምባሮና ከሊሙ ስንቃቸውን ይዘው በየመንገዱ እያደሩ ሄደው ተሰበሰቡ:: ለሕዝቡ ማረፊያ በተሰጡአቸው ቤቶች ውስጥ የግቻ ሣር ተነጥፎላቸው እየተኙ እያደሩ ቃሉን ይሰሙ ነበር::

የሊሙ አካባቢ የቤተ ክርስቲያን እናቶችና እህቶች እንግዶችን ለመቀበል ስንቅ አዘጋጅተው ወደ ኮንፍራንሱ ተሳታፊ ሕዝብ ማደሪያ ቤት እየዞሩ "መኝታ ለተቸገራችሁት ጅባዎች አምጥተንላችኋል፤ ስንቅ ላለቀባችሁም ከቃሉ እንዳትቀሩ ምግብ የገብስ ቆሎ አምጥተንላችኋልና ውሰዱ" እያሉ በማስተናገድ ስለ ጌታ የነበራቸውን ፍቅር ይገልጹ ነበር:: በኮንፍራንሱም የወንጌልን መልእክት እንዲያቀርቡ ተጠርተው የነበሩት እንግዳ ሚስዮናዊ ሚስተር ፐልፈር የሚባሉ አረጋዊ ሽማግሌ ነበሩ:: ከሰጡትም መልእክቶች ክፍል አጠንክረው የሰበኩት ረዳት የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን ጠብቁአቸው የሚል አደራ ነበር::

ቀጥለውም "አሁን እናንተ ከሰይጣን ጨለማ ግዛት በኢየሱስ በኩል ወደ ሚደነቅ ብርሃን ስለወጣችሁ በሰይጣን ግዛት በጨለማ ውስጥ ያሉትን ወደ ክርስቶስ በማቅረብ በወንጌል ነፃ ለማውጣት በገንዘባችሁ ጀምሩ" ብለው ጥሪ አቀረቡ::

የወንጌላዊቱ ማኅበር መሪ የነበሩ ሽማግሌዎች ተቀምጠው የመጡባቸውን በቅሎዎቻቸውን ከነሙሉ ዕቃዎቻቸው ሰጡ:: አንዳንዶቹም በቤት ያሉትን ሰጥተናል እያሉ አስመዘገቡ:: በስብሰባው የነበረው ሕዝብም የለበሰውን እያወለቀ በአንድ ቦታ ላይ መከመር ጀመረ::

ወንጌላዊውም ቀጥለው "ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ..." የሚለውን ክፍል ጠቅሰው ከተናገሩ በኋላ "ለዚህ ለወንጌል ሥራ ማን ይሄዳል?" ብለው ሲጠይቁ በስብሰባው ውስጥ የነበረው አብዛኛው ሕዝብ እጁን አነሣ:: እርሳቸውም "ሁላችሁ አትሄዱም፥ የምትቀሩት በጸሎታችሁና በገንዘባችሁ በመተባበር ከበስተኋላቸው ደጀን በመሆን የተወሰኑትን ወንጌላውያንን ትልካላችሁ ዋጋችሁም በመንግሥተ ሰማያት አንድ ይሆናል አሉ::" 1ኛ ሳሙ. 30:24፤ ሉቃ. 8:1-3 ተመልከት::

በዚያን ጊዜ የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረቱት አልበርት ብራንት በዚያ አውራጃ ብዙ ወንጌላውያን እንደሚያስፈልጉ ሲናገሩ በወንጌላውያን ዝርዝር የተገለጹት ፈቃደኞች ሊሄዱ ተነሥተው ተመዘገቡ:: በዚያን ጊዜ ፕሮግራሙን ያስተባብሩ የነበሩት

የአሞሾራው አቶ ሞሎሮ መሌቦ ነበሩ:: እርሳቸው በሀዲይኛ ቋንቋ መዝሙሮችን በየስብሰባዎች የመዘመር ስጦታ ነበራቸው::

ያኔ የተጀመረው ኮንፍራንስ አንድ ዓመት በቦቢቾ ጣቢያ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ በዱራሜ በየበጋ ወራት እየተደረገ ሥራውም በጥንስሱ ላይ በነበረው ሁኔታ ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ ለ 31 ዓመታት ሲካሄድ ቆየ::

ከዚያም ጌታ በሁለቱ ጣቢያዎች ላይ ይፈስ የነበረውን መንፈሳዊ በረከት ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አዘዋውሮ በየቀዬአቸው እንዲቀጥሉ አደረገ::

ከዚህ ቀጥሎ የወንጌል እንቅስቃሴ የዕድገት ሂደት በዝርዝር ይቀጥላል::

ሚስተር ዶንዋልድ የዱራሜን ጣቢያ ሁኔታ ካመቻቹ በኋላ የሚስዮናውያንን የመኖሪያ ቤቶችን ለመሥራት በ 1944 ዓ.ም ሚስተር እስፖር ወደ ዱራሜ ጠዛ ደረሱ:: ቀጥለው ራልፍ ጄኮብሰንና ገስ ካይዘር ሌሎችም ሚስዮናውያን ጭምር ከቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ጠዛ ጣቢያ ደረሱ:: ራልፍ ጄኮብሰን በጠዛ ግቢ በየሳምንቱ ማክሰኞ የየቤተ ክርስቲያናት መሪዎችን፣ ዓርብ ደግሞ ወጣት ለክርስቶስ አገልጋዮችን በመሰብሰብ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ አስተምህሮ በጌታ ቃል መሠረት ሳይጨምሩ ሳያጉድሉ አስተማሩ (ዘዳ 4:2)::

## ሐ. ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ የቤተ ክርስቲያናት መደራጀት

የከምባታና ሃዲያ ማኅበር በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 2 እና 3 በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተመለከተው መሠረት ገና ወደፊት በዓለም ዙሪያ ለሚወለዱት አብያተ ክርስቲያናት ዓይነተኛ ምሳሌ ሆነው መስጠታቸውን የተገነዘቡ ነበሩ:: በማቴ. 18:19-20 "ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል:: ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ" ተብሎ በተጻፈው አምላካዊ ቃል መሠረት ከየአካባቢው ቤተ ክርስቲያናት የተውጣጡ መሪዎች ከሚስዮኖቹ ጋር ስለ ወንጌል ሥርጭት ጉዳይ በመመካከርና በመስማማት በየአጥቢያ የሚገኙትን ቤተ ክርስቲያናትን እንደ የአካባቢአቸው ቅርበት በመመደብ የሰባቱን አብያተ ክርስቲያናትን ስም መሠረት በማድረግ ሰባት ማኅበራትን መመደብ ጀመሩ::

በዚሁም መሠረት:- 1ኛ ሊሙ ሰባት፥ 2ኛ አምቡርሴ ሰባት፥ 3ኛ ኩየአ ሰባት፥ 4ኛ ድኒቃ ሰባት፥ 5ኛ ሶሮ ደንስዓ ሰባት፥ 6ኛ ጠምባሮ ሰባት፥ 7ኛ ዶንጋ ሰባት፥ 8ኛ እልጊራ ሰባት፥ 9ኛ ሚሽግዳ ሰባት፥ 10ኛ አሸራ ሰባት ተሰየሙ:: በኋላ ቆይተው በ 1948 አካባቢ የተመሠረቱት ደግሞ 11ኛ ሻሸጐ ሰባት፥ 12ኛ የጌዮጣ ሰባት ናቸው:: ከ1942-1948 ዓ.ም ባሉት ዘመናት በየአካባቢው ያሉትን ቤተ ክርስቲያናት ከላይ በተዘረዘሩት ማኅበራት ውስጥ በማካተት አደራጁ::

## መ. የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር መቋቋም

የወንጌሉ ብርሃን የጨለማ ኃይላትን ይዞታ እየደረመሰ ነፍሳትን ለክርስቶስ በመማረክ ታላቅ ድልን ተጎናጸፈ::

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት የቤተ ክርስቲያናት መቋቋም ያስቆጣቸው ኢአማንያን (ግኖስቲኮች) ያነሣሡትን ስደት ለመቋቋም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያናት ማኅበራት ጋር በመተባበር አቋመ ሕጉንና የመተዳደሪያ ውስጠ ደንቡን ረቂቅ በሕግ ባለሙያ አስጠንተው ማኅበሩ በሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስቴር ተመዝግቦ "በወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር" በሚል ስያሜ ሰኔ 28 ቀን 1955 ዓ.ም ከመንግሥት ሕጋዊ ፈቃድ አገኙ::

በኋላም ቆይተው እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በየማኅበሮቹ ራሱን ችሎ በድርጅትነት ሲመዘገብ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም በ 1ኛ ዮሐ. 5:12 መሠረት በተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል ላይ "ወልድ ያለው ሕይወት አለው" የሚለውን አርማ በማውጣት በውስጠ ደንባቸው መሠረት በድርጅትነት ተመዘገበ:: በሕዝብ ደኅንነት ጥበቃ ሚኒስቴርም የሥራ ፈቃድ ተሰጥቶት ዕውቅና አግኝቶ ማኅበሩ ሥራውን በመላ ኢትዮጵያ በይፋ ማንቀሳቀስ ጀመረ::

በተለይ ይህን ጉዳይ ለማስፈጸም የማኅበሩን ስም በመሰየም ታላቅ ሚና የተጫወቱትን ከአዲስ አበባ አቶ ላቀው ተሰማንና አቶ ጉሣዬ ዘመድኩንን፥ ከከምባታና ሀዲያ ማኅበር አቶ አበበ ቡሼሮ፥ ከወላይታ ማኅበር አቶ መርኪና መጀን ታሪክ እያስታወሳቸው ይኖራል::

## ሠ. ከ1943-1965 ዓ.ም ድረስ የአንጋፋ ወንጌላውያን የመላክ ሂደት

በዚያን ዘመን ከመንግሥት እንዲህ ዓይነት ሕጋዊ ፈቃድንም ሳያገኙና ካገኙም በኋላ በታላቁ ተልዕኮ በመለኮታዊ ትእዛዝ መሠረት ከ1943 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ በአልበርት ብራንት

ጠያቂነት ከከምባታና ሃዲያ አውራጃ ቤተ ክርስቲያናት ወደ ሲዳማ ጌዴኦ አውራጃና ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ምድር ተልከው ከነበሩት አንጋፋ ወንጌላውያን 1ኛ. ወንጌላዊ ደሌ አወኖ÷2ኛ. ወንጌላዊ ዘኬዎስ ኤርድሎ÷ 3ኛ. ወንጌላዊ ኢዩኤል ፉጌ÷ 4ኛ. ወንጌላዊ በቀለ ወርቁ÷ 5ኛ. ወንጌላዊ ሣህሌ ጆፌ÷ 6ኛ. ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ÷ 7ኛ. ወንጌላዊ ዓለማየሁ በለንገ÷ 8ኛ. ወንጌላዊ ታፌሰ ዕልጎ÷ 9ኛ. ወንጌላዊ መነሾ ጫዕምሶ÷ 10ኛ. ወንጌላዊ ዳና ዳለሎ÷ 11ኛ. ወንጌላዊ አቢዮ ሐሲሶ÷ 12ኛ. ወንጌላዊ ሱጌቦ አቦሴ÷ 13ኛ. ወንጌላዊ አርፍጮ የኖሬ ይገኙበታል:: 14ኛው ወንጌላዊ ያዕቆብ ባፋ በሲዳማ በወናጎ ከተማ ስለ ጌታ ታሥረው ተንገላተው ነበር::

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ሌሎችም ወንጌላውያን በብዛት ተልከዋል::

ወደ ሲዳማ ተልከው የነበሩት:- 1ኛ ወንጌላዊ አየለ ቡኩሎ÷ 2ኛ ወንጌላዊ ዳለሎ ወተንጐ እና 3ኛ ወንጌላዊ ደስታ ሾብሶ÷ እንዲሁም ሌሎች ነበሩ::

ወደ አርሲ ተልከው የነበሩት:- 1ኛ ወንጌላዊ ሺፈራው አረከ÷ 2ኛ ወንጌላዊ ያዕቆብ ባፋ÷ 3ኛ ወንጌላዊ ማቴዎስ ሄመቻ÷ 4ኛ ወንጌላዊ አየለ ለቴቦ÷ 5ኛ ወንጌላዊ ዘለቀ አሸንጐ÷ 6ኛ ወንጌላዊ ወልደነዌ ለጅቦ እና 7ኛ ወንጌላዊ ዲንዳሞ ለሬቦ ነበሩ::

እነዚህ ወንጌላውያን በሲራሮ ቀጫጩሎ ጠንቆ ወንዶ ገነት ዙሪያ እየተዘዋወሩ በሚሰብኩበት ወቅት ምግብ የሚሰጣቸው አጥተው በየጫካ ውስጥ እየተዘዋወሩ ለረሃብ መቅመቆ እየቆፈሩ እየበሉ ልዩ ልዩ ፍራፍሬ ከጹር ውስጥ እየለቃቀሙ ÷ወራጅ ውኃ እየጠጡ በሰይጣን ምርኮ ውስጥ የታሠረውን ሕዝብ ነፃ በማውጣት ዋጋ የሚያስከፍለውን የወንጌልን አደራ ያዳርሱ እንደነበረ ወንጌላዊ ያዕቆብ ባፋ አስረድተዋል::

ወንጌላዊ ኤሃ ጉበና ወደ ኩሎኮንታ ተልከው ነበር:: በ 1964 ወንጌላዊ ኃይሉ ለተሞ÷ ወንጌላዊ ጋሎ በጅጐ÷ ወንጌላዊ ሳሙኤል መልሰቦ÷ ወንጌላዊ ለገሠ ላሎቶ÷ ወንጌላዊ ዮሐንስ አብቼና...ሌሎችም ወደ ጂማ ዙሪያ ተልከው የነበሩ ናቸው::

በ 1950 ዓ.ም ወደ ጨቦና ጉራጌ አገር ተልከው የነበሩት ደግሞ:-1ኛ. ወንጌላዊ ዮሐንስ ሮባ÷ 2ኛ. ወንጌላዊ ዘብዴዎስ ሙጐሮ (ቡታጅራ ጠደሌ)÷ 3ኛ. ወንጌላዊ ሠላሙ አወኖ (ቡታጅራ ጠደሌ)÷ 4ኛ. ወንጌላዊ ዮሐንስ አንሼቦ÷ 5ኛ. ወንጌላዊ ማቴዎስ ዳታጐ÷ 6ኛ ወንጌላዊ ኃይሌ ጉቤ 7ኛ. ወንጌላዊ ኑራሞ ሐምቤቦና...ሌሎችም ነበሩ:: በተልእኮአቸው የጌታ ቃል በተዘራበት በቅሎ በማቴ. 13:23 ተመዝግቦ እንደሚገኘው አንዱ መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ

አፈራ። ከዚህ የተነሣ ሕዝበ ምእመናኑ ጌታቸውን በዝማሬና በሃሌሉያ እስከ አሁን ድረስ እያከበሩ ያገለግሉታል።

ወንጌላዊ አቡዬ ቲርካሦ፥ ወንጌላዊ ጴጥሮስ ሂሰቦ፥ ወንጌላዊ ዮሐንስ አንሼቦ ወደ ልብዶ ከተላኩት መካከል ሲሆኑ፥ በ1950 ዓ.ም ወደ ባሌ ከገቡት ደግሞ ወንጌላዊ በቀለ ወርቁ፥ ወንጌላዊ ታፈሰ ዕልጎ፥ ወንጌላዊ ዮሐንስ አንሼቦ፥ ወንጌላዊ ዮሐንስ ሌንጃሞ ይገኙበታል። ባሌ ጎባ፥ ሮቢ፥ ጉሮ፥ ደሎ ሠብሮ፥ ጉሉልቻ፥ አይብሳ፥ መልዩ ሰልቃ...ወዘተ ተዘዋውረው ነፃ የሚያወጣውን የወንጌል አደራ ያደረሱትን ወንጌላውያንን በሙሉ ታሪክ ያስታውሳቸዋል።

ወንጌላዊ መጋቦ ሔገኖና ወንጌላዊ ወዕሜ አየለ በ1949 እና በ 1950 ዓ.ም ወደ ጐጃም ዳንግላ ተልከው የወንጌልን እውነት ዘርተዋል። በ 1959 ዓ.ም ወደ ኑራኤራ ተልከው የነበሩት ደግሞ 1ኛ ወንጌላዊ ታገሠ ባምቦሮ፥ 2ኛ ወንጌላዊ ዮሐንስ አኑሎ እና 3ኛ ወንጌላዊ ሞላ አቡዬ ናቸው። እነርሱም አደራቸውን ተወጥተዋል።

ከ1958-1964 ዓ.ም ወደ ጐጃም ድባጢ ወደ ምዕራብ ጐጃም ዳንግላ ተልከው የነበሩት፡- 1ኛ ወንጌላዊ ተሰማ ሙጐሮ፥ 2ኛ ወንጌላዊ ታደሰ ኤርቲሮ፥ 3ኛ ወንጌላዊ ጴጥሮስ ኤርቲሮ ሲሆኑ ሌሎችም በተለያዩ ጊዜያት ሄደው የዘሩት ቃል ዛሬ በቅሎ አድጐ ፍሬ በማፍራት ላይ ይገኛል።

ወንጌላዊ ማቴዎስ ዳታጐና ወንጌላዊ ኃይሌ ጎቤ በ1950 ዓ.ም ወደ ትግራይ ማይጨው ተልከዋል። ወንጌላዊ በቀለ ወርቁ እና ወንጌላዊ ዳና ዳለሎ ወደ አላማጣ ተልከው ከሰይጣን እሥራት ነፃ የሚያወጣውን የወንጌል እውነት ዘርተዋል።

በወሎ ደሴ በቦሩ ሜዳ ዙሪያ ተልከው የወንጌልን ብርሃን የፈነጠቁ ደግሞ ወንጌላዊ ኢዩኤል ፉጌ ፥ ወንጌላዊ ታፈሰ ዕልጎ፥ ወንጌላዊ ዮሐንስ ደጋጋ፥ ወንጌላዊ አዲሴ ቤሌሎና ሌሎችም ነበሩ።

ወደ ወሊሶ ተልከው ከነበሩት ደግሞ ወንጌላዊ ዮሐንስ በሊሎ እና ሌሎቹም ነበሩ። እነዚህን አንጋፋ ወንጌላውያንን የወንጌል ስርጭት ታሪክ እያስታወሳቸው ይኖራል።

## ረ. በእነዚያ ዘመናት የሴቶች ተሳትፎ በወንጌል ስርጭት

የምሥራቹን የወንጌል ቃል የማድረስ አደራና ኃላፊነት የወንዶች ብቻ ሳይሆን የሴቶችም ጭምር መሆኑን በዛን ዘመን የነበሩ ሴቶች ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ወንዶቹ ለወንጌል አገልግሎት ሲወጡ

ብቻቸውን መሄድ ስለማይገባቸው ከሴቶች እህቶቻቸው ጋር በጋብቻ ተጣምረው መውጣት ስለነበረባቸው በጋብቻ ላይ የነበረውን የሥጦታ (ጥሎሽ) መናርን ከምባታ ወንጌላዊት በውስጠ ደንብ ደንግገው አስቀሩት:: ለወንጌል አገልግሎት የሚወጣ ወጣትና ወጣቷ ለጋብቻ ከተስማሙ ፈቃደኝነትዋ ተረጋግጦ በዘፍ. 14:56-60 በተጻፈው መሠረት ዘመዶቻቸውም ተስማምተው መርቀው ከባሎቻቸው ጋር ተሰልፈው የወንጌልን አደራ እንዲያዳርሱ ይሸኙአቸዋል::

የወንጌልንም አደራ ለማድረስ በሄዱበት አካባቢ ወንዶቹ በቀን ወንጌልን ለማሰራጨት በሚሄዱበት ጊዜ ባለቤቶቻቸው በጸሎት እየደገፉአቸው የማይሠራ አይብላ በሚለው በጌታ ቃል መርሆ መሠረት ለኑሮ መደጎሚያ እንዲሆንላቸው የእጅ ሙያ እየሠሩና ሕፃናትንም በማሳደግ ኃላፊነት እየተደጋገፉ ቃሉን ያሠራጩ ነበር::

"ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል" (መክ. 4:9)::

በሌላ ጎን ከሊሙ ማኅበር እመት ሀከላ ዓመሌ የሚባሉ እናት የወንጌልን አርማ አንሥተው የእነ አባ ጎሌን ፈለግ ተከትለው ከሊሙ እስከ ባዳዋቾ÷ ቀዕላማ÷ አበንሣ÷ ዌረቦያ÷ ሲቄ÷ ኩየአና ቃጫ ድረስ በእግራቸው እየተተዘዋወሩ እናቶችን እየሰበሰቡ ለመኝታ የሚሆነውን "ጅባ" እንዲሠሩ የእጅ ሙያ በማስተማር ጭምር ወንጌልን በምሳሌ እየዘሩ "ከእምነታችሁ የሚያስከዳችሁ ችግር ሳይሆን ድሎት ስለሆነ ከችግር ስትወጡ ጌታን እንዳትረሱ" እያሉ የብርድንና የፀሐይ ሙቀትን ምሳሌ እያደረጉ "ሰው በብርድ ጊዜ ልብሱን በደንብ ወደ ሰውነቱ አስጠግቶ ይለብሳል:: በሙቀት ጊዜ ግን ልብሱን አውልቆ በእጁ ይይዛል" እያሉ ያስተምሩ ነበር::

## ሰ. የራልፍ ጄኮብሰን አገልግሎት

በ 1945 ዓ.ም ራልፍ ጄኮብሰን በከምባታና ሃዲያ አውራጃ ውስጥ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በማስተማር ቤተ ክርስቲያናትን በሚያደራጁበት ወቅት በትርጉም ሥራ እንዲረዷቸው ከሚሽግዳ ክፍለ ማኅበረ ምእመናን አቶ ሻሜቦ መኪሶ ተመደቡላቸው:: በዱራሜ ሚስዮን ጣቢያ ዙሪያ ያሉትን ቤተ ክርስቲያናትን ለማስተማር ከአቶ ሻሜቦ ጋር ሆነው ዱክ በሚባል ፈረሳቸው ላይ እየተቀመጡ ለማስተማር በሚዘዋወሩበት ጊዜ ፈረሱ በጣም ሯጭ ስለነበረ በቆላ በገደላማ አካባቢ ድንገት ወድቆ አንገቱ ተጠምዝዞ ሞተ:: ጌታ ግን ራልፍ ጄኮብሰንን ጠበቃቸው:: ስለዚህ እርሳቸው በብዙ ቦታ እንደምሳሌ እየተጠቀሙ "እንደ ዱክ ሲሮጡ የዚህ ዓለም ነገር ድንገት ያልፋል!" እያሉ ያስተምሩ ነበር::

ራልፍ ጄኮብሰን ከመንፈሳዊ ትምህርታቸው ጐን የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታን በመስጠት እያገለገሉ ሲኖሩ ጌታ ሥራቸውን ባርኮ ስላሰፋላቸው ሸክሙን ለመጋራት ብዙ ሚስዮናውያን ወደ ዱራሜ ጣቢያ ደረሱ።

የአካባቢውን ልጆች ደብተርና እርሳስ በነፃ እየሰጡ ኑ ተማሩ እያሉ በማባበል የቀለም ትምህርትን በወንዝ ዳር ባለች በትንሽ ሣር ክዳን ቤት ውስጥ ያስተምሩ ነበር። ይህንን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለማስተማር ሚስ ራስል የሚባሉ አስተማሪ ትምህርት ቤቱን ያስተዳድሩ ነበር። የሕክምናን አገልግሎት ለመሸከም ሚስ ሸነል የሚባሉ መጥተው በትንሽ ጎጆ ቤት ውስጥ ሕክምና ይሰጡ ነበር።

በ 1946 ዓ.ም ላይ ራልፍ ጄኮብሰን ለዓመት ዕረፍት ወደ አገራቸው ሲሄዱ በቦታቸው ሚስተር ቶሚሊንሰን የሚባሉ ለወንጌል ሥራ አስተዳደር ለአንድ ዓመት ወደ ዱራሜ መጡ።

እርሳቸውም ስለ ድርብ ጋብቻ እና ስለ አልኮል መጠጥ አላስፈላጊነት አጥበቀው በማስተማራቸው፤ ሁለትና ሦስት ሚስቶች የነበራቸውና የሚያሰክረውንም መጠጥ እየጠጣንም አማኞች እንሆናለን የሚሉት ሰዎች ከመጀመሪያዎቹ አማኞች ኅብረት መካከል "የመጠጥ ማኅበር" ተብለው ተለዩ። ከዚያ ወዲህ የተለያየ የዶክትሪን ልዩነት ትምህርትም ሲገባ እያንዳንዱ እንደ መረዳቱ መጠን ልዩ ልዩ ስም እየወሰዱ መለየት ጀመረ። ሆኖም እነዚህ ሚስዮናውያን ጥሩ መሠረት ቢጥሉም የእኛ መሠረታችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። "የእግዚአብሔር ጸጋ እንደተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (1ኛ ቆሮ. 3:10-11)።

በፊልጵ 3:12-15 በተገለጸው መሠረት የሚሆነውን እውነት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በሚገልጸው መሠረት ሊፈጸም እንደሚገባ የጹሑፉ አዘጋጅ ያምናል።

## ሸ. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች መከፈት

ገስ ካይዘር በዱራሜ ጠዛ በትንሽ ጎጆ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከፍተው ሲያስተምሩ ቆይተው አዲስና ሰፋ ያለው ባለ ቆርቆሮ ክዳን ቤት በ1949 ዓ.ም ተሠርቶ በዱራሜ ጠዛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በ1950 ዓ.ም ተከፈተ።

በተከፈተው ትምህርት ቤትም ውስጥ የአካባቢውን ቤተ

ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ከነባለቤቶቻቸው ያስተምሯቸው ነበር።

ስለ ቤተ ክርስቲያን አያያዝና አስተዳደግ ጭምር የመጽሐፍ ቅዱስን ጭብጥ ቃል ተምረው ወደ እየቀዬአቸው ሲመለሱ አንድ አዲስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲቋቋም ማለትም ከእናት ቤተ ክርስቲያን ተለይቶ ራሱን ሲችል ቢያንስ ቢያንስ መጽሐፍ ቅዱስን ከተማሩት አንድ ሰው መጋቢ መሆን እንዳለበት አጠንክረው አስተምረዋል። ይህም ሁኔታ እስከ ዛሬ እንደ ቀጠለ ነው።

በተጨማሪም በ1949 ዓ.ም ላይ የቀለም ትምህርትን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስተማር ሚስተር ጆን ካምቤል የሚባሉ ሚስዮናዊ መጥተው በእርሳቸው ዳይሬክተርነት በጠዛ ግቢ እስከ 10ኛ ክፍል የተከፈተበት ባለ ቆርቆር ክዳን ቤት ተሠርቶ ሥራው ቀጠለ። የተለያዩ ሚስዮናውያንም መጥተው አገልግሎት ሰጡ።

በቦቢቾና በዱራሜ ሚስዮናዊ ጣቢያ የነበሩት ትምህርት ቤቶች እስከ 6ኛ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፦ በቦቢቾ እስከ 8ኛ በዱራሜ እስከ 10ኛ የቀለም ትምህርት ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዙ ወንጌላውያንን፥ ምሁራን ዶክተሮችን ፕሮፌሰሮችንና የጤና ባለሙያዎችን አስገኝተዋል። እነዚህም ባለሙያዎች እንደየተሰጥዖአቸው በኢትዮጵያ ምድር በያሉበት ሕዝቦችን በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

በዚያን ዘመን የአካዳሚ ትምህርት የጤና ክሊኒኮች፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና የአካባቢ የወንጌል ሥራ ጉብኝት ከብዙ ሠራተኞች ጋር እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በተጠናከረ ሁኔታ ይሠራ ነበር። በዚያን ዘመን በጉብኝት የታወቁ ሚስ መከምበር የሚባሉ ሚስዮናዊት ከወ/ሮ አስቴር አግዴ (አስተርጓሚ) ጋር ሴቶችን እያስተማሩ እስከ ሶሮ፥ ኩየአ፥ ሚሽግዳ፥ ጌዮጣና ጠምባሮ...ወዘተ እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ነበር። ታዲያ በጠምባሮ ሴቶችን በማስተማር ላይ እያሉ ስለ ታመሙ ራልፍ ጀኮብሰን ወደ አዲስ አበባ ወስደዋቸው ሲመረመሩ በሽታቸው ካንሰር ሆኖ ተገኘ። በዚያን ጊዜ ራልፍ ጀኮብሰን ይዘዋቸው ወደ አሜሪካ ሄዱ። ወደ ቤታቸውም ሳይደርሱ በሆስፒታል ውስጥ በጣም እየተደሰቱ ፊታቸው እየበራ ከዚህ ዓለም ተለዩ። በለቅሶአቸው ሥነ ሥርዓት ላይ ራልፍ ጀኮብሰን የእግዚአብሔርን ቃል እየተናገሩ የሕይወት ታሪካቸውን መናገር ሲጀምሩ የሐዘን ተካፋዮች የነበሩት ልባቸው ተነክቶ የጀመሩት ሥራ እንዳይቋረጥ በማለት ገንዘብ አዋጥተው ለራልፍ ጀኮብሰን ሰጡአቸው። እርሳቸውም ገንዘቡን ወደ ኢትዮጵያ ዱራሜ ድረስ አምጥተው የሚስ መከምበርንም ዕቃ ሸጠው ጨምረው በጠዛ ግቢ ለመታሰቢያ የሴቶች ትምህርት ቤት ተሠርቶ ሴቶች ከየአካባቢው

እየተሰበሰቡ ሲማሩ ቆይተዋል:: በአሁኑ ጊዜ (በዚህ ዘመን) ቤቱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ቢሮነት እያገለገለ ነው::



በፎቶግራፉ ላይ የሚታየው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር አቶ አቡዬ ረጃቶ በዚያ ቢሮ ውስጥ የዕለት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ነው:: "እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰዎቹ ላይ የሾመው ታማኝ ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው (ማቴ. 24:45)::

በ1966 ዓ.ም በመጣው የመንግሥት ለውጥ ወቅት በመላ ኢትዮጵያ ከነበሩት ቤተ ክርስቲያናት አብዛኞቹ ሲዘጉ ጌታ በታምራቱ እየተዋጋ የዱራሜ ጠዛ እና የቦቢቾ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና የአካባቢው ከ 600 የሚበልጡ ቤተ ክርስቲያናት ሳይዘጉ ቆይተዋል:: ወደ ሁለቱ ትምህርት ቤቶችም ከጋሙ ጎፋ ማኅበር፥ ከቁጫ ማኅበር፥ ከወላይታ ማኅበር፥ ከዋካ ማኅበር፥ ከጂማ

ማኅበር፥ ከባሌ ማኅበር፥ ከአርሲ ማኅበር፥ ከጎጃም ድባጢ ማኅበር፥ ከወንጂና መተሃራ ማኅበር፥ ከጨንቻ ማኅበር፥ ከወሎ ማኅበር፥ እና ከቡርጂና አማሮ ማኅበር የጌታ ሐዋርያት እየመጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተምረው ለየአካባቢአቸው አደራና ኃላፊነትን እየተሸከሙ ተመልሰዋል።

በዚያን ዘመን በሌሎች አካባቢዎች የነበሩ ጸሎት ቤቶች ተዘግተው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይታሠሩ ነበር። በዚያው ጊዜ ለወደፊት ጌታ ለቤቱ አገልግሎት ሸክም ያላቸውን ሁሉ ከየአቅጣጫው እየመለመለ አምጥቶ ስለ ስሙ በጠበቃቸው ስፍራዎች ላይ ካሠለጠናቸው በኋላ ቤተ ክርስቲያኖቹ በየስፍራው ተከፍተው ሥራቸውን ማንቀሳቀስ በጀመሩበት ወቅት የቤተ ክርስቲያናት ሥራና ኃላፊነት በእነዚህ ሰዎች ላይ ተጣለ።

## ቀ. የሰይጣን ሥራ መሟሸሽ

ሻሸጐ በ1947 ዓ.ም ከአቶ ጫዕምሶ አንቼ የተነገረ ታሪክ።



በፎቶግራፉ ላይ አጠር ብለው የሚታዩት አቶ መናሞ ሁሮ ከአቶ ጫዕምሶ ጋር ሆነው ለብዙ ዘመናት የወንጌልን ዓርማ ያነሡ ናቸው::

በመጀመሪያ በሻሸጐ ምድር ጌታን የተቀበሉት:- 1ኛ አቶ አርታቦ ባደሮ÷ 2ኛ አቶ ጫዕምሶ አንቼና÷ 3ኛ አቶ ገለቶ ከኬቦ ነበሩ::

በከምባታና ሃዲያ ምድር በስተ ምሥራቅ በሚገኘው ሸለቆ ውስጥ ዛሬ ከ37 የሚበልጡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: በመጀመሪያ የወንጌልን ችቦ ያበሩት አቶ አርታቦ ባደሮ÷ አቶ ጫዕምሶ እና አቶ ገለቶ ነበሩ:: እነርሱም ገና በወጣትነታቸው ጌታን አምነው በአካባቢአቸው ለሚገኘው ሕዝብ ለትንሹም ለትልቁም ወንጌልን እየሰበኩ ይዞሩ ነበር::

በዚያን ዘመን በዚህ ሸለቆ ውስጥ የነበረው ሕዝብ በሙሉ (የከምባታ ብሔረሰብ) ከባሕር ወለል 3000 ሜትር በላይ ከፍ ብሎ ወደ ሚገኘው ወደ አምባርቾ ተራራ ድረስ እየወጣ አባ ሠሬቾ ለተባሉ ጠንቋይ ይሰግድ ነበር:: ይመለክ የነበረው ጠንቋዩም የጠንቋዮች ሁሉ አለቃ ነኝ ስለሚል ሕዝቡ ሁሉ አባ ሠሬቾ ለሚባለው ለዚህ ሰው ልዩ ልዩ ስጦታዎችን እየወሰደ እጅ መንሻ ያበረክት ነበር::

የሻሸጐ ሕዝብም ሲገዛለት የነበረው ይህ የተራራው ጠንቋይ አባ ሠሬቾ በሻሸጐ በአቶ ጫዕምሶ አንቼ ቤት አጠገብ የነበረችውን ልጃገረድ ሊያገባት ጀርባዋን መትቷት እጮኛው ሆና ትኖር ነበር::

ጠንቋዩ ከአጫት ጊዜ ጀምራ ፀጉሯ አይላጭም÷ አትታጠብም÷ ወዟ ደርቆ ውበቷን አጥታ አመዳም ሆና መኖሯ ለጠንቋዩ ክብሩ ነበር::

ከዕለታት አንድ ቀን ከሩቅ አገር የዘመድ ለቅሶ መጥቶ ጐረቤቶች በሙሉ ተጠራርተው ለቀብር ሲሄዱ የልጅቷ ቤተሰቦች ቤት ንብረታቸውን አስጠብቀዋት ሄዱ::

በዚያ መኻል አቶ ጫዕምሶ ወደ ልጅቷ ሄደው "ከአባ ሠሬቾ እሥራት ትፈቺያለሽና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመኚ " አሉአት:: እርሷም "አባ ይገድሉኛል" አለች:: አቶ ጫዕምሶም መልሰው "ኢየሱስ እኮ ከአባም በላይ ነው አትሞችም፤ ብቻ እመኚ" አሉአት:: ልጅቷም "እንደዚህ ከሆነማ እሺ አምናለሁ" ብላ ቀኝ እጇን አንሥታ "ሰይጣንን ክጄ ኢየሱስን አምኛለሁ" ብላ ጌታን ተቀበለች:: አቶ ጫዕምሶም ወዲያውኑ ውኃ አሙቀው ፀጉሯን አጥበው ላጩአት:: ቀጥለውም "ወላጆችሽ ቢመጡ ስለሚያስከፉሽ አማኞች በብዛት ወደ ሚገኙበት አካባቢ እንሸሽ " አሉአት:: እርሷም ቤተሰቦቿ ቤት ንብረቱን ሁሉ አደራ ሰጥተዋት ስለሄዱ ልትሰደድ ፈቃደኛ አልሆነችም::

ወደ ማታ ወላጆቿ ተመልሰው መነካት የሌለበት ፀጉሯ ተላጭቶ ስላዩአት ወዲያውኑ ኡኡታውን አቀለጡት፡፡ ጎረቤቶቻቸው ምን መጣ በማለት እየተሯሯጡ ወደዚያ ቤት ሲሄዱ አንዱ ጦር የያዘ ሰው ጦሩን እየሰበቀ ሲሮጥ አቶ ጫዕምሶ በሰፈሩ ባለው ጉብታ ላይ ሆነው ይመለከቱ ነበር፡፡ በዚህ ጦር ይወጋኝ ይሆን ብለው በልባቸው ሥጋት ነበር፡፡ ሆኖም ጌታ ተጠነቀቀላቸው፡፡ ያ ጦሩን ነጥቆ የመጣው ሰው በጩኸት ወጥቶ ለተሰበሰበው ሕዝብ "ይህችን ልጃገረድ ፀጉሯን የላጫት ጫዕምሶ ከሆነ ዘንዳ ነገ ጧት ወደ አባ ሠሬቾ አንድ እንሥራ ማር ይዞ ሄዶ ጉዳዩን ነገሮ ከማስገደል በስተቀር ሌላ መፍትሔ አይኖርም!" በማለት አሳብ አቀረበ፡፡ ሕዝቡም በዚሁ አሳብ ተስማምቶ በማግሥቱ ከአካባቢ ሽማግሌዎች ለትዝብት ተጨምረው ልጅቷንም ይዘው ማሩን አሸክመው ወደ ጠንቋዩ ሄዱ፡፡ ጠንቋዩ ጓዳ ውስጥ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ነበር፡፡ የልጅቷም አባት በጠንቋዩ ፊት ቆሞ "እኛ በሌለንበት አንድ ልጅ የእጮኛዎን ፀጉር ስለላጫት እንዲገድሉት ልንነግርዎ ነው የመጣነው፤ ልጅቷም ይችትና" በማለት የሄደበትን ጉዳይ ተናገረ፡፡

ጠንቋዩም ከተቀመጠበት ወንበር ላይ አንገቱን አስግጎ ዓይኑን አፍጥጦ በቁጣና በንዴት ቃል "ምን ዓይነት ደፋር ነው እንዲህ ሊነካት የቻለው?" ብሎ በፉከራ ቃል ጠየቀ፡፡

የልጅቷም አባት "በጎረቤታችን አንድ በኢየሱስ ያመነ ወጣት (የሱስ መና የሆነ) ይህንን አደረገ" ብሎ ሊናገር ገና ከአፉ የኢየሱስን ስም ሲጠራ ረዝሞ የነበረው የጠንቋዩ አንገት ወደ ውስጥ ገባ፡፡ አንደበቱ ተሳስሮ ልሳኑም ተይዞና "እኔ አልችለውም፡፡ ኃያሉን ጌታ መቋቋም ስለማልችል የምታደርጉትን እነግራችኋለሁ፤ ከዚህ ተመ-ልሳችሁ እንደሄዳችሁ የላጫት ሰውዬ የእጁ ጥላ በልጅቷ ላይ ስላረፈ፥ ጥላው እንዲለቅቃት በድጋሚ ላጩአት" ብሎ መመሪያ ሰጠ፡፡ ሰዎቹም የእንስራውን ማር አስረክበው ሲመለሱ በልጅቷ ላይ አርፎ የነበረው የአቶ ጫዕምሶ ጥላ የኢየሱስ ጥላ ተምሳሌት በመሆኑ ጠንቋዩ ፈርቶ በልጅቷ ላይ ያደረውን የእግዚአብሔር ኃይል እንደማይችለው አምነው ተመለሱ፡፡ "ለካስ ይገድለናል ብለን ለሰይጣን እየገበርን የምንኖረው በከንቱ ኖሯል?" በማለት ሕዝቡ ወደ ጌታ ዞር አለ፡፡

"እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፡፡ ስለዚህ ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወስዱ ነበረ፡፡ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር፡፡ ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር" የሐዋ. 19፡11-12)፡፡

በአባቶቻችን ዘመን የአማኞች እጅ የጨበጠው ይፈወስ ነበር፡፡

አጋንንትም እየጮኹ ይሰደዱ ነበር:: "ወገኖች ርኵሳን መናፍስት በኢየሱስ ታላቅ ኃይል ድል ተመትተዋል:: አታላዩን ሰይጣንና አጋንንትን አትፍሩ፤ አታምልኩ:: ወንጌል ነፃ ያወጣልና ወደ ኢየሱስ ኑ!

## ሠ. የቤተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ በዘመነ-ደርግ (1966-1983 ዓ.ም)

በ1972 ዓ.ም የከምባታና ሃዲያ አውራጃ አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበረ ሰው "በዱራሜና በሾኔ ቀይ ሽብር አፋፍማለሁ" ብሎ ውስጥ ለውስጥ ለወረዳ አስተዳዳሪዎች "በዚህ ቀን ስለምመጣ የእምነት አባቶችን ዋና ዋና ሰዎችን በሾኔና በዱራሜ ሰብስባችሁ ጠብቁኝ" በማለት ምሥጢራዊ መልእክት አስተላለፈ::

በትእዛዙም መሠረት በተቀጠረው ቀን ወደ አደባባይ ሊቀርቡ የሚሸግዳ ክፍለ ማኅበር መሪ አቶ አየለ አንዮና የቤተ ክርስቲያን መዘምራን ተይዘው በሾኔ ከተማ አንድ ተሠርቶ ባላለቀ ቤት ውስጥ ታሠሩ:: ቤቱም መዝጊያ የሌለው በመሆኑ በውስጡ በቆሻሻ ዝቃጭ የተሞላ ስለነበረ እሥረኞቹ ተንበርክከው ጌታን የሚጠሩበትን አጥተው ሲቸገሩ ጌታ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስን ልኮ የቤቱን ቆሻሻ ሙልጭ አድርጎ ጠርጎ የቤቱን ጣሪያ በታተነ:: በዕለቱ በሾኔ ከተማ የብዙ ሰዎችን ቤት ጣሪያ ነፋሱ ነቃቀለ:: ከዚያም ወደ ሌላ ሁለተኛ ቤት ወስደው አሠሯቸው:: በድጋሚ ያንንም ቤት ጌታ ኃይለኛ ነፋስ ልኮ ነቃቀለ:: ወደ ሦስተኛም ቤት ወስደው አሠሯቸው:: በዚያ ቤት ሌሊት ሲገርፉቸው የነበረው ካድሬ እጁ ደነዘዘ:: በዚያው ምሽትም አበደ:: ሳይነጋ ወደ ወሊሶ ጠበል ተወሰደ፤ በዚያው ሞተ:: እሥረኞቹም ይህንን ሰሙ:: ጌታም ከእነርሱ ጋር መሆኑን ስላረጋገጠላቸው ጸጋው በዛላቸው::

በቀጠሮው ቀን ከላይ የተጠቀሰው ባለሥልጣን ቀይ ሽብርን ለማፋፋም ታጥቆ ተነሥቶ ከሆሣዕና ከተማ በጂፕ መኪና ብቻውን ተቀምጦ ወደ ሾኔና ወደ ዱራሜ ጉዞ ጀመረ:: ሆሣዕና ከተማ ሲደርስ ሁለት ሴት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሊፍት ጠይቀውት አብረው ሲመጡ ወደ ሌሾ ማዞሪያ ለመድረስ ጥቂት ኪሎ ሜትር ሲቀረው በአውላላ ሜዳ ላይ እየበረረ ሳለ መኪናው ተገለበጠ:: በደረሰበትም አደጋ ሰውዬው ከወገቡ በታች ሽባ ሆኖ እዚያው ወደቀ:: እነዚያ ልጃገረዶች ግን ጌታ ለምስክርነት ያስቀመጣቸው ስለነበሩ ምንም ሳይሆኑ ቀሩ:: ቀይ ሽብሩም በዚህ ሁኔታ ሳይፈጸም ተገታ:: እግዚአብሔር አምላክም ተዋጊነቱን አስመሠከረ::

በዚያ ዘመን በነበሩት አማኞች መካከል በአባቶችና በልጆች መካከል ከፍተኛ መግባባትና ፍቅር ነበር:: የቤተ ክርስቲያናት መሪዎች በወርሃዊ ስብሰባ ጊዜ በነበራቸው አንድነት በመጀመሪያ ከጌታ ኃይል ለማግኘት የእንብርክክ የጸሎት ጊዜ ነበራቸው::

ከጌታ ኃይል ካገኙ በኋላ የጌታን ቃል ሰምተው ወደ ዕለቱ ውይይት ሲገቡ፥ የመጀመሪያ አጀንዳቸው በወንጌል ስርጭት ዓላማ ላይ ያተኩራል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔርም ዓላማ በነፍሳት መዳን ጉዳይ ላይ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያንም በምድር ላይ ያለችው ለዚሁ ዓላማ ስለሆነ ነው:: የወንጌላውያንን ስንቅ ከየተወካዮች መሰብሰብና ገንዘቡን በወንጌል ስርጭት ማዋል ተቀዳሚ ሥራቸው ነበር:: ሽማግሌዎቹ ወንጌላውያንን ወደ ሄዱበት አቅጣጫ በመሄድ እየጎበኙ ያጽናኑአቸው ነበር:: ጌታም አብሯቸው ይሠራ ነበረ::

ቤተ ክርስቲያናትም እንዳይዘጉ በመጠበቅ ቸርነቱን አሳይቷል:: የፈርዖን ቍጣ የእስራኤልን ሕዝብ ሊጨርስና ሊነካ ያለመቻሉና ጌታ በኮሬብ ተራራ በቍጥቋጦ ላይ እሳት ሲነድ ቍጥቋጦው ሳይቃጠል ያሳየው ትዕይንት በዚያን ዘመን ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ተደርጎላታል (ዘጸ. 3፡1-12)::

በዘመነ-ደርግ ፍልስፍናው ለቤተ ክርስቲያናት የማይመች በመሆኑ በቀጥተኛና በተዘዋዋሪ መንገድ ቤተ ክርስቲያናትን ለማዳከም ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ነበር:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ዘመን ይልቅ ውስጥ ለውስጥ ተጠናክራ ነበር:: በመጀመሪያው መቶኛ ዘመን ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ለመጽናናትና ለመጸለይ ይሰበሰቡ የነበረው በግለሰቦች ቤት ነበር:: በቆሮንቶስ ከተማ የነበሩት አይሁዳውያን ባልና ሚስት አቂላና ጵርስቅላ ቤታቸውን ለዚህ ለተቀደሰ አገልግሎት ሰጥተው ነበር (የሐዋ. 18፡2 ፤ ሮሜ 16፡5)::

"ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል:: ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና::" (ማቴ. 18፡19-20):: በዚህ ዓይነት ኅብረት የተጸለየውን ጸሎት ጌታ ስለሚሰማ ለሚያስቸግራት መንግሥትም ቤተ ክርስቲያን ጸሎትዋን ቀጠለች [መዝ.(34)፡15፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡1-2] :: የጌታ ልጆች የአምልኮን ስልት ቀይረው በየቤታቸው ተሰብስበው ጌታን ማምለክ ጀመሩ::

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመለከት ቤተ ክርስቲያንን የሚያዳክማት የጸሎት ማነስ፥ የኢኮኖሚ ችግር፥ የእርስ በርስ አለመስማማት፥ የማኅበረሰቡ መለዋወጥና የሐሰት ትምህርቶች...

ወዘተ እንጂ በፖለቲካ በኩል የሚመጣ ችግር አይደለም:: ይህ ቤተ ክርስቲያንን ውስጥ ለውስጥ ያጠነክራታል እንጂ ከቶውንም አያዳክማትም:: በተጨማሪም የሚያዳክማት ነገር ቢኖር ከመንግሥት ጋር በመንፈሳዊ ጉዳዮች በለዘብተኛ አቋም መስማማት ነው:: የቤተ ክርስቲያንን መሪዎችና አገልጋዮችዋን መንግሥት ታማኞች ናችሁ በማለት ለጌታ ሥራ ጊዜ እንዳይኖራቸው በማድረግ በከባድ ኃላፊነት ውስጥ ሹመት መስጠት ስልቱ ነው:: የደርግ መንግሥት በአገልጋዮቻችን ላይ ያሳየው ይህንን ነበር :: በአጠቃላይ የደርግ መንግሥት ለከፋት ያደረገው አሳብ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ትልቅ መሠረት ጥሎልን አልፏል::

ጌታ ደግሞ ለልጆቹ የሚጠነቀቅ አምላክ በመሆኑ በምእመኑ ደረጃ የቤት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ተጠናከረ:: ከዚያም አልፎ በየሠፈሩ ለማኅበራዊ ጉዳይ ምክሮችም ጭምር በተሰበሰቡበት ትንንሽ የቤተ ክርስቲያናት ቡድኖችን አደራጁ::

በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ይወርድ የነበረው በነቢያት፥ በካህናትና በነገሥታት ላይ ነበረ:: በአዲስ ኪዳን ግን ባመኑት ሁሉ ላይ ስለሚወርድ በበዓለ ኀምሳ ቀን የጀመረው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ስደትን ለመቋቋም ዋነኛና ዓይነተኛ ኃይል ሆነ:: በሐዋርያት ዘመን የነበረች ቤተ ክርስቲያን ስደትን ተቋቁማለች፥ ለዓለምም ወንጌልን አድርሳለች፥ ቅዱሳንን መንከባከብ ችላለች፥ ኅብረተሰቡንም ቀይራለች፥ እግዚአብሔርንም ለማምለክ ችላለች፥ አባሎችዋም በጸጋ ደስተኞች ሆነዋል፥ በድህነታቸውም ረድተዋል (2ኛ ቆሮ. 8፡1-3)::

አሁንም ትናንሽ የቤተ ክርስቲያናት ቡድኖች መጠናከር ይኖርባቸዋል:: የአምልኮ ሥነ ሥርዓቶች በቤተ ክርስቲያን በየቤቱ ደግሞ በኃላፊው ማለትም ወንጌልን በሚያውቀው ወይም በምታውቀው አስተባባሪነት ቢቀጥል ለሚከተሉት ነጥቦች ይረዳል::

1. የእያንዳንዱን አባል ጸጋ ለመጠቀምና ለማሳደግ

2. የጌታን ቃል በጥልቀትና በስፋት ለማጥናት

3. በጸሎት ሕይወት ለማደግ

4. የአምልኮን ሥነ ሥርዓት ለመለማመድ

5. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማደግ

6. በጌታ መደገፍን ለመለማመድ...ወዘተ::

ይህ ዓይነቱ አሠራር ከቤተሰብ ወደ ትንሽ ቡድን ማደግ

ያስፈልገዋል:: መሪዎችንም በየቡድኑ ማሠልጠን ብሎም የክትትል ትምህርት በመስጠት ማሳደግ ነው:: አንድ ዛፍ ግንዱ ጠንካራ ሆኖ በቅርንጫፎቹ ላይ መልካም ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው ሥሩ ጠንካራ የሆነ እንደሆነ ነው:: "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥..." (ኤፌ. 3:17-19)::

"የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤.." (ቆላ. 3:16)::

"...የገገር ቊጣ የተነሣብህ እንደሆነ ሥፍራህን አትልቀቅ::" (መክ. 10:4)::

በዚህ ዓይነት የተቀናጀች ቤተ ክርስቲያን ከውጪ ነፋስ ቢገፋት በዐለት ላይ ስለተመሠረተች አትወድቅም::

# ምዕራፍ አምስት

# ከ 1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለው

# የቤተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ

ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ በመሆኑና መንጋዎቹን ወደ በረቱ ለመሰብሰብ ጊዜው በመቃረቡ በሩ ተከፈተ [መዝ. (119):126፤ ዮሐ. 10:16 እና 27-28] ::

በከምባታና ሃዲያ ምድር አሁን ያሉት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች አብያተ ክርስቲያናት ቃለ ሕይወት፥ መካነ ኢየሱስ፥ መሠረተ ክርስቶስ፥ ሙሉ ወንጌልና የሕይወት ብርሃን ናቸው:: እነርሱም በግንዱ አንድነት በቅርንጫፍ ልዩነት በመሠረተ እምነት በመስማማት አገልግሎታቸውን በኅብረት እያከናወኑ ነው:: "ሄዳችሁም:- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ::" (ማቴ. 7:10) የሚለውን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ በየስፍራው በመተግበር ላይ ይገኛሉ::

በተጨማሪም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዋዜማ መደረግ ያለበትን እውነት ለመግለጽ "በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው፥ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፥ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ" (ዕብ 10:25) በሚለው መሠረት በየአብያተ ክርስቲያናት

ዙሪያ ከሞት ወደ ሕይወት፥ ከድካም ወደ መንፈሳዊ ብርታት፥ የሚያደርስ መነቃቃት በመካሄድ ላይ ነው::



በሥዕሉ ላይ የሚታየው በከምባታና ሃዲያ አውራጃ በዌራሞ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከነሐሴ 4-6 ቀን 1982 ዓ.ም በተካሄደው የማነቃቂያ ፕሮግራም ላይ ሰውን ከኃጢአት ቀንበር ነፃ የሚያወጣ የወንጌል እውነት ሲሰበክ ነው:: "እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ::" ተብሎ ተጽፎአልና::



በዚህ ሥዕል ላይ የሚታየው ደግሞ ከምባታና ሃዲያ አውራጃ በሻሸጐ አፍቶ ቤተ ክርስቲያን ከግንቦት 17-19 ቀን 1982 ዓ.ም ብዙ ሰዎች ከኃጢአት እሥራት ነፃ ወጥተው ሕይወታቸውን ለጌታ እንዲያስረክቡ ምክንያት የሆነ መንፈሳዊ መነቃቂያ ፕሮግራም ነው:: እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚፈልገው ሥነ ምግባር ሕይወትን ለእርሱ አስረክቦ ማገልገልን ነው:: "ከእርሱ ጋር ለመሥዋዕት ኪዳን የቆሙትን ቅዱሳኑን ሰብስቡለት" [መዝ. (50):5]::



በ 1983 ዓ.ም የወንጌል አደራ ተረካቢዎች

በዱራሜ ከተማ በቍጥር 1 ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በድል ማለዳ በእሑድ አምልኮ ፕሮግራም ላይ የወንጌል አደራ ከእግዚአብሔር በጸጋ የሚሰጥ ከባድ አደራ ነው:: ይህን ከባድ አደራ ከተቀበሉ በኋላ ተደላድሎ በመቀመጥ የሚሠራ ሳይሆን በመከራና በሞት ውስጥ አልፎ የመጣ ስለሆነ ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከአሁን በኋላም ከአባቶች አደራውን ተረካቢ የሆኑ ወጣቶች ወንጌል የሚጠይቃቸውን መሥዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል::

“...እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፥ የሕይወትንም አክሊል

እሰጥሃለሁ" (ራእይ 2:10)።

"... ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ።" (1ኛ ቆሮ. 9:16)።

በምድር ላይ እውነተኛ የጌታ ሥራ ቅንጅት

"ወደ ዓለም ሄዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" ብሎ ጌታችን ባዘዘን መሠረት የምሥራቹን ወንጌል ቃል ወደ ምዕራብ ጐጃም ለማድረስ ጸሐፊው ሰኔ 1987 ዓ.ም በዝግህ በረሃ ጉዞ ውስጥ ነው።

"ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል፥ ብላቴኖች ይደክማሉ፥ ይታክቱማል፥ ጐበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፥ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፥ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፥ ይሮጣሉ ፥ አይታክቱም፥ ይሄዳሉ አይደክሙም" (ኢሳ. 40:29-31)።

"እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፥ እስከ ሽበትም ድረስ

እሸከማችኋለሁ፥ እኔ ሠርቻለሁ፥ እኔም እነሣለሁ፥ እኔ እሸከማለሁ፥ እኔም አድናለሁ" (ኢሳ. 46:4)።



የከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ባላት ኃላፊነት የወንጌል አደራ በፊልም አማካይነት በኢትዮጵያ ምድር ስታስተምር በ1987 ዓ.ም በምዕራብ ጐጃም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጌታን በየግላቸው ዐውቀው ሳያምኑ በወላጆቻቸው በውርስ እምነት ብቻ ጌታን ሲያገለግሉ የነበሩትን ሕፃናት የወላጆቻቸው እምነት እነርሱን እንደማያድናቸው ተረድተው፡- ከሰይጣን ግዛት ወደ ኢየሱስ ሲገቡ በልባቸው የወሰኑትን የእምነት ቃል ኪዳናቸውን ውሳኔ ለማጽናት እጅ በማንሣት በማረጋገጥ በየግላቸው ለመዳን ጌታን ወደልባቸው

ሲቀበሉ። ይህም በሮሜ 10፡10 “ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል በአፉም መስክሮ ይድናል።” በሚለው በአምላካችን ቃል መሠረት ላይ ነው።

“ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ” (ማቴ. 10፡32-33)።

“ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።” [መዝ. (68)፡31]።

“ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ ፥ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ፥ እላችኋለሁና” (ማቴ. 18፡10)።





ሰኔ 20 ቀን 87 ዓ.ም በምዕራብ ጐጃም በዳንግላ ከጉሙዝ ብሔረሰብ ጌታን የተቀበሉት ወገኖች:-

"...በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ (ራእይ 5:9-10)::

"ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው:: እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፥ አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ አሉት" (የሐዋ. 16:30-31)::



በ 1988 ዓ.ም የከምባታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስተባባሪዎችና ወንጌላውያን በዱራሜ ጠዛ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በራፍ

"እንግዲህ እኔ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፡- በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጐ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ:: እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል::" (1ኛ ጴጥ. 5:1-5)::

# ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ሁሉ አባቶቻችን ስለ ጌታ ፍቅር ብለው በከፈሉት መሥዋዕትነት

- ሕይወታቸውን የሠውበትን፥
- ሬሳ ተሸክመው የተንገላቱበትን፥
- ሀብታቸውን የተዘረፉበትን፥
- የፌጥኝ ታሥረው የተገረፉበትን፥
- በወህኒ የተጣሉበትን፥
- የዓለም መቀለጃ የሆኑበትን፥
- በዘመዶቻቸው የተጠሉበትን፥
- ከዓለም ተለይተው የጠበቁትን፥
- በፍቅር ያቆዩትን፥
- ከሰይጣን ጋር ታግለው ያሸነፉበትን፥
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተጋድሎ ያቆዩትን እውነት እንልቀቅ::

ኢየሱስ በዮሐንስ 8:32 "እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው::"

አባቶቻችን ይህንን እውነት ተረድተው የያዙት የእውነት እምነት ነፃነትን አጎናጽፎናል:: ታሪካችንንም ለውጦአል::

"በተወለድሽበት ቀን ከሰውነትሽ ጉስቍልና የተነሣ በሜዳ ላይ ተጣልሽ እንጂ ከዚህ አንዳች ይደረግልሽ ዘንድ ዓይን

አልራራልሽም፥ ማንም አላዘነልሽም::

"በአንቺም ዘንድ ባለፍሁ ጊዜ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ...ነገር ግን ዕርቃንሽን ሆንሽ፥ ተራቍተሽም ነበርሽ:: በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ፥ እነሆ፥ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበረ፤ እኔም መጐናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ ኅፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽም ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ አንቺም ለእኔ ሆንሽ:: በውኃም አጠብሁሽ ከደምሽም አጠራሁሽ በዘይትም ቀባሁሽ:: ወርቀ ዘቦም አለበስሁሽ በአቆስጣ ቁርበትም ጫማ አደረግሁልሽ፤ በጥሩ በፍታ አስታጠቅሁሽ በሐርም ከደንሁሽ:: በጌጥም አስጌጥሁሽ በእጅሽም ላይ አንባር በአንገትሽም ላይ ድሪ አደረግሁልሽ:: በአፍንጫሽም ቀለበት በጆሮሽም ጉትቻ በራስሽም ላይ የክብር አክሊል አደረግሁ:: በወርቅና በብር አጌጥሽ፥ ልብስሽም ጥሩ በፍታና ሐር ወርቀ ዘቦም ነበረ፤ አንቺም መልካሙን ዱቄትና ማርን ዘይትንም በላሽ፤ እጅግ በጣም ውብ ሆንሽ ለመንግሥትም ደረስሽ:: ባንቺ ላይ ካኖርኋት ከክብሬ የተነሣ ውበትሽ ፍጹም ነበረና ዝናሽ በአሕዛብ መካከል ወጣ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር (ሕዝ. 16፡5-14)::

"ዛሬ እኔ አንተን የማዝዘውን ትእዛዙንና ፍርዱን ሥርዓቱንም ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ፤ ከበላህና ከጠገብህ በኋላ፥ መልካምም ቤት ሠርተህ ከተቀመጥህበት በኋላ፥ የላምና የበግ መንጋ ከበዛልህ በኋላ፥ ብርህና ወርቅህም ያለህም ሁሉ ከበዛልህ በኋላ፥ ልብህ እንዳይኰራ፤ ከግብፅም ምድር ከባርነት ቤት ያወጣህን፥... መና በምድረ በዳ ያበላህን አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ፤ በልብህም፦ ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን ሀብት አመጣልኝ እንዳትል" (ዘዳግ. 8፡11)::

ነገር ግን በጸሎታቸው ዕንባ ያቆዩልንን ንጹሕ የወንጌል ቃል የሚያደፈርስ ክፉ ጠላት ሰይጣን ወደ አማኞች አንበሳ መስሎ መጥቶ የነበረው አሁን ስልቱን ቀይሮ ለማዳ ነብርና ወዳጅ መስሎ ቀርቦ ነው የሚሠራው:: ሰው ኃጢአት እንዳይሰማው አድርጎ አንድ ቀን በጉሮሮው ላይ ሊወጣ ያለው የጨለማ ኃይላት የንስሐ ሕይወትን በመከልከል ሰው ቅድስናውን ፍጹም እንዳያደርግ በማድረግ፥ በአባካኝ ሕይወት ውስጥ በማስገባት ለጌታ ቃል ጀርባ እንዲሰጡ በማድረግ አንድነትንና ፍቅርን በማሳጣት ታላቅ ስውር ውጊያ በማድረግ ላይ ነው:: የወንጌልን እውነት አዛብቶ የእግዚአብሔርን ድምፅ እንዳይሰሙ ቀድሞ ወደ ወጡበት ወደ ጨለማ የሰይጣን ሰንሰለት እንዲመለሱ ታላቅ ጥረት በማድረግ ላይ ነው::

የገሃነም ደጆች ሊይዙት የማይችሉት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ

ወንጌል የጠላትን ኃይል እያከሸፈ እስከዚህ ደርሷል:: በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን:: እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ::... የሚያናውጣችሁ ማንም ቢኖር ግን ፍርዱን ሊሸከም ነው:: "እንግዲህ ጌታ በደጅ ነው" ::እያንዳንዱ ሰው በያለበት በየቀዬው ላልዳኑት የወንጌልን እውነት እየመሰከረ ንስሐ እየገባ ቅድስናውን ፍጹም እያደረገ የጌታችንን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በክብር መመለስ በተጠንቀቅ መጠበቅ እንደሚኖርበት መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል (1ኛ ተሰ. 5:22-23፤ 2ኛ ጴጥ.3:14፤ 1ኛ ተሰ. 4:3)::

ስለዚህ ቀን መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን መልስ ማቴ. 24:44 "ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና" ሚልክ. 3:1-4፤ 1ኛ ተሰ. 5:23:: "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል" (2ኛ ጴጥ. 3:9)::

"እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችንም አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን" (1ኛ ቆሮ. 15:51-52)::

"ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ ላይ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና:: እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ" (ሉቃ. 21:34-36)::

ነፃ የሚያወጣውና ታሪክን የሚለውጠው እውነተኛ ወንጌል የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ምድራችንና ሕይወታችንን ስለጐበኘ የእግዚአብሔር ስም እስከ መጨረሻው ድረስ ይባረክ!! የታሪኩ ተረካቢ ባለአደራዎችም እስከ መጨረሻው አጽንተን እንድንይዝ ጌታ ጸጋውን ያብዛልን!! አሜን::

ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ ቅዱሳኖችም ቅድስናቸውን ፍጹም ሲያደርጉ (1ኛ ጴጥ. 1:15-16፤ 1ኛ ተሰ. 4:3-8) በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል (ማቴ. 24:14):: "ይህንን የሚመሰክር አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል:: አሜን:: ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" (ራእይ 22:20)::

ስላለፈው አገልግሎት ሁሉ ጌታ ይክበር!

በሚመጣውም የጌታ ዕቅድ ይፈጸም! አሜን::

# ዋቢ መጻሕፍት


1. አቶ ዳዕሞ አበበ ከታሪክ ማኅደር ነሐሴ 5 ቀን 1983 ዓ.ም
2. Count It All Joy: Testimonies From a Persecuted Church as Told to John Cumbers, 1995 G.C.
3. ክርስትና በኢትዮጵያ፥ በኤስ.አይ.ኤም ማተሚያ ቤት ታተመ።
4. የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፥ በዶክተር ቻርልስ ሲ.ራይሪ ተጽፎ በሲሳይ ደሳለኝ ተተረጎመ፥ በሳፕስሊ ብሩክስ ፋውንዴሽን አሳታሚነት በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ፤ 1987 ዓ.ም
5. Amharic Rev. Bible 1967-Ro 63 B.F B.S , 1962 Printed in Great Britain.
6. Life of Christ (Original title Studies in the Life of Christ) by Irving L Jensen. Copyright @ 1969 by the Moody Bible Institute of Chicago, printed in the USA.